
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፩ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ጥር/የካቲት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.




© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ጭፈራ - ለሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማሠርያ

በጀርመን ሙኒክ ከተማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ለሚሠራው ሕንፃ ገቢ ለማግኘት የጭፈራና የዳንኪራ ዝግጅት ተካሂዷል:: ዝግጅቱን ለየት የሚያደርገው:- ፕሮግራሙ በሙኒክ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በጸሎት መከፈቱ፣ ከ10,000 ብር ያላነሰ ክፍያ የሚከፈላቸው የናይት ክለብ ዘፋኞችና ባንድ መታጀቡ፣ «የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን» በሚባለውና ከ0በይት በዓላት አንዱ በኾነው የጳራቅሊጦስ ዕለት መካሄዱ፣ የተለያዩ አልኮል መጠጦች በሽያጭ እየቀረቡ ሁኔታው ለውጭ ዜጎችና ለኢትዮጵያውያን ሕፃናት የአገራችን ባህልና ሥርዐት ተደርጎ መቅረቡ፣ በመጨረሻም በጀርመን የቤተ ክርስቲያን ልሳን ነው ተብሎ በሚታወቀው <ሰላማ> መጽሔት ላይ እንዲወጣ፣ በአርኣያነትም እየተጠቀሰ ወደ ሌሎቹም አጥቢያዎች እንዲስፋፋ መደገፋቸው:: ይህን እያየንና እየሰማን የቤተ ክርስቲያን ሥርዐትና ትውፊት ተብላሽ፣ የአገር ባህል ተዛባ፣ ብለን ውስጣችን እየተቃጠለ ብዙ ጊዜ ቆየን:: አሁን ግን ጉዳዩ ትችት እንዲሰጥበትና የሚመለከተው ክፍልም ርምጃ እንዲወስድ በማለት አስተያየታችንን ለመጻፍ ተነሣን:: ምን ይሻለን ይሆን ....?

ከምእመናን አንዱ
ጀርመን

## መዘባበቻ ባያደርጉን

ዛሬ ዛሬ በቁጥር በርከት ያሉ ወጣት ዘማርያን በተሰጣቸው ጸጋ ምእመናንን በማገልገል ላይ እንዳሉ ይታወቃል:: በአንጻሩ ግን የ<መዝሙራቸውን> ዜማ ከዘፈን የሚከልሱና የሚወርሱ እንዳሉ ግልጽ እየኾነ መጥቷል:: ይባስ ብሎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በየአውቶቡስ ፌርማታው፣ በየአደባባዩ፣ ሕዝበ ክርስቲያኑ በብዛት በሚገኝባቸው የታላላቅ አድባራትና ገዳማት ክብረ በዓላት ላይ ጭምር የድምፅ ማጉያዎችን በማጓጓዝ እንደ መልካም ነገር እያስተዋወቁ በማወክ ላይ ናቸው:: ምናለ÷ ምእመኑን ባይረብሹት፣ ቤተ ክርስቲያናችንንስ የማንም መዘባበቻ ባያደርጓት? የእግዚአብሔር ቃልስ መሸቀጫና ሀብት ማካበቻ መሆን ይገባዋልን? ኋላ የማንወጣው ችግር ውስጥ እንዳንገባ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ከወዲሁ ቢመክሩበት ይበጃል እላለሁ::

እስክንድር መስፍን
አ.አ

## ከነገሩ አነጋገሩ
## «እግዚአብሔር የሚደሰተው በዘፈን ወይስ በመዝሙር?»

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን ዘፈንና ዘፋኝነት የተገለጠ የሥጋ ሥራ ነው:: ገላ.5÷21:: ኅዳር 14 ቀን 1998 ዓ.ም በተላለፈልን የአሜሪካን ድምፅ ሬድዮ ፕሮግራም ግን «አባ» ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ይህን ቃል ተጻረዋል:: «... *ዘፈን ዐይነት አለው እንጂ የተወደደ ነው:: ሕዝቡም ይህን ማወቅ አለበት:: ዘፈን ግጥሙ /ስንኞቹ/ ሰውን ወደ ክፉ ነገር የሚገፋፋ እስካልሆነ ድረስ በዜማው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም:: በዚህ ዓለም ያለ ማንኛውም ዜማ ከሦስቱ የቅዱስ ያሬድ ዜማዎች የተገኘ ነው:: ትልቁ የሰዎች ስሕተት ይህን አለማወቃቸው ነው::*» ብለው መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞንንና መዝሙረ ዳዊትን ለውስጣዊ የዘፈን ፍላጎታቸው ማጣቀሻ አድርገውታል:: ይባስ ብለው ዘፋኞችን «ሲመርቁ» እንዲህ ነበር ያሉት:- *እናንተም መልካሙን ዘፈን በመዝፈን፣ ሰውንም እግዚአብሔርንም ለማስደሰት ያብቃችሁ*

ሁሉን ወውና እግዚአብሔር የሚደሰተው በዘፈን ወይስ በመዝሙር? «ቅዱስ ያሬድን እናስታውስ» ብለው ለተነሣሡት አርቲስቶችስ እንዲህ ነው ሊነገር የሚገባው? «ከነገሩ አነጋገሩ» እንዲሉ የሰውዬው ሁኔታ በሬድዮ ጣቢያው ሠራተኞች ዘንድ ሳይቀር ትዝብት ላይ ሳይጥላቸው የቀረ አይመስለኝም:: አሁን የእኔ ስጋት ሰውዬው እንደ ለመደባቸው ዓለም የሰማውን «ክመ ረቃችወኑ» «ዳኅፀ ልሳን ነው» እንዳይሉ ነው:: ጥሩው ነገር÷ «ሰው ዬው ለይቶላቸዋል::» ይህንንም በቅርቡ ከስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ተረድተናል:: ስለሆነም ከዚህ በኋላ «አባ» ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ስለ ምንም ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን አፈ ጉባኤ ሊኾኑ እንደ ማይችሉ መገንዘብ የሚገባቸው ይመስለኛል::

[ዳንኤል፣ዮሐንስ /አ.አ፣ማይጨው]

## ሦስት መጻሕፍት በገበየ ላይ

### የናግራን ሰማዕታት

- በ6ኛው መ/ክ/ዘ በዛሬዋ የመን ናግራን የተባለችው ከተማ የነበሩት ክርስቲያኖች ስለ ሃይማኖታቸው የከፈሉት መሥዋዕትነት
- የዐፄ ካሌብን አስደናቂ ዘመቻ እና የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት የሚያሳይ ጥንታዊ መጽሐፍ

- አዘጋጅ - ዲ/ን ዳንኤል ክብረት
- አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን
- ዋጋ ብር 6.00

### በበረሐው ጉያ ውስጥ

ከ3ኛው - 5ኛ መ/ክ/ዘ በግብጽ በረሃዎች በምናኔ የነበሩ አበው እና እማት ሕይወት፣ ምክርና ትምህርት

- አባባሎች
- ታሪኩች
- ምክሮች
- የኑሮ መፍትሔዎች
- ከሰይጣን ጋር የመዋጊያ ስልቶች የቀረቡበት ለሕይወት መመሪያ የሚሆን መጽሐፍ

አዘጋጅ - ዲ/ን ዳንኤል ክብረት
አሳታሚ - ማኅበረ ቅዱሳን
ዋጋ ብር 10.00

### መንፈሳዊ ሕይወት ምንድን ነው

ታላቁ አባት ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ የጻፈውና የሙሴን ሕይወት መሠረት በማድረግ የሰበከው

- የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃዎች
- ፍጹምነት
- ተጋድሎ
- ፈተናዎች፣ ወዘተ በተመለተ ያስተማረበት መጽሐፍ

አዘጋጅ - ዲ/ን ዳንኤል ክብረት
አሳታሚ - ማኅበረ ቅዱሳን
ዋጋ ብር 8.00

## የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 8 ዶላር | 36 ዶላር |

ለማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት የባንክ ሂሣብ ቁጥር ፬164 ሥላሴ ቅርንጫፍ
Mahibere kidusan Lemate Tequamat
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን
ወይም በ E-mail Mk_ distribution @ Yahoo.com

እስልምና ሰላም ከፍተኛ ዋጋ እንደሚሰጥ «ፍቅር» የእምነቱ መሠረት እንደ ሆነ መምህራኑ ያስተምራሉ:: «ያለ ሕግ አግባብ ሰውን መግደል፣ አንድን ነፍስ ማጥፋት፣ የሰውን ልጅ በአጠቃላይ እንደ ማጥፋት ነው» ይላሉ:: የእምነት፣ የሐሳብ ነጻነት እንዲሁም ሰብአዊ ክብር የእምነቱ መሠረታዊ መብቶች እንደሆኑ መምህራኑ ያስረዳሉ:: ይህ መሠረታዊ መርሕና ትምህርት ያለው እምነት ተከታዮች የሌሎችን እምነት በማቃለልና በማጥቃት እንዲህ ዐይነቱን ሥቃይና መከራ ያደርሳሉ ብሎ መቀበል ያስቸግራል::

የጥቃቱ መንሥኤ በግለሰቦች የዕለት ግጭት ወይም በአለመስማማት የተፈጠረ ነው ማለትም ስሕተት ነው:: ሕዝብን የመምራትና የማስተዳደር ሐላፊነት ያለበት መንግሥት ጉዳዩን በጥንቃቄ ሊከታተለውና መፍትሔ ሊፈልግለት ይገባል::

«በአክራሪነት» ሽፋን እስልምናን የእኩይ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ ያደረጉ ክፍሎች ካሉ ትኩረት ተሰጥቶት መመርመር ያለበት ጉዳይ ነው:: የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ እስከ ሀገረ ስብከት፣ ወረዳ ቤተ ክህነት እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ድረስ ከፍተኛ ሥራ ይጠበቅባቸዋል::

/የማኅበሩ መልእክት/

*የጌታ ጥምቀት በየዓመቱ የሚከበረው የአዲስ ሕይወትና ልደት መሠረት በመሆኑ ነው::*
*ሕይወትነቱንና ብርሃንነቱን ለተቀበሉ ሁሉ ዘወትር አዲስ ስለሆነ ነው::*
*የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ይህን የምትፈጽመው ጌታችን ለእኛ ብሎ ያደረገውን ትሕትና ለመመስከር፣ ለምእመናን የጌታን በረከተ ጥምቀት ለማሳተፍ እንጂ የተጠመቁትን ምእመናን እየመላለሰች በየዓመቱ ስታጠምቅም::*
*ጥምቀት አሐቲ መሆኗን ታውቃለችና::*
*እርግጥ ያልተጠመቁ ኢአማንያን ሲኖሩም የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ጊዜ እየመጡ በክርስቶስ አምነው ሥርዐቱ ተፈጽሞላቸው ይጠመቃሉ::*

/ከሰሞኑ በረከት/

ሐመር
፲፬ኛ ዓመት ቁጥር ፩
ጥር/ የካቲት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

# ይዘት

የማኅበሩ መልእክት
• ሁሉንም የሚመለከት ሃይማኖታዊና አገራዊ ሐላፊነት ........ ፪

ደብዳቤዎች ........ ፬

ከሰሞኑ በረከት
• የጥምቀት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ........ ፰

ወቅታዊ ጉዳዮች
• በታሪክ ጥናት ትልቁ ወንጀል........ ፲፯

ትምህርተ ሃይማኖት
• ቅድስና እና ፈለገ ቅዱሳን........ ፳፬
• ሰባቱ ኪዳናት........ ፳፯

ኪነ ጥበብ
• ደባ ቴአትር ሲቃኝ ........ ፳፱

እናስተዋውቃችሁ
• አቡነ ዮሐንስ እና ከሣቴ ብርሃን ........ ፴፪

ሐመረ ሕይወት
• መንፈሳዊ የምክር አገልግሎት ለጠባይ ለውጥ.. ፴፬

ክርስትና በማኅበራዊ
• መርሳት ........ ፴፰

ዋና አዘጋጅ - ዲያቆን ዳንኤል ክብረት
ም/ዋና አዘጋጅ- አሉላ ጥላሁን

ሪፖርተር - ዲያቆን ደረጀ ጅማ

ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊ - ፍቅርተ ኃይሌ
- ጸዳሉ ሁንዴሳ
- ገነት ግርማ
E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
ስልክ 011-1225729
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

«ማኅበረ ቅዱሳን»
እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል::

*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅትማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::*
*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓት እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::*

# የማኅበሩ መልእክት

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።*

## ሁሉንም የሚመለከት ሃይማኖታዊና አገራዊ ሐላፊነት

ባሳለፍነው ወር ኅዳር 7 እና 8 ቀን 1998 ዓ.ም በአርሲ ሀገረ ስብከት ኮፈሌ ወረዳ ውስጥ የብዙዎችን ልብ በሐዘን የነካ ድርጊት ተፈጽሟል። ይኸውም በኮፈሌ ወረዳ ቆሬ ልዩ ስሙ አንሻ ተብሎ በሚጠራው ቀበሌ የአካባቢው ነዋሪዎች የሆኑ «ወጣት አክራሪ ሙስሊሞች» ይሏቸዋል፤ በ1916 ዓ.ም የተተከለችውን አንሻ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ አቃጥለዋል። ንዋያተ ቅድሳቷን አውድመዋል።

ሰብአዊነት በጐደለው ሁኔታ በቆሬ ስድስት ምእመናን ተገድለዋል። የሰባ ሁለት ክርስቲያን አባወራዎች መኖሪያ ቤቶች እየተመረጡ ተቃጥለዋል። ንብረታቸው ተዘርፏል። ከሙስሊም ጐረቤቶቻቸውና የአካባቢው ኅብረተሰብ ጋር ለዘመናት በመተሳሰብ፣ በመከባበር፣ በመደጋገፍና በመልካም ግንኙነት ከኖሩት ክርስቲያኖች መካከል፤ በተፈጸመባቸው ግድያና ድብደባ፣ በደረሰባቸው መከራ የተነሣ፤ ተወልደው ያደጉበትን፣ ለወግ መዓርግ የበቁበትን፣ እትብታቸው የተቀበረበትን ቀዬ ጥለው ለመሔድ የተገደዱ አሉ። ክርስቲያኖቹ የወደፊት ኑሯቸውንና ህልውናቸውን በማሰብ በከፍተኛ ሐዘንና ስጋት ውስጥ ናቸው።

ከመተዳደሪያ ሥራቸው፣ ከቤት ንብረታቸው ተለይተው ያሉት ክርስቲያኖች የምግብና አልባሳት ጊዜያዊ ርዳታ እየተደረገላቸው ይገኛሉ። ሆኖም የእነዚህ ክርስቲያኖች የወደፊት ዕጣ ፈንታስ? በዚህ ዐይነት በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ጥቃትና ግፍ ዛሬ የመጀመሪያው አይ ደለም። በጥቂት ግለሰቦች የዕለት ግጭት ምክንያት ወይም በአጋጣሚ የተከሠተ ነው ለማለትም ያስቸግራል።

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለያየ ዘር፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነት ወዘተ ይዞ በመከባበርና በመተሳሰብ ኖሯል። አሁንም ይህ መቻቻል በፍቅርና በስምምነት መቀጠል አለበት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለያየ እምነት ሆኖም በመከባበርና በመተሳሰብ የኖረውን ያህል በእምነት ልዩነት ሳቢያ ለግጭት ለጦርነት መዳረጉን ማስታወስም ተገቢ ነው። ዮዲት ጉዲት ያስነሣችው ጦርነት፣ የአሕመድ ግራኝ ወረራ፣ በሱስንዮስ ዘመን በካቶሊኮች ምክንያት የተነሣው ብጥብጥ እጅግ ከፍተኛ ጉዳት አስከትለዋል። ይህንም ማስታወስ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያዊ የሆኑ ዜጎች ሁሉ የመኖር፣ የማሰብ የአመለካከት ነጻነት፣ የመረጡትን እምነት በግላቸው የመከተል መብት እንዳላቸው በሕገ መንግሥቱ ተደንግጎ ተቀምጧል። የተለያየ አመለካከት ይዞ፣ በተለያየ እምነት ውስጥ ሆኖ በመቀራረብ፣ በመተሳሰብና በመከባበር ለመኖር ደግሞ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ኢትዮጵያውያን ለዘመናት የዘለቁበት ስለሆነ እንግዳ ነገር አይደለም።

በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን /615 ዓ.ም/ ቀረይሾች / የመካ ነዋሪዎች/ መሐመድንና ተከታዮቹን ማሳደድ በጀመሩ ጊዜ፤ «ወደ ሐበሻ አገር ብትሔዱ በሥሩ ማንንም የማይበድል ንጉሥ ታገኛላችሁ። ያም/ሀገር/ የፍርድ ሀገር ነው። አላህም በዚያ ለእናንተ ዕረፍትን ይሰጣችኋል» (Ibn Hisham, i, 343) በማለት ተከታዮቹን ልኳቸዋል። በዚህ መሠረት የመጀመሪያዎቹ ሙስሊም ስደተኞች ገብተው እንግዳ ተቀባይ የሆኑት ኢትዮጵያውያንም በወቅቱ ከአሳዳጆቻቸው ታድገዋቸው ፈቅደው በሰላምና በፍቅር ተቀብለዋቸው ኖረዋል።

ጣዖት አምላኪዎቹ ቀረይሾች የስደተኞቹን በሰላም መኖር ሰምተው ለኢትዮጵያው ንጉሥ አሳልፎ እንዲሰጣቸው መልእክተኛ ቢልኩም ስደተኞቹን ለጠላቶቻቸው አሳልፎ አልሰጣቸውም። እዚሁ በሰላም እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። /ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ፤ እስልምናና የታላቁ ነቢይ የሙሐመድ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 1995።/እንዲሁም በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በሁለተኛው ዙር ሙስሊም ስደተኞች መጥተው ኢትዮጵያውያን ተቀብለዋቸው በሰላም ኖረዋል።

ይህ ሆኖ ሳለ ሕዝቦቿ በሰላምና በመከባበር አብሮ በመኖር በሚታወቁባት ኢትዮጵያ በክርስቲያኖች ላይ በተደጋጋሚ እየደረሰ ያለው ጥቃት ምን ያመለክታል? በቀላሉ ችላ ተብሎ መታለፍ ያለበትስ ጉዳይ ይሆን?

እስልምና ለሰላም ከፍተኛ ዋጋ እንደሚሰጥ «ፍቅር» የእምነቱ መሠረት እንደሆነ መምህራኑ ያስተምራሉ። «ያለ ሕግ አግባብ ሰውን መግደል፣ አንድን ነፍስ ማጥፋት፤ የሰውን ልጅ በአጠቃላይ እንደ ማጥፋት ነው» ይላሉ። የእምነት፣ የሐሳብ ነጻነት እንዲሁም ሰብአዊ ክብር የእምነቱ መሠረታዊ መብቶች እንደሆኑ መምህራኑ ያስረዳሉ። ይህ መሠረታዊ መርሕና ትምህርት ያለው እምነት ተከታዮች የሌሎችን እምነት በማቃለልና በማጥቃት እንዲህ ዓይነቱን ሥቃይና መከራ ያደርሳሉ ብሎ መቀበል ያስቸግራል። የጥቃቱን መንሥኤ የግለሰቦች የዕለት ግጭት ወይም አለመስማማት የተፈጠረ ነው ማለትም ስሕተት ነው።

ሕዝብን የመምራትና የማስተዳደር ሐላፊነት ያለበት መንግሥት ጉዳዩን በጥንቃቄ ሊከታተለውና መፍትሔ ሊፈልግለት ይገባል። «በአክራሪነት» ሽፋን እስልምናን የእኩይ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ ያደረጉ ክፍሎች ካሉ ትኩረት ተሰጥቶት መመርመር ያለበት ጉዳይ ነው።

ቤተሰቦቻቸው በዚህ ጥቃት የሞቱባቸው፣ ሥቃይና መከራ የደረሰባቸው ወገኖቻችን፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ «ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፤ ያጸናችሁማል፣ ያበረታችሁማል።» [1ጴጥ.5፥10] እንዳለ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ሊጽናኑ ይገባል።

የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ እህጉረ ስብከት፣ ወረዳ አብያተ ክህነት እስከ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ ከፍተኛ ሥራ ይጠበቅባቸዋል። ጉዳዩ በሚመለከተው የመንግሥት አካል በሕግ አግባብ መፍትሔ እንዲያገኝ በቅርብ መከታተል አለባቸው። ከዚህ በላይ ግን የክርስቲያኑና ሙስሊም ወገኖቻችን ሲያደርጉት እንደ ኖሩት ሁሉ በመከባበርና በመተሳሰብ በበለጠ ተቀራርበው እንዲኖሩ የሁለቱ ሃይማኖት መሪዎች ተገናኝተው መወያየታቸው አስፈላጊ ነው። በቦታው ድረስ በመሔድ ሕዝቡን ማጽናናት መምከር ያስፈልጋል። ሕዝቡን ስለ እምነቱ በሚገባ እንዲያውቅ፣ በእምነት ሽፋን እኵይ ዓላማቸውን ለማስፈጸም የሚጥሩ ካሉ ለእነሱ መጠቀሚያ እንዳይሆን ማስገንዘብ የሁሉም ቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት። በዚህም ቤተ ክርስቲያንን እና ምእመናንን ከጥቃት፣ ሀገርንም ከአስከፊ ብጥብጥ አስቀድሞ ማዳንና መጠበቅ ይቻላል። ይህን ማስፈጸም ሁላችንንም የሚመለከትና የሁላችንም ሃይማኖታዊና አገራዊ ሐላፊነትና ግዴታ ነው።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## «ፖለቲከኛ መኾን ማለት.....»

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትም «መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ» በሚል ርእስ በስፋት ያነበብኳቸው ጽሑፎችና ቃለ ምልልሶች በሚገባኝ መልኩ ተብራርተው የቀረቡ ናቸው:: በእኔ በኩል የተጻፈውን ነገር ሚኒስትሩ ተናግረውታል ብዬ ለመቀበል ይከብደኛል:: ይሁንና እንዲህ ያሉ ግልጽ ውይይቶች ለሌሎችም ችግሮቻችን ሁነኛ መፍትሔዎች ይሆናሉ:: በወቅቱ ሚኒስትሩ ተናገሩት የተባለው ነገር በምእመናን ላይ የፈጠረው ስሜት ጥሩ አልነበረም:: ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል ምስጋና ይግባው:: እንደ አጠቃላይ ግን መንግሥት ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ሥርዐት እንዳይናጋ መጠበቅ ይገባዋል:: ፖለቲከኛ መኾን ማለት እምነት የለሽ መኾን አይመስለኝም:: ክቡር ሚኒስትሩ ለቀሪ ጥያቄዎቻችሁ ምላሽ እንደ ማይነፍጓችሁ ተስፋ አደርጋለሁ:: በመጨረሻም ፍቅረ ሥላሴ አርአያ ባቀረቡት አስተያየት መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን መልስ መስጠት ይኖርባታል እላለሁ::

ንጉሤ ገብረ ሚካኤል
ማታዶር አዲስ ጎማ ፋብሪካ
ኪዳነ ማርያም
ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል
ቤተ ክርስቲያን

## «መነታረክና መወቃቀስ አይጠቅመንም»

ሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትም «መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ» በሚል ርእስ ምእመናንን እንድናስተምር መንገድ የከፈተልን አምላክ የተመሰገነ ይሁን:: እኔ ግን በበኩሌ የምለውን ልበል:: ስለ ቀድሞው ነገር እያነሣን መነታረኩና መወቃቀሱ አይጠቅመንም:: ከዚህ በፊት ኢትዮጵያም ኾነች ሌሎች አገሮች ሠናይም ኾነ እኩይ ታሪክ አላቸው:: ይህም ለዚህ ትውልድ የተሰወረ አይደለም:: ለመኾኑ እኛ በዚያ ዘመን ብንኖር ኖሮ የየትኛው ታሪክ አካል እንኾን ነበር? ራሳችንን መጠየቅ የሚያስፈልገን ይመስለኛል:: ይህ ግን በፊንታው ቤተ ክርስቲያንን የሚያስወቅስ አይደለም:: ... ያለፈውን መጥፎ ታሪክ ለማደስ:- ሕዝብ፣ መንግሥትና የእምነት ተቋማት በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ ተደጋግፈው መነሣት አለባቸው::

ዛሬ የአንዱን እምነት ደግፎ የሌላውን ነቅፎ እንደ መንግሥትም ይሁን እንደ ሕዝብ መቀጠል አይቻልም:: ባለፈ መጥፎ ታሪክ ደግሞ ለዚህ ትውልድ ሌላ ጠባሳ እንዳንተው መጠንቀቅ ይገባናል:: ቤተ ክርስቲያናችንም ራስዋን ችላ በነጻነት ልትንቀሳቀስ ይገባታል:: ስለ ቆሙትም ይሁን ስለ ሞቱት አቋሟ ግልጽ መኾን አለበት:: ፈተና ከየትኛውም አቅጣጫ ቢመጣ መጠንከር ይኖርብናል:: በአጠቃላይ ስለ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተዐቅቦ ግንኙነት ወይም አንድነት መነጋገር ያስፈልገናል:: በተካሄደው ውይይት ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ጉዳይ መሆኗ ለመልካም ነው:: እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ::

መ/ር ሙሉታ ዘቀይ
አሰላ

## ከትላንት ብንዘገይም ዛሬ አልመሽብንም

በኅዳር /ታኅሣሥ 1998 ዓ.ም የሐመር መጽሔት እትም በተላለፈው የማኅበሩ መልእክት ከግንቦት- 97 ዓ.ም ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ጋር ተያይዞ በተፈጠረው ችግር የሰው ሕይወት ሲያልፍና ንብረት ሲወድም ቤተ ክርስቲያናችን የሚጠበቅባትን አለመወጣቷ የሕዝበ ክርስቲያኑ ጥያቄ ነበር:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሰላም፣ ዕድገትና ብልጽግና የበኩሏን አስተዋፅኦ ስታደርግ ቆይታለች:: የፖለቲካ ቡድኖች በራሳቸው ሊፈቱት ያልቻሉት ችግርና አለመግባባት ሲፈጠርም ደግሞ የእርስዋ የተማኅፅኖና የሽምግልና ጥሪ የሚጠበቅ ነበር:: አሁን ባለው ሁኔታ ግን የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ተረካቢ የሚኾነው ወጣቱ ትውልድ አባቶቹን የማያከብር፣ ቤተ ክርስቲያኑን የሚጠላ እንዳይሆን ስጋቴ ነው::

በዛሬዋ ዓለማችን የእምነት ተቋማት ድርሻ ዘርፈ ብዙ ሆኗል:: ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያናችን በአገራችን ልማትና ዕድገት እንዲመጣ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን ዘርግታ እየሠራች ያለችው:: ይሁን እንጂ ይአገር ሰላም ሲናጋ፣ ወንድማማቾች ሲጋደሉና ሲጨካከኑ እያየች ዝምታን መምረጥ የለባትም:: በመጨረሻም:- ፍቅር ከሁሉም በላይ ነው:: ቤተ ክርስቲያንም የምታስተምረን ይህንኑ ነው:: ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶሳችን በተለይም በዕውቀትም በሐላፊነትም በከፍተኛ ደረጃ ካሉት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርካችን ብዙ እንጠብቃለን:: የሰላም በር ሁል ጊዜ ክፍት ነው:: የሰላም ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ብናንኳኳ ይከፍትልናልና እንበርታ:: ከትላንት ብንዘገይም ዛሬ አልመሸብንም::

ገብረ ኢየሱስ
ሰሜን አሜሪካ

## «ሐመር ፖለቲካ ውስጥ ገብታለች»

የሐመር መጽሔት የ14 ዓመት ደንበኛ ነኝ:: ከደንበኝነትም አልፎ መጽሔት በማሰራጨት ረገድ የማገለግልበት ተሳትፎ አለኝ:: የሐመር መጽሔት በ14 ዓመታት ጉዞዋ ለምእመናን ያበረከተችው አስተዋፅኦ ወደር አልነበረውም:: ሌላው ቀርቶ መጽሔቷን ለትውልድ የሚያልፍ ቅርስ አድርገው የሚገዙ ደንበኞች አሉ:: የኅዳር/ታኅ ሥ 1998 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም ግን ለነቀፌታ ዳርጋናለች:: «መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ» የሚለውን ጽሑፍ ገለጥ አድርገው የተመለከቱ ሁሉ:- «ማኅበረ ቅዱሳን ፖለቲካ ውስጥ ገባ እንዴ!» በማለት ጠይቀዋል:: በማየት ብቻ «እንገዛም» ያሉም አጋጥመውኛል:: ኪሳራውን ትከፍሉኛላችሁ:: በበኩሌ ጽሑፉን ሦስቴ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ:: ጊዜው ግን አልነበረም:: ለመኾኑ ከሚኒስትሩ ጋር የተደረገው ቃለ ምልልስ ለእኛ ምን አስተማረን:: ደግሞ'ኮ የሚገርመው ሊቀጥል ሁሉ ይችላል!! «ሐመር ፖለቲካ ውስጥ ገብታለች» የማይሉ'ኮ የሉም:: የሥነ ጽሑፍ ሰው ባልኾንም ሐመርን ግን እንደ ተልእኮዋ አድርጓት:: ጨርሻለሁ::

መ/ር ጌታሁን ዐሥራት
ዱብቲ

## «ነጻነታቸውን ጠብቀው ሕዝብን ማገልገል ከሁለቱም ይፈለጋል»

ሃይማኖትና መንግሥት ሊደጋገፉ የሚገባቸው ማኅበራዊ ተቋማት /Social institutions/ ናቸው:: በሥነ ማኅበረሰብ ትምህርት /Sociology/:- ቤተሰብ፣ የትምህርት ተቋም፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የምጣኔ ሀብት ተቋምና የፖለቲካ ተቋም በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ መሠረታዊ የማኅበረሰብ መገለጫዎች ናቸው:: እያንዳንዳቸው ሚናቸውን በመጫወት ማኅበረሰቡን ያቆማሉ፤ ያጸናሉ:: አንዱ ብቻውን ሳይሆን ከሌላው ጋር በመኾን በትስስር ይኖራሉ:: ከዚህ አንጻር መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ ሃይማኖትም እንደዚሁ .... ቢባልም ቅሉ ነጻነታቸውን ጠብቀው ሕዝብን ማገልገል ከሁለቱም ይጠበቃል:: ከዚህ አንጻር አንዱ በሌላው ላይ የሚሰነዝረው ወደ ነቀፌታ ብቻ ያደላ ትችት ሚዛናዊነት ጎድሎት ወደ ማኅበረሰባዊ ቀውስ እንዳይወስድ ያሰጋል:: ተቋማቱ ለሚያደርጉት ማንኛውም እንቅስቃሴ የግለሰቦች ሚና ወሳኝነት አለው:: የሚወክሉትን አካል ዓላማ በትክክልና በአግባቡ ማንጸባረቅ የግለሰቦች ሐላፊነት ነው:: በግለሰቦች ሕይወት ውስጥ የተቋማትንና የግልን ሚና መለየት ፈታኝ ነው:: የሚና ግጭት /Role conflict/ የሚከሠተው ከዚህ አንጻር ነው:: ዛሬ በእምነትም ይሁን በፖለቲካ ተቋማት÷ በግለሰቦች ላይ የምናስተውላቸው እንከኖች በዚህ ምክንያት ይሆንን? የሚል ጥያቄ አለኝ::

ዲ/ን ዜና ብርሃኑ
አ.አ.ዩ





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# የጥምቀት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ

## *«ይህ ዓይነት አከባበር ሊታይ የቻለው ሕዝቡ በፈቃዱ ያመጣው ጥምቀት፣ በተሰፋው ፍጻሜ የተቀበለው ክርስትና ስለሆነ ነው።»*

*/ዘማርያም ኤፍሬም እና በእደ ማርያም ዳንኤል/*

### *«ውኃ ለመዓት ውኃ ለምሕረት»*

እንደ ጎርጎሮሳውያን ዘመን አቆጣጠር ዲሴምበር 15 ቀን 2004 ዓ.ም። በረዷማውንና ቀዝቃዛውን የምዕራብ ዓለም የአየር ሁኔታና የገናን ሰሞን የዕረፍት ጊዜ ለማሳለፍ ከልዩ ልዩ አገሮች የመጡ ቱሪስቶች ናቸው። በደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች የሕንድ ውቅያኖስ የመዝናኛ ዳርቻዎች ላይ ይታያሉ። በኢንዶኔዥያ- አቼ ግዛት ከሚገኘው የሕንድ ውቅያኖስ የባሕር ወለል በሬክተር ስኬል ከ9.2-9.3 የሚደርስ የከርሠ ውኃ ነውጥ ተፈጥሯል። ነውጡ የባሕሩን ውኃ ቀስቅሶ ማዕበሉን በ10 ሜትር ከፍታ እያጓነ በመምዘግዘግ ላይ ነው። ቱሪስቶቹ ይህ ኀያል ማዕበል ሊ ያጥለቀልቃቸው እየገሠገሠ ስለ መሆኑ ጥርጣሬው እንኳ አልነበራቸውም። የርዕደ መሬት ማእከል ወይም የመሬት ነውጥ መናኸርያ ከሚባለው አካባቢ ተነሥቶ ለ10 ደቂቃ ብቻ የቆየው ይኸው የከርሠ ውኃ ነውጥ /በጃፓንኛ ቋንቋ ሱናሚ/ 13 የሕንድ ውቅያኖስና ከአራት ያላነሱ የምሥራቅ አፍሪካ አገሮችን አጥቅቶ 300,000 ያህል ሰዎችን ሰለባ አድርጓል። ሚልዮኖችን አፈናቅሎ ለከፍተኛ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ዳርጓቸዋል። ብዙዎች ክሥተቱን «የደቡብ እስያ የጥፋት ውኃ» ብለውታል።

ከአዳም ዐሥር ትውልድ በኋላ በምድር ላይ የአስረሽ ምችው ሕይወት ሲመሩ የነበሩ ሰብአ ትካት /የቀደሙ ሰዎች/ በማየ አይኅ፣ ማየ ድምሳሴ፣ ማየ ስራዌ /የጥፋት ውኃ/ ጠፍተዋል። ዘፍጥ.7። በኋላ ዘመንም ግራና ቀኝ ተከፍሎ እስራኤል ዘሥጋ በሊቀ ነቢያት ሙሴ መሪነት በደረቅ /በየብስ/ የተሻገሩበት የኤርትራ ባሕር በፈርዖንና በሠራዊቱ ላይ ተመልሶባቸዋል። ዘጸ.14 ÷28። ከዚያ ወዲህ «ውኃ ለመዓት እንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም» የሚል እምነት ሰፍኗል።/ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ ምዕ.3 ቁ.17/።

እግዚአብሔር ግን ምድርን ዳግመኛ በውኃ እንዳያጠፋ ተስፋ ሰጥቶ ከኖኅና ከሕያው ፍጥረታት ሁሉ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶ ነበር። /ዘፍ.8÷21፤22፤9÷8-17/። በጥንተ ፍጥረት ቅሉ የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር። /ዘፍጥ.1÷2/። ውኃ የዓለም ሥነ ፍጥረት ሁሉ ከሚንቀሳቀስባቸው አራቱ ባሕርያት አንዱ ነው። ሕይወታውያን ፍጥረቶች ሁሉ ያለ ውኃ መኖር አይችሉም። ለሕይወት ጠቀሜታ በሚሰጡና ከሕይወት ጋር ተዛምደው በሚኖሩ ነገሮች ሰውን መርዳት ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ረቂቅ ጥበብና ፈቃድ ነው። ወልደ እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የመጣ እንደ መኾኑ መጠን ሰው የወደቀበትን ቦታ ሁሉ አስሶታል። እግዚ አብሔር የሰውን ልጅ በውኃ ውስጥ ፈልጎታል። ፈልጎም አላጣው አግኝቶታል። ይኸውም በጥምቀተ ክርስቶስ ተፈጽሟል።



*«ኢየሱስ ዮሐንስን ውኃው በሰማያዊ ቡራኬ ይቀደስ ዘንድ አጥምቀኝ አለው»*

ውኃ ለምሕረትም እንደ ተፈጠረ ለማጠየቅ ጌታችን ጥምቀቱን በውኃ አደረገ። /ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ ምዕ.3ቁ.17/። ይህን ለመመስከርና ለማስተማር በየዓመቱ በውኃ አካላት ዳርቻዎችና በሜዳዎች የጥምቀትን በዓል እናከብራለን። ወቅቱ ሥነ በዓሉን ለመመልከት በርካታ ቱሪስቶች ከዓለም ዙርያ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡበት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በ5531 ዓመተ ዓለም፣ ዘመነ ሉቃስ፣ ማክሰኞ ዕለት፣ ጥር 11 ቀን ከሌሊቱ በ10ኛው ሰዓት ነበር። /ፍት. ነገ. አን. 19 ድስቅ 29፤ ተረፈ ቄርሎስ/።

ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ የዮርዳኖስ ወንዝ ወደፊት መፍሰሱን ትቶ ሸሽቶ ወደ ኋላው ተመልሶአል። «እንደ ገና በቃሉ ተመልሷል» ይባላል። ይህም ክርስቶስ በሥነ ፍጥረታት ሁሉ ላይ ኃይልና ሥልጣን እንዳለው፣ ፍጥረታት እንደ ሚፈሩትና እንደ ሚገዙለት ያሳያል። ቅዱስ ቄርሎስም ጌታችን በተጠመቀ ጊዜ «ውኆች እንደ ሞቀ ውኃ ፈሉ» ይላል። ይህ አስደናቂ ሥራ በአንድ በኩል የክርስቶስን መለኮታዊ ኃይል ሲያመለክት በሌላ በኩል ደግሞ በምሥጢረ ሥላሴና ምሥጢረ ሥጋዌ አምኖ የተጠመቀ ሁሉ ሙቀት መንፈስ ቅዱስን እንደ ሚያገኝ ያሳያል። ሌላው ሊቅ ደግሞ «አኮ ዘረከበ ጸጋ በተጠምቆቱ፤ አላ ከመ ያበርህ መካናተ ወያኀይል ማያተ ለእለ ህለዎሙ ይጠመቁ ውስቴታ፤ ዮርዳኖስን ብርሀት ለማድረግ ለውኃውም (ለጥምቀትም) ኃይልን ለመስጠት ተጠመቀ እንጂ ለራሱ ረብ ጥቅም ለማግኘት አይደለም።» ብሏል። /ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴ. ም.3ቁ.13/። ቅዱስ ያሬድም ስለዚህ ሲያስረዳ፡- «ይቤሎ ኢየሱስ ለዮሐንስ አጥምቀኒ በማይ ከመ ይትቀደስ ማይ በማዕተበ ሰማይ፤ ኢየሱስ ዮሐንስን ውኃው በሰማያዊ ቡራኬ ይቀደስ ዘንድ አጥምቀኝ አለው።» ሲል ዘምሮአል። /መዝሙር፣ ዮሐንስ አንድዓ/። ጌታችን የተጠመቀው ለእኛ ሥርዐተ ጥምቀትን /ዳግም ልደትን/ ለመሥራት፣ ትሕትናን ለማስተማርና ውኃውን ለመባረክ መሆኑን መረዳት ይገባል።

*ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በጽሑፍ ባቆዩልን ስብከት እንደ ገለጹት፡- «ዮርዳኖስ የሕይወት ውኃ ነው፤ የሕይወት ወንዝ ነው፤ የበረከት በር ነው። ይህን ረስተንና ዘንግተን ወደ ሙት ባሕር እንዳንገባ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ብዙ ሰዎች ዛሬ ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ምድረ ርስት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከገቡ በኋላ እንደገና ወደ ሙት ባሕር እየዘለሉ እየገቡ ነው። ታድያ በሙት ባሕር ሕይወት ስለሌለ እዚያው ቀልጠው ይቀራሉ። ይህም ያሳዝናል፤ የዘላለም ሞት ነውና። »*

ጌታችን ከተጠመቀ በኋላ ከውኃው ወጥቶ ሲጸልይ በኃጢአት ምክንያት በአዳምና በዘሮቹ ላይ የተዘጋው የመንግሥተ ሰማይ በር ተከፍቷል። የአምላኩን ገጽታ አጥቶ በሞት መንገድ ላይ ሲቅበዘበዝ የነበረው የሰው ልጅ የአምላኩን ፊት አይቷል፤ ዐውቋል። በክርስቶስ አምነው የሚጠመቁ ሁሉ የመንግሥተ ሰማያት በር ተከፍቶላቸው የሚገቡ ኾነዋል። «ሰው ከውኃ እና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።» ዮሐ.3÷5። በጥምቀት ከእግዚአብሔር በጸጋ እንወለዳለን። በጥንተ ፍጥረት በውኃ ውስጥ በደመ ነፍስ ሕያዋን የኾኑ ፍጥረታት ተገኝተውበታል። ጥምቀትም ለሁሉ የተሰጠ የሕይወት መሠረት ነው። አምኖ ሊቀበለው የሚሻ ሁሉ ያገኘዋል። ውኃ በዓለም ሁሉ እንዲፈስ ጥምቀትም ለሰው ልጆች ሁሉ ያለ መከልከል ሲሰጥ ይኖራል።



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የጌታችን በዓለ ጥምቀት በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በሦስተኛው ምእት ዓመት መከበር ጀምሮአል:: በመጀመሪያ ከልደት በዓል ጋር በአንድነት ይከበር ነበር:: ዛሬም በኢየሩሳሌም ያለችው የአርመንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልደትንና ጥምቀትን በአንድ ቀን ታከብራለች:: በአራተኛው ምእት ግን ከመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ዐበይት በዓላት /ትንሣኤ፣ በዓለ ኀምሳና ልደት/ ጋር እኩል ኾኖ ለብቻው ጥር 11 ቀን እንዲከበር ተደርጓአል:: በዓለ ጥምቀት በምዕራቡ የክርስትና ዓለም የታወቀው ከአራተኛው ምእት ዓመት ጀምሮ ነው:: የልደት በዓል የዘመን መለወጫ ዕለት ጭምር በመኾኑ ከፍተኛ መሰናዶ ይደረግለታል:: የመልካም ምኞት መግለጫና ልዩ ልዩ የማስታወሻ ስጦታዎች በቤተሰብና ወዳጅ ዘመድ መካከል ይለዋወጡበታል:: የጥምቀት በዓል ግን በመታሰቢያነቱ ብቻ የሚዘከር ነው::

ስለ ጥምቀት በዓል በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተለያየ ትውፊት አለ:: በአንዳንድ አገሮች ምእመናኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይም በውጭ እንደ አየሩ ሁኔታ ተሰብስበው ካህኑ የጌታን ጥምቀት የሚያመለክተውን ጥቅስ ከወንጌል አንብቦ በምእመናኑ ላይ ውኃ በመርጨት በዓሉ ይታሰባል:: ሌሎች ደግሞ ወደ ወንዝ (ባሕር) ወርደው ሻማ አብርተው ሊሠጥም በማይችል ተንሳፋፊ ዕቃ ላይ በመትከል በባሕሩ ይጥሉታል:: ሻማው እስከ ሚያልቅ ድረስ ባሕሩ ላይ እየተንሳፈፈ በነፋስ ኃይል ይጓዛል:: ይህም ብርሃነ ዓለም ክርስቶስ ወደ ጨለማው ዓለም መጥቶ በሞት ጥላ አገር ለነበሩት የሰው ልጆች ብርሃን ትምህርቱን ማብራቱንና የማይታየው አምላክ በሥጋ መገለጡን ነው:: /ት.ኢ ሳ.9÷2፤ ዮሐ.1÷9/:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት፣ <u>በዓለ ልደት ወጥምቀት</u>፣ 1985 ዓ.ም፤ ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ፣ ቁጥር 9፣1987 ዓ.ም/::

በቤተ ክርስቲያን አነጋገር ጥምቀተ ክርስቶስ *«አስተርእዮተ እግዚእ»* ይባላል:: በግሪክ ቋንቋ *«ኤጲፋንያ»* ይሉታል:: መገለጥ፣ መታየት እንደ ማለት ነው:: ይህም ሥግው ቃል ክርስቶስ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በሕዝብ መካከል በግልጥ መታየቱን፤ ዳግመኛም ምሥጢረ ሥላሴ በጥምቀተ ክርስቶስ የጎላ የተረዳ መሆኑን ያጠይቃል:: ማቴ 3÷16-17፤– 1ጢሞ.3÷16:: ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ የጌታን መገለጽ /አስተርእዮን/ *«ምጽአተ ብርሃን»* ይለዋል:: ዮሐ.1÷9:: ቅዱስ ያሬድም «በሠላሳ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ ዘነቢያት ሰብክዎ ወአስተርአየ ገሃደ፤ ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት ጌታ በሠላሳ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ፤ በገሃድም ታየ፤ ተገለጠ» በማለት አመስግኗል:: /መጽሐፈ ድጓ/::

## ዜና ጥምቀት በኢትዮጵያ

ፊትም በሕገ ልቡና በኋላም ሕገ ኦሪትን ተቀብላ ስለ ድኅነተ ዓለም የተነገረውን ትንቢት የተቆጠረውን ሱባዔ ስትጠባበቅ የኖረችው አገራችን ኢትዮጵያ ዜና ጥምቀትን የሰማችው በመንፈስ እግዚአብሔር መሪነትና አስፈጻሚነት የራስዋ ሐዋርያ በጥም ቀት ከመንፈስ ቅዱስ የመወለ ድን ዕድል በማግኘቱ ነው:: ግብ.ሐዋ.8÷29:: የተነገረው ትንቢት፣ የተቆጠረው ሱባዔ እንደ ተፈጸመ ከቅዱስ ፊልጶስ ቃል የተረዳው የንግሥት ሕንደኬ በጅሮንድ አቤላክ-ባ ከስ:- «እነሆ ውኃ አለ፤ ታድያ መጠመቅን ማን ይከለክለኛል?» /ግብ.ሐዋ.8÷36/ ብሎ በፈቃዱ ማመኑንና መጠመቁን ተከትሎ ነው:: ጊዜውም 34 ዓ.ም ነበር:: ጃንደረባው የተጠመቀበት እምነት:- «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ኾነ አምናለሁ» የሚል ነው:: ግብ. ሐዋ.8÷37:: ቀሲስ ከፍ ያለው መራሒ «የቤተ ክርስቲያን አስተዋፅኦ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ» /1986 ዓ.ም/ በተባለ መጽሐፋቸው ላይ ይህን የጃንደረባውን የእምነት ምስክርነት:-

*«የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐዲስ አማንያንን ሲያጠምቁ የሚጠቀሙበት የክርስትና ጥምቀት ፎርሙላ ነው::»* ብለውታል::

ኢትዮጵያችን ለእምነትም ኾነ ለጥምቀት ራሷ በራሷ በየጊዜው ያደረገችው ሐዋርያዊ አገልግሎት ከፍ ያለ ነው:: በንግሥት ሕንደኬ ግምጃ ቤት ሹም /በጅሮንድ/ አንደበት በኢትዮጵያ የተሰማው ዜና ጥምቀት ፍጹም የኾነው /የተስፋፋው/ በነገሥታቱ አብርሃና አጽብሐ (313-351 ዓ.ም) ቤተ መንግሥት በጅሮንድ የነበረው ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ ተልኮ ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስነት ተሾሞ ከተመለሰ በኋላ በ330 ዓ.ም ነው:: ቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በኢትዮጵያ ግዛት በሙሉ የወንጌልን ትምህርት ለማዳረስ የሚረዱትን ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሾሟል:: እነርሱም የክህነት አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ሥርዐተ ጥምቀትን፣ ሥርዓተ ቁርባኑን... እንዲያከናውኑ አድርጓል::

*«በኢትዮጵያ ብቻ ይህ ዐይነት አከባበር ሊታይ የቻለው ሕዝቡ በፈቃዱ ያመጣው ጥምቀት፣ በተስፋው ፍጻሜ የተቀበለው ክርስትና ስለሆነ ነው::*



*የኢትዮጵያ መንግሥት በጅሮንድ በቅዱስ ፊልጶስ እጅ እንደ ተጠመቀ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ::» /ግብ.ሐዋ.8÷37/*



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# በዓለ ጥምቀትና ትውፊቱ በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰው ከቅድስት ሥላሴ ረቂቅ ልደት ሊወለድ የቻለበትን፣ ወደ ክርስቶስ ቤተሰብነትና የክርስቲያን ማኅበር አንድነት ብሎም ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚተላለፍበትን በዓለ ጥምቀትን በየዓመቱ ጥር 11 ቀን የመታሰቢያ በዓል አድርጋ ታከብረዋለች፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በሥዕላዊ መልክ ከምታከብራቸው በርካታ በዓላት መካከል በዓለ ጥምቀት አንዱ ነው፡፡ ሥዕላዊ መልክ ማለት በዓሉን በሜስ መልከት መዝሙር መዘመር፣ ምስጋና ማቅረብ፣ በበዓሉ ዕለት የተፈጸመውን ድርጊት በኅሊና ማሰብ ብቻ አይደለም፡፡ የበዓሉን ጥንታዊ ድርጊት በሚታይ ነገርና ሁኔታ መግለጥ ማለት ነው፡፡ ይህም የረቀቀውን አጉልቶ የራቀውን አቅርቦ ለማሳየት ነው፡፡ የጥንተ ክርስትናውን መሠረት ሳትለቅ ከቀደምት አበው በተላለፈው እምነትና ሥርዓት የምትጓዘው ጥንታዊት፣ ብሔራዊትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ጥምቀት በዓል አከባበር የራሷ ትውፊት አላት፡፡ የብሉያትና ሐዲሳት መጻሕፍት በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥራዝ እንደ ሚገኙ ሁሉ ሥርዐቱንም ባህሉንም አስተባብራ ይዛ የምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት፡፡

የጥምቀት በዓል በሌሎቹ ዘንድ ለመታሰቢያ ያህል በጸሎት እንዲሁም ከላይ እንደ ገለጥነው በልዩ ሥርዐት ይከበራል፡፡ ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የምታከብርበት ትውፊታዊ ሥነ ሥርዐት ዓለምን ወደ አድናቆት ስቦት ይገኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜም የሃይማኖት በዓልነቱን ሳይለቅ ጥንታዊ ታሪኩንም ሳይለውጥ የቱሪስቶችን አትኩሮት በብዛት ሲማርክ ይገኛል፡፡ በ1963 ዓ.ም ስለ ጥምቀት በዓል አከባበር የወጣ መጽሐፍት እንዳተተው፡-

*«በኢትዮጵያ ብቻ ይህ ዓይነት አከባበር ሊታይ የቻለው ሕዝቡ በፈቃዱ ያመጣው ጥምቀት፣ በተስፋው ፍጻሜ የተቀበለው ክርስትና ስለሆነ ነው፡፡ ሕዝቡ ከነገሥታቱ ጋር እንደ መንግሥት በዓል አድርጎ በሰልፍ ያከብረዋል፡፡ ከሌላው ዓለም ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያ ተለይታ በመኖሯ የጥንቱን ሥርዐት ያለ መለወጥ ለመያዝ ችላለች፡፡... ይህም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለጥንታዊነቷና ለከፍተኛ እምነቷ ትልቅ መታወቂያ ምልክት ኾኖ ኖሯል፤ ይኖራልም፡፡»*



*አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ነገሥተ ኢትዮጵያ አብርሃና አጽብሐ /ከግራ ወደ ቀኝ/*

የበዓለ ጥምቀት አከባበር በኢትዮጵያ የተጀመረው የክርስትና እምነት እንደ ገባ መኾኑ ይታመናል፡፡ እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ግን የጥምቀት በዓል አሁን በምናከብርበት ሁኔታ የሚታሰብበት ሥነ ሥርዐት አልነበረም፡፡ በዓለ ጥምቀትን በሜዳና በውኃ አካላት ዳር ማክበር የተጀመረው በዐፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት (530-544 ዓ.ም) እንደ ኾነ ይነገራል፡፡ ይኸውም ከማኅሌታዊው ቅዱስ ያሬድ (505-572 ዓ.ም) ዜማ መስፋፋት ጋር ተያይዞ ታቦታቱ በየዓመቱ ጥር 11 ቀን ጠዋት ወደ ወንዝ ወርደው ማታ ወደ መንበረ ክብራቸው እንዲመለሱ ይደረግ ነበር፡፡ ጻድቁና ጠቢቡ ንጉሥ ላልይበላ (1140-1180 ዓ.ም) ሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለየብቻቸው በሚቀርባቸው ቦታ በተናጠል ሲፈጽሙት የነበረውን ክብረ በዓል አስቀርቷል፡፡ በምትኩም በአንድ አካባቢ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በአንድነት ተሰባስበው በአንድ ጥምቀተ ባሕር እንዲያከብሩ ትእዛዝ አስተላልፏል፡፡ ይህም ተግባራዊ በመኾኑ የበዓሉ አከባበር ሥነ ሥርዐት ቅንጅት እና ድምቀት እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ከዚህም ባሻገር በቅዱስ ላልይበላ ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ ምድር እየተመላለሱ በብሕትውና እና በስብከተ ወንጌል ተግተው ያገለግሉ የነበሩት ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በአክሱም፣ በመቐለና በመርጡለ ማርያም እየተዘዋወሩ ባሕረ ጥምቀቱን ባርከዋል፡፡ በዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት (1260-1275 ዓ.ም) በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት (1203-1304 ዓ.ም) አሳሳቢነት የተጀመረው ሥርዐተ በዓል ተጠናክሮ እንዲቀጥል በዐዋጅ ትእዛዝ አስተላልፈዋል፡፡ ታቦታቱም በሕዝብ ጥበቃና ክብካቤ ተደርጎላቸው በየጥምቀተ ባሕሩ እንዲያድሩ ወስነዋል፡፡ የበዓሉ አከባበር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና አድማሱ ብሔራዊነትን እየያዘ መጣ፡፡

በመንፈሳዊነታቸውና በደራሲነታቸው መጻሕፍትን ጽፈው፣ ሥርዐትን ሠርተው ለቤተ ክርስቲያን ያበረከቱት ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ (1426-1460 ዓ.ም) ታቦታቱ ወደ ወንዝ ወርደው ዕለቱን እንዳይመለሱ፣ በዚያ ፈንታ በጥምቀት ዋዜማ ጥር 10 ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ወርደው እንዲያድሩ፣ አገሩን በኪደተ እግር ይባርኩም ዘንድ በሄዱበት መንገድ እንዳይመለሱ በዐዋጅ ወሰኑ፡፡ ይህን ታሪክ በመከተል ዐፄ ናዖድ (1486-1500 ዓ.ም) ማንኛውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ምእመን ታቦተ ሕጉ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ በሚወርድበት እና ከባሕረ ጥምቀቱ ወደ ቤተ መቅደሱ በሚመለስበት ጊዜ አጅቦ አውርዶ፣ አጅቦ መመለስ እንዳለበት በዐዋጅ አስነግረው ነበር፡፡ ሕዝቡም ታቦታተ ሕጉን በሆታና በእልልታ ከቤተ መቅደስ አጅቦ ከአወጣ በኋላ በባሕረ ጥምቀት ከትሞ ማደር ጀመረ፡፡ ሊቃውንቱም እንዲሁ ለበዓሉ የሚስማማውን ቃለ እግዚአብሔር እያደረሱ ያድሩ ጀመር፡፡

ታቦተ ጽዮን በኢሎፍላውያን ተማርካ፣ የሚያመልኩበትን ጣዖተ ዳጎንን ድል አድርጋ ተኣምር ሠርታለች፡፡ በኋላም በእስራኤላውያን ተመልሳ በአሚናዳብ ቤት ለኻያ ዓመታት ተቀምጣለች፡፡ የአሚናዳብ ቤትም በበረከት ተሞልቶ ነበር፡፡ /1ሳሙ.7÷2/፡፡ ዛሬም ኦርቶዶክሳዊው ምእመን በየአካባቢው ታቦታቱ እንዲያድሩለት የሚፈልገው፣ ታቦታቱ የሚያድሩበትን ድንኳን ከቦ የሚያነጋው ያን በረከት ለማግኘት ነው፡፡

ይኸው ታሪካዊ ሂደት ሳይቋረጥ ቀጥሎ እስከ አሁን ድረስ ፍጹም መንፈሳዊና ትውፊታዊ ይዘቱን ሳይለቅ እየተከበረ ይገኛል፡፡ በበዓሉ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

***ታቦታቱ በጥምቀት ዋዜማ ከመንበራቸው ወደ ጥምቀተ ባሕር መውረዳቸውና በዚያ ማደራቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ከማታው ጀምሮ መውረዱንና ተሰልፎ ተራውን ሲጠብቅ ማደሩን ያጠይቃል።***


አከባበር ሥነ ሥርዓት ላይ የሚዘመረውና የሚነገረው ቃለ እግዚአብሔር በጥምቀት የምናገኘውን ጸጋና በረከት የሚያመሠጥር ነው። የሚከናወነው ሥርዐትም ሃይማኖታዊ ታሪክና ምሳሌ አለው።

ከ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን አንሥቶ ሲያያዝ እንደ መጣው በዓለ ጥምቀት የሚታሰበው ከዋዜማው ጥር 10 ቀን ጀምሮ ነው።

## ሀ/ በዋዜማው ጥር 10 ቀን

በየሰበካው ቦታ ተለይቶና ተከልሎ ታቦታቱ በዳስ ወይም በድንኳን የሚያድሩበት፣ የተለያዩ የውኃ አካላት ተጠርገው የሚከተሩበት ወይም ሰው ሠራሽ የግድብ ውኃ የሚበጅበት ስፍራ ***«ባሕረ ጥምቀት»***፣ ***«የታቦት ማደርያ»*** እየተባለ ይጠራል። ***ባሕር፡-*** የውኃ መሰብሰቢያ (ምእላደ ማይ፣ የውኃ መከማቻ (ምቋመ ማይ) ነው። በሌላ አነጋገር ***«የውኃ አገር»*** /መካነ ማይ፣ ዓለመ ማይ/ ነው። ***ጥምቀት፡-*** ከውኃ መንከር፣ መዝፈቅ፣ ከውኃ ማግባት፣ በውኃ ማጠብ፣ ውኃን በራስ ገላ ላይ ማፍሰስ፣ መቸለስ፣ መርጨት፣ ማረብረብ ሲኾን ***ምጥማቃት*** ሲል ደግሞ መጥመቂያ፣ ማጥመቂያ፣ መጠመቂያ ቦታ ማለት ነው። /ኪ.ወ.ክ÷261 እና 502-503/። በመላው ኢትዮጵያ የታነፁት ከ20,000 በላይ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ጥር 10 ቀን በየአካባቢያቸው በተመደበላቸው አብሕርተ ምጥማቃት /Baptismal Pool, Baptismal Site/ ይወርዳሉ። ካህናቱም ስብሐተ እግዚአብሔር ሲያደርሱ ያድራሉ። በመንፈቀ ሌሊትም ሥርዐተ ቅዳሴው ተጀምሮ ከሌሊቱ በ9:00 ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል።

በአክሱም የንግሥት ሳባ መዋኛን ***«ማይ ሹም»***፣ በጎንደር የዐፄ ፋሲል መዋኛን፣ በላስታ የላሊበላ መዋኛን፣ በሸዋ የዐፄ ዘርዐ



*ማይ ሹም-በአክሱም ማይ ቆይ ኮረብታ ግርጌ የሚገኘውና በዓለ ጥምቀት የሚከበርበት የንግሥት ሳባ መታጠቢያ*

ያዕቆብ ፍርድ መስጫ አደባባይን፣ አርባ አራት ታቦታት የሚያድሩበትን የሸንኮራ ሜዳን ***«ራቡቴ ወንዝ»***፣ በአዲስ አበባ ደግሞ ጃንሆይ ሜዳን ጃንሜዳን ለአብሕርተ ምጥማቃት እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። እኒህ ቦታዎች ዛሬም ድረስ ተከብረው ይገኛሉ።

እንደ ሊቀ ማእምራን ጽጌ ከበረ ገለጻ፡- «የቃል ኪዳኑን ታቦት አክብሮ (ይዞ) መጓዝና ወደ ወንዝ መውረድ የተጀመረው በአሮን ልጅ በአልዓዛር ጊዜ ነው። ኢያሱ በሙሴ እግር ተተክቶ ሕዝበ እስራኤልን እየመራ ከዮርዳኖስ ወንዝ ሲደርስ ባሕሩ ከሁለት ይከፈልና ወራጁም ይቆም ነበር። እስራኤል ዘሥጋ ወደ ምድረ ርስት ለመግባት የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገሩ፡- ድንኳን ጥለው የቃል ኪዳኑን ታቦት በድንኳን ውስጥ አድርገው ሌዋውያኑ በዙሪያው፣ ካህናቱ ደግሞ በውስጥ ኾነው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ አድረው ተሻግረዋል። መጽ.ኢያሱ 3÷8-9።» የጥምቀት ዋዜማ ***ከተራ*** ተብሎ ይጠራል። መምሬ ተዘራ ወርቁና ሊቀ ትጉሃን ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም ስለዚህ ሲያስረዱ፡- «ካህናቱ የቃል ኪዳኑን ታቦት አክብረው (ይዘው) የወንዙን ዳርቻ በረገጡት ጊዜ እንደ ክረምት ማዕበል ይወርድ የነበረው ውኃ ግራና ቀኝ ተከፍሎ እንደ ግድግዳ ወደ ላይ ቆሟል። ሕዝቡ ተሻግሮ እስከሚያበቃም ታቦተ ጽዮንን ያከበሩት /የያዙት/ ካህናት ከወንዙ መሀል ቆመው ነበር። በዚህ መሠረት «ወተጠምቃ እገሪሆሙ ለካህናት» ተብሎ ተጽፎአል። ይህም «የካህናት እግር የዮርዳኖስን ውኃ በመርገጡ እንደ ጥምቀት ሆናቸው» ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያኖችን የጥምቀትን ዋዜማ ከተራ ብላ የጠራችው ከዚህ በመነሣት ነው። ከተራ ማለት መዝጋት፣ ማቆም፣ ማገድ፣ ማጠር፣ ዙሪያውን መያዝ፣ መክበብ፣ መከለል ማለት ነው።» ብለዋል።

ታሪኩ ከጌታችን ጥምቀት ጋር በተያያዘ ምሳሌነት አለው። ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀበት ጊዜ የላይኛው ሸሽቶ ወደ ላይ ተመልሶ ሽቅብ ፈሷል። የታቹም ወደ ታች ሸሽቷል። የላይኛው ፈሳሽ ተቋርጦ እንደ ክምር ተቆልሎ መቅረቱ÷ ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ድረስ በዘር ይወርድ የነበረው ፍዳ መርገም በክርስቶስ ቤዛነት ተቋርጦ ለመቅረቱ፣ ከአበው ወደ ዉሉድ ሳለመተላለፉ፤ የታቹም ፈጽሞ መድረቁ ኃጢአተ አዳም ከሥሩ እንደ ተነቀለ ወይራ ሆና ለመውደቋ ምሳሌ ነው። እስራኤል ፈለገ ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ኢያሪኮ አቅንተው መኼዳቸው ምእመናን በጥምቀት ከቊራኝነት ተላቀው እግራቸውን ወደ ልምላሜ ገነት ወደ ዕረፍት መንግሥተ ሰማያት አቅንተው ለመኼዳቸው ምሳሌ ነው። በጠቅላላው ኢያሱ የጌታ፣ እስራኤል ዘሥጋ የምእመናን፣ ዮርዳኖስ የጥምቀት፣ ምድረ ርስት የገነት መንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው። ለአይሁድ በትእዛዝ ከታወጁት ስምንት በዓላት አንዱ ***የዳስ በዓል /በዓለ መጸለት/*** ነው። ይህም የአዝመራ መክተቻ በዓል ነው። በሰባተኛው ወር በዐሥራ አምስተኛው ቀን፣ እህል ከተከማቸ በኋላ የእስራኤል ልጆች ለሰባት ቀናት ዳስ ጥለው ድንኳን ተክለው እየተቀመጡ አምላካቸውን ያመሰግኑ ነበር። ዘሌዋ.23÷39-43። የበዓለ መጸለት ምሳሌነቱ ለሐዲስ ኪዳኑ በዓለ ጥምቀት ነው። ይኸውም ዛሬ እኛ በዚህ ወቅት ታቦት ይዘን፣ ከወንዝ ወርደን፣ ድንኳን ተክለን በማክበራችን ይፈጸማል።

ቀደም ባለው ጊዜ የአንድ አጥቢያ ታቦት በከተራ ዕለት የሚወርደው ከአንድ የተወሰነ ቦታ ብቻ ሳይሆን በየሰበካው አቅጣጫ ነበር። ታቦቱ የወረደበት ሰፈር ድግስ ይደግሳል። ይህም በየዓመቱ ስለሚለዋወጥ ሕዝቡ ደስ ብሎት ያደርገዋል። በገጠሩ ክፍል ውኃ በማይገኝበት አካባቢ ወንዶቹ ለባሕረ ጥምቀቱ ይሆን ዘንድ እየቆፈሩ ይከትራሉ። ሴቶች ደግሞ ከሩቅ ቦታ እየኼዱ ውኃ በእንስራ እየቀዱ እያመጡ የከተራው ግድብ በውኃ ተሞልቶ የዮርዳኖስን ባሕር እንዲመስል ያደርጉታል። ታቦተ ሕጉ ለአዳር ሲጓዝ እናቶች ለበዓሉ መስተንግዶ ምግቡንና መጠጡን አሰናድተው ካህናቱንና በባሕረ ጥምቀቱ የሚያድሩትን ይጋብዛሉ። ጥር 10 ቀን /ከተራ/ ቅዳሜና እሑድ ገጥሞት ***በዓለ ሰንበት*** ካላገደ በቀር



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

በዚህ ቀን ገበሬው ሞፈር ቀንበሩን አቀናብሮ በቅርብ ባለው ማሳ ላይ በሬዎቹን ጠምዶ መሬቱን ተልሞ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ፈር ከዚያም በላይ ቢሆን ማረስ የተለመደ የሀገር ባህልና ልማድ ነው:: በዚህ ቀን መሬቱ ሲተለም ረድኤት፣ በረከት እንደ ሚገኝ ያምንበታል:: /ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ <u>የቤተ ክርስቲያን የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u>፣ ቅጽ 12፣ ገጽ 196/::

ጥር 10 ቀን ከቀኑ በአራት ሰዓት በመላው አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ዋዜማ ይቆማል:: ከሰዓት በኋላ ታቦታቱ በተለያየ ሕብር በተሸለሙ የክህነት አልባሳት በደመቁ ካህናትና የመጾር መስቀል በያዙ ዲያቆናት ክብረው፣ ከቤተ መቅድስ ወደ አብሕርተ ምጥማቃት ለመሄድ ሲነሡ መላው አብያተ ክርስቲያናት የደወል ድምፅ ያሰማሉ:: ምእመናን ከልጅ እስከ ዐዋቂ በነቂስ ወጥተው በዐጸደ ቤተ ክርስቲያንና ታቦታቱ በሚልፉባቸው መንገዶች ይሰባሰባሉ::

ካህናቱ «ወረደ ወልድ እምሰማያተ ወስተ ምጥማቃት በፍሥሐ ወበሰላም፤ ቅድመ ዓለም የነበረ እግዚአብሔር ወልድ በሰላምና በደስታ በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከሰማያት ወረደ፤ ከዊኖ ሰብአ በዮርዳኖስ ተጠምቀ፤ ሰው ኾኖ በዮርዳኖስ ተጠመቀ» እያሉ ይዘምራሉ:: እልልታ፣ ሆታ፣ ሃሌታ፣ ግርግርታ ይሰማል:: የሰንበት ት/ቤት መዘምራን በዝማሬና በሽብሸባ፣ ጎበዙ በሆታ፣ ሴቶች በእልልታ... ሁሉም በሚረዱት መንገድ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ:: ታቦታቱን አጅበው ወደ ባሕረ ምጥቀቱ በኅብረት ያመራሉ::

ዩኒፎርም የለበሱ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን፣ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ዲያቆናትና ቀሳውስት ከታቦታቱ በፊት፤ የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣ አረጋጠውያን አበውና መላው ምእመናን ከታቦታቱ ኋላ ይጓዛሉ:: ዕጣኑ፣ ዝማሬው፣ ታቦታቱ አገሩን እየባረኩት ነው የሚጓዙት:: ቀደም ብለው በባሕረ ጥምቀቱ ዙሪያ ሰፍረው የታቦታቱን መምጣት በጉጉት የሚጠባበቁ ምእመናን በእልልታና በስግደት ይቀበላሉ:: የዓመቱ ተረኞች የኾኑት አድባራት /የምራት ባለተረኞች/ መዘምራን «ወረደ ወልድ ውስተ ምጥማቃት በፍሥሐ ወበሰላም» የሚለውን ግስ ቃኝተው ያሸበሽባሉ:: ቃለ ምዕዳንና ጸሎተ ቡራኬ ተሰጥቶ ታቦታቱ ለማደርያ ወደ ተዘጋጀላቸው ወደ መንበረ ክብራቸው ይገባሉ:: ካህናቱም ለበዓሉ የሚስማማውን ማኅሌት እስከ መንፈቀ ሌሊት ያደርሳሉ:: ከምእመናኑም የበረቱት በማኅሌት ይሳተፋሉ:: የተቀሩትም በታቦታቱ ማደርያ ዙርያ በተተከሉት ድንኳኖች ሌሊቱን ያሳልፋሉ:: ታቦታቱ ወደ ማደርያ ድንኳናቸው እንደ ገቡ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የተለያዩ መርሐ ግብሮችን በመዘርጋት፣ ጣዕመ ዝማሬዎችን በማሰማት ምእመናንን እያስተማሩ እስከ ንዋመ ሌሊት ይቆያሉ:: ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ሥርዐተ ቅዳሴው ይካሄዳል::

«የምራት ባለተረኞች» የሚባሉት በዓመቱ ግሱን ለመቃኘትና ለማሸብሸብ፣ ማኅሌት ለመቆም፣ ቅዳሴ ለመቀደስና ሌላውንም ሥርዐት ለመፈጸም ሐላፊነት ያለባቸው ገዳማትና አድባራት ካህናት ናቸው:: ለቀጣዩ (ለከርሞው) ዓመት ተረኞች የኾኑትና በአሁኑ ዓመት የምራት ባለተረኞችን የሚረዱት ገዳማትና አድባራት ካህናት ደግሞ «*አጋሺዎች*» ይባላሉ::

የበዓለ ጥምቀት ጸሎተ ቅዳሴ የሚከናወነው በመንፈቀ ሌሊት ስለ ሆነና በማግሥቱም ኸብሎትሽ ስለ ሆነ በዋዜማው ጾም ነው:: የጥምቀት ዋዜማ ከጥሉላት መባልዕት ይጾማል፤ የሚቆርብም ሰው አክፍሎ ያድራል:: እርሱም ጋድ ይባላል:: ለውጥ፣ ምትክ ማለት ነው:: ጥምቀት ረቡዕ ቢውል ጋዱ ማክሰኞ፣ ዐርብ ቢውል ጋዱ ኀሙስ ለውጥ ኾኖ ይጦማል፤ ጥምቀት የሚውልባቸው ረቡዕና ዐርብ አይጦሙም:: /ፍት.ነገ.አን.15/::

በአጠቃላይ በበዓለ ጥምቀት ዋዜማ የታቦታቱ ወደ ወንዝ መውረድና የባሕረ ጥምቀቱ መዘጋጀት የሚከተለው ሃይማኖታዊ ታሪክና ምሳሌ አለው:: ታቦቱ የጌታችን፣ ታቦቱን አክብሮ /ይዞ/ የሚሄደው ካህን የቅዱስ ዮሐንስ፣ ባሕረ ጥምቀቱ የዮርዳኖስ ወንዝ፣ ታቦታቱን አጅበው የሚሄዱትና በዓሉን የሚያከብሩት ምእመናን ወደ ቅዱስ ዮሐንስ እየመጡ የንስሐ ጥምቀት ሲጠመቁ የነበሩት ሰዎች ምሳሌዎች ናቸው:: ታቦታቱ በጥምቀት ዋዜማ ከመንበራቸው ወደ ጥምቀተ ባሕር መውረዳቸውና በዚያ ማደራቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ከማታው ጀምሮ መውረዱንና ተሰልፎ ተራውን ሲጠብቅ ማደሩን ያጠይቃል:: «ጥምቀት የሞቱ አርአያ የመቃብሩ አምሳል ነው:: ከኃጥአን ጋር ተቆጥሮ እንዲጠመቅና እንዲሰቀል የተጣፈውን ቃልኸ ንስሐና ጥምቀት የሚሻ ፍጹም ኃጥእ መስሎ በዮሐንስ እጅ ለመፈጸም በዮርዳኖስ እግር ተጠመቀ::» /ኪ.ወ.ክ ÷517/:: ጌታችን የተጠመቀበት ወርኀ ጥር በእስራኤላውያን ዘንድ የዝናም፣ የበረዶ ወራት ነው:: እንኳንስ ከወንዝ ዳር ከማናቸውም ቦታ ቢኾን ያለ መጠለያ መዋልና ማደር አይቻልም:: በመኾኑም ከዮሐንስ ለመጠመቅ የሚሄዱ ሰዎች ሁሉ በዮርዳኖስ ዙሪያ ድንኳናቸውን ተክ ለው ያርፉ ነበር:: በዚህ አንጻር ዛሬም በባሕረ ጥምቀት ዙሪያ በድ ንኳኖች የተከለሉ ዳሶች ይጣላሉ::

***ለ/ በዕለቱ ጥር 11 ቀን የበዓለ ጥምቀቱ አከባበር***

ጥር 11 ቀን ንጋት÷ ካህናቱ ባሕረ ጥምቀቱን ከበው መጽሐፈ ጥምቀት ይነበባል:: ተስማሚው ቃለ



*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የጃንሜዳን ባሕረ ጥምቀት እንደ ባረኩ /1995 ዓ.ም./*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እግዚአብሔር ደርሶ ሲያበቃ ባሕረ ጥምቀቱ የሚገኝበት ቦታ መንበረ ፓትርያርክ ያለበት ከኾነ÷ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ፣ የመንበረ ጵጵስና ቦታ ከኾነ ሊቀ ጳጳሱ፣ ጳጳሱ ወይም ኤጲስ ቆጶሱ፣ ይህም ካልኾነ ቆሞስ አልያም በቦታው በክብርና በሥልጣን የሚበልጠው ካህን ወይም ገባሬ ሠናይ ቄስ ባሕረ ጥምቀቱን ይባርካል:: አራት የሚበሩ ጧፎች የታሰሩበት መስቀለኛ እንጨት ወደ ባሕሩ ይለቀቃል:: ይህም ጌታችን ሲጠመቅ ብርሃን የመውረዱ ምሳሌ ነው::

ጸሎተ አኰቴት ደርሶ ሥርዐተ ቡራኬው ከተፈጸመ በኋላ ሕዝቡ በረከት ለመቀበል እየተጋፋ ጠበሉን እየተሻማ ይረጫል:: በግፊያው ውስጥ ጉጉት አለ:: በሽሚያው ውስጥ ፍቅር አለ:: ... ሁሉም የሚረጨውን ጠበል ከሰውነቱ ጋር ለማገናኘት ይታገላል:: የጠበሉን ፍንጣቂ ካገኘ ፍጹም በረከት÷ ሙሉ ጸጋ እንዳገኘ ያምናል:: ጎንደርን በመሳሰሉ ስፋፊ ባሕረ ጥምቀት */የዐፄ ፋሲል መዋኛ/* ባላቸው መካናት ሊቀ ጳጳሱ ባሕረ ጥምቀቱን ባርከው ሲያበቁ ምእመናኑ ልብሳቸውን አውልቀው እየተወረወሩ ወደ ባሕሩ በመግባት እንደ ቻሉት ይጠመቃሉ:: የውኃ ዋና ልማድ ያለው ወደ ጥልቁ እየዘለቀ እርስ በርሱ እየታገለና እየተናነቀ በመዳፈቅ የውኃ ዋና ሞያውንና የጉልበቱን ልክ ያሳያል:: የውኃ ዋና ሞያና አቅም የሌለው ከባሕረ ጥምቀቱ ዳርቻ እየተጠመቀ ይወጣል:: በዚህ ዕለት ወጣት ሽማግሌ ሳይባል የገና ጨዋታ፣ የፈረስ ጉግስና ሌሎችም የየብሔረሰቡ የባህል ጨዋታዎች ሲከናወኑ እንደ ሚውሉ የሚያመለክቱ ምንጮችም አሉ::

ይህ ሁሉ እንግዲህ በቱሪስቶች ዐይነ ልቡና ልዩ ትዕይንት በመፍጠር በየዓመቱ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ እንዲተሙ እያደረጋቸው ይገኛል:: ይሁንና በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ወደ ሀገራችን መጥተው የነበሩ «ኢየሱሳውያን ሚስዮናውያን» (Jesuit missionaries) *«የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ታጠምቃለች፤ ጥምቀቷን ትከልሳለች»* ብለው አጥላልተው ጽፈዋል:: ነገር ግን እንደ መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን ገለጻ:- «የጌታ ጥምቀት በየዓመቱ የሚከበረው የአዲስ ሕይወትና ልደት መሠረት በመሆኑ ነው:: ሕይወትነቱንና ብርሃንነቱን ለተቀበሉ ሁሉ ዘወትር አዲስ ስለሆነ ነው::» ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ ዐማኑኤል በበኩላቸው:- «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ይህን የምትፈጽመው ጌታችን ለእኛ ብሎ ያሳየውን ትሕትና ለመመስከር፣ ለምእመናን የጌታን በረከተ ጥምቀት ለማሳተፍ እንጂ የተጠመቁትን ምእመናን እየመላለሰች በየዓመቱ አታጠምቅም:: ጥምቀት አሐቲ መሆኗን ታውቃለችና:: እርግጥ ያልተጠመቁ አረማውያንና ሌሎችም የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ጊዜ እየመጡ በክርስቶስ አምነው ሥርዐቱ ተፈጽሞላቸው ይጠመቃሉ::» በማለት ያስረዳሉ:: ጥሩው ነገር÷ ዛሬ የበዓለ ጥምቀቱ መርሐ ግብር ቢያንስ በሁለት ቋንቋዎች ስለሚተላለፍና ልዩ ልዩ የኅትመት ውጤቶች ስለሚሰራጩ በዚህ ረገድ ኹን ተብሎም ይሁን ባለማወቅ የሚናፈሰው ሐሜት ሳይቀንስ አልቀረም::

ምእመናኑ በመረጨትም ይሁን በዋና ቡራኬ ካገኙ በኋላ ታቦታቱ ካደሩበት ወጥተው በተዘጋጀላቸው ቦታ ይቆማሉ:: መዘምራንም ከታቦታቱ ፊት «ኀዲጎ ተሰዐ ወተሰዐተ ነገደ ቆመ ማእከለ ባሕር ገብአ ወወፅአ በሰላም፤ ዘጠና ዘጠኙን የመላእክት ነገድ ትቶ በባሕር መሀል ቆመ» የሚለው ግስ በባለ ተራው /የምራት ባለተረኛው/ ደብር መሪነት ተቃኝቶ ይሸበሸባል:: የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችም በዓሉን የተመለከተ መንፈሳዊ መዝሙር ይዘምራሉ:: የበዓሉን መንፈሳዊ ታሪክ የተመለከተ ትምህርት ይሰጣል:: በተገኙት አባት ቃለ ምዕዳንና ጸሎተ ቡራኬ ተሰጥቶ ካህናቱ «ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መሬታዊ» የሚለውን ግስ እየዘመሩ ታቦታቱን ከድንኳን አንሥተው መንቀሳቀስ ሲጀምሩ እልልታው ይደምቃል:: መንገዶች በሕዝባዊ ማዕበል ይጥለቀለቃሉ:: ሕዝቡ ግን ግፊያውን አይሰቀቀውም:: ይልቁንም ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳኑ ካለው ፍቅር የተነሣ ላቡን እያፈሰሰ፣ ፍጹም ኃይል በተሞላበት ደስታ እያመሰገነ ታቦታቱን አጅቦ ጉዞውን ይቀጥላል:: ጎበዙ በሆታና በጭፍራ ጉዞውን እያገደና እያስቆመ:-

«እንኳን ለታቦት ለደጉ ጌታ
ይጨበጨባል ለጋለሞታ...፤
ሁሉም ያምረኛል በመር በመሩ
እነ መምሬ ቅኔ ሲመሩ፤

እያለ ታቦቱን በልዩ ልዩ ቃላት ያሞግሳል:: ሴቶቹም እንደዚሁ በበኩላቸው:- ከወላጆቻቸው ሲወርስ ሲዋረስ በመጣው መሠረት የአገር ልብሳቸውን ለብሰው መቀነታቸውን በወገባቸው ሽብ አድርገው የታቦት ዜማ ያሰማሉ::

በሕይወት ግባ በሕይወት
የአገሬ ታቦት ...፤
ሲያምር ዋለ ሲያምር
የአገራችን ደብር፤
እይው ወሮዐት ሲገባ
የእኛ ጌታ ባለአበባ፤
አለው አለው አበባ
የአገሬ ታቦት ወደ መንበሩ ሲገባ፤
ሲወርድ÷ ይመስላል የእሳት ነድ፤
ሲነሣ÷ መሰለ እንበሳ
ርግቤ በቀሚሱ ላይ
ርግቤ በካባው ላይ
የሰላም ምልክት ይዛ ልትታይ፤

/ኢሳ.63÷1 «ርግቤ» ማለታቸው መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል፤ ማቴ.3-16 -17/

ልብሱ አረፈረፈ ልብሱ አረፈረፈ
ርግብ በራሱ ላይ ዐረፈ፤

«ልብሱ አረፈረፈ» ማለት ጥምቀት የሚያደምቅ፣ የሚያነጻ፣ የሚያድስና የሚለውጥ መኾኑን ይገልጽልናል::/ት.ሕዝ.36÷25/::

የማይ ውኃ
ፈሰሰ በር ሐ፤

እያሉ በእልልታና በሆታ ታቦቱን ያጅባሉ:: *«የማይ ውኃ ፈሰሰ በርሐ»* የሚለው አባባል:- ጥምቀት ለሁሉ ይዳረስ ዘንድ፣ ሁሉን ያድስ ይቀድስ ዘንድ፣ በኃጢአት በረሐ የሚቃጠሉትን ሁሉ ያቀዝቅዛቸው፣ ያበርዳቸው፣ ኃጢአታቸውን እንደ በረዶ አጥቦ ያንጻላቸው ማለት ነው:: «ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ፤ እናንተም ትጠራላችሁ፤ ከርኩሰታችሁም ሁሉ፣ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁኹ አዲስ ልብም እሰጣችኋለሁ:: አዲስም መንፈስ

***የበዓለ ጥምቀት ትውፊታዊ አከባበር በስብከት ከሚገለጠው ይልቅ የተጨበጠ ክርስቲያናዊ ማስረጃ ኾኖ ክርስትናን ጠብቆ ኖሯል:: ብዙዎች ጥንታዊውን ክርስቲያናዊ ትውፊት በተመለከቱ ጊዜ እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን እያስታወሱ የሚመለሱበት ታላቅ ምክንያት ሆኗል::***



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

በልባችሁ አኖራለሁ።» የሚል ትንቢት ተናግሯል። /ት.ሕዝ.36÷25/።

ሁሉም በየወገኑ እንዲህ ባለው ሁኔታ በክብር አጅቦ ያወጣውን ታቦት በክብር አጅቦ ወደ ቤተ መቅደሱ ይመልሳል። /ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ፣ ቁጥር 10፣ 1988 ዓ.ም/። ታቦታቱ ከጥምቀተ ባሕሩ ተነሥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዳቸው፣ ጌታችን ከተጠመቀ በኋላ ሳይውል ሳያድር ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ መሄዱን ያጠይቃል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በገዳመ ቆሮንቶስ ትመስላለች።

የበዓለ ጥምቀት ትውፊታዊ አከባበር በስብከት ከሚገለጠው ይልቅ የተጨበጠ ክርስቲያናዊ ማስረጃ ኾኖ ክርስትናን ጠብቆ ኖሯል። ብዙዎች ጥንታዊውን ክርስቲያናዊ ትውፊት በተመለከቱ ጊዜ እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን እያስታወሱ የሚመለሱበት ታላቅ ምክንያት ሆኗል። በማኅበራዊ ኑሮና በባህል በኩል ደግሞ ሕዝብ ከሕዝብ የሚገናኝበት፣ የግል ስሜቱን የሚገልጥበት፣ ባህላዊ ጨዋታን የሚያሳይበት ዕለትና በዓል ስለሆነ ሕዝቡ በናፍቆት ይጠብቀዋል። አዲስ ልብስ ለልጅም ኾነ ለዐዋቂ የሚገዛው ለጥምቀት ነው። በተለይ ይህ የሚጸናው በሴቶች በኩል ነው። «ለጥምቀት ያልኾነ ቀሚስ ይበጣጠስ» የሚለው ብሂል ይህን አባባል ያጠናክረዋል። የተቀመጠው፣ የተከተተው ወጥቶ የሚለበስበት፣ የሌለው ተበድሮ ተለቅቶም ገዝቶ የሚያጌጥበት ዕለት ነው። በልማዳችን÷ ለጥምቀት አንዲት ሴት ተኳሪቤት ተውሳ አምራ ተኳኩላ ትወጣለች። ወንዱም አፍዓዊ ውበት ብቻ ይማርከውና አጭቶ ያገባታል። ቤት ስትገባና በቅርብ ሲያያት ሁናቴዋ ሁሉ እንደ ገመተው ያልኾነ እንደ ኾነ *«ጥምቀት አረደኝ»* ይላል። በአጠቃላይ ክርስቲያናዊ እምነቱን የሚያጸናበት፣ ማኅበራዊ ግዳጁን የሚፈጽምበት፣ «እስትንፋስ ያለው ሁሉ» በነቂስ ወጥቶ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት ዕለት ነው- በዓለ ጥምቀት።

## የጥምቀት በዓል አከባበር በአዲስ አበባ

### ከእንጦጦ ተራራ እስከ ጃንሆይ ሜዳ

ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በእንጦጦ ተራራ ላይ የከተሙት በ1871 ዓ.ም ሲኾን አዲስ አበባ ደግሞ የተቆረቆረችው በ1878 ዓ.ም ነበር። በወቅቱ የነበራት የሕዝብ ብዛት 60,000 ያህል ነበር። ከዚህ ወቅት ቀደም ብለው ወይም በዚህ ወቅትና ከዚያም በኋላ ዘግየት ብለው ከታነፁ የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ከያዝነው ርእስ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የጥቂቶቹን የምሥረታ ዘመን ማስታወስ ይገባል።

በቃል ሲያያዝ እንደ መጣው ከአዲስ አበባ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት አንዱ የየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ነው። ቤተ ክርስቲያኑ የተቆረቆረው በዐፄ ላልይበላ /1140 -1180 ዓ.ም/ ነበር። ይኸውም ቤተ ክርስቲያኑ ቀድሞ ይገኝበት የነበረው የየካ ተራራ አናት ለውቅር ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ስለሚመች ነው። ከተራራው ወርዶ ዛሬ ከሚገኝበት ቦታ የተተከለው በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በ1898 ዓ.ም ሲሆን ሕንፃውን ያሠሩት ደግሞ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በ1919 ዓ.ም ነው። የደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን በ1845 ዓ.ም በእንጦጦ ተራራ ላይ ተተክሎ ነበር። ከእንጦጦ ተራራ ወርዶ ዛሬ ካለበት የቀበና ወንዝ አጠገብ የተተከለው በ1875 ዓ.ም በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት /1881 -1906 ዓ.ም/ ነው። የጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን የተተከለው በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በ1870 ዓ.ም ሲሆን የአሁኑ ሕንፃ የታነፀው ደግሞ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት /1909-1922 ዓ.ም/ ነው። የመካነ ሥላሴ በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን በ1882 ዓ.ም በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ተተክሏል። ይሁንና ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ አርበኞች መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልን በ1936 ዓ.ም ባሠሩ ጊዜ የቅድስት ሥላሴ ታቦት ከዚያ ወጥቶ አሁን ወደ ሚገኝበት ቦታ ተዛውሯል።

መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም /እልፍኝ ገብርኤል/ የተሠራው በ1889 ዓ.ም ቢሆንም አሁን ካለበት ቦታ የተተከለው በ1898 ዓ.ም ነው። የርእሰ አድባራት እንጦጦ መንበረ ፀሐይ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተተከለችው ደግሞ በእቴጌ ጣይቱ በ1876 ዓ.ም ነው። የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ ክርስቲያን በዐፄ ምኒልክ በ1874 ዓ.ም ተተክሏል። የገነተ ጽጌ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በዐፄ ምኒልክ በ1888 ዓ.ም ተተክሏል። የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የተተከለው በ1903 ዓ.ም በልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት /1906-1909 ዓ.ም/ ጊዜ ነው። የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተመሠረተችው በ1904 ዓ.ም በእቴጌ ጣይቱ አማካይነት ነው። የቀበና መካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን የተተከለው የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ የፍርድ ሚኒስትር በነበሩት በአፈ ንጉሥ ጥላሁን በ1907 ዓ.ም ነው። የደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ /በ1909 ዓ.ም/፣ ደብረ ነጎድጓድ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ /1914 ዓ.ም/፣ መንበረ ንግሥት ቁስቋም ማርያም /በ1919 ዓ.ም/፣ የመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ /በ1917 ዓ.ም/፣ የታዕካ ነገሥት በኣታ ለማ ርያም ገዳም /1910 ዓ.ም መሠረቷ ተጥሎ በ1920 ዓ.ም የተጠናቀቀ/፣ የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም /በ1922 ዓ.ም መሠረቷ ተጥሎ በ1926 ዓ.ም የተጠናቀቀ/፣ /የመርካቶ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን/ በ1948 ዓ.ም በእቴጌ መነን የተ ተከለ/ እና አንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል /ጭቁኑ ሚካኤል -1968 ዓ.ም/ ተተክለዋል። */ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ፣ ደጃዝማች*



*የጃንሆይ ሜዳ ባሕረ ጥምቀት ትዕይንት*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ 1962 ዓ.ም፤ ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ *የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት*፣ ቅጽ 1፤ መ/ር ሰሎሞን ቶልቻ፣ *ፍኖተ ቤተ ክርስቲያን*፣ 1991 ዓ.ም/::

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከየተተከሉባቸው ዘመናት አንሥቶ በተሠየሙበት በየሰበካው አቅጣጫ ወደሚገኙ የውኃ ምንጮች በተናጠል በመውረድ በዓለ ጥምቀትን ያከብሩ ነበር:: ተቀራርበው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ታቦቶቻቸውን በአንድ ቦታ እንዲያሳድሩ ትእዛዝ የተላለፈው በጻድቁና ጠቢቡ ንጉሥ ላልይበላ ዘመነ መንግሥት /1140-1180 ዓ.ም/ እንደ ነበር ማስታወሳችን አይዘነጋም:: እንደ ሊቀ ማእምራን ጽጌ ከበረ ገለጻ:- «በአዲስ አበባ ያሉት ታቦታትም በቦታ ርቀት እስከ ተለያዩበት ቀን ድረስ በእንጦጦ ጋራ ጥግ በአንድ ላይ በመገናኘት እያደሩ ያከብሩ ነበር:: ከዚያም በኋላ የተቀሩት በጃንሆይ ሜዳ /ጃንሜዳ/ በአንድ ላይ የሚያድሩት ከጻድቁና ጠቢቡ ንጉሥ ላልይበላ ሲወርድ ሲወራረድ በመጣ ዐዋጅ ነው::»

በእንጦጦ ተራራ በዓለ ጥምቀትን በአንድነት በማክበር የሚታወቁት የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስና የርእሰ አድባራት መንበረ ፀሐይ ቅድስት ማርያም አብያተ ክርስቲያናት ናቸው:: ባሕረ ጥምቀቱም በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በሚገኘው መስክ ላይ ካለው ረባዳ ሥፍራ /የተፈጥሮ ምንጭ/ ነው:: የመንበረ ንግሥት ቁስቋም ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታቦት ደግሞ ከጀርባው ከሚገኘው ወንዝ እየወረደ ያድር ነበር::

መልአከ አርያም ሐረገ ወይን ብርሃኑ በበኩላቸው በዓለ ጥምቀት በጃንሆይ ሜዳ /ጃንሜዳ/ መከበር የጀመረው ከ1887 ዓ.ም አንሥቶ መኾኑን አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑልን በቃል አስረጅነት በመጥቀስ ይገልጻሉ:: ለመሆኑ <ጃንሜዳ> የሚለው ስያሜ ከየት መጣ? በዓለ ጥምቀት በጃን ሜዳ እንዲከበር የተደረገበት ምክንያት ምንድን ነው? እኒህን ጥያቄዎች በተመለከተ አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል እንደ ሚከተለው ያስረዳሉ::

*«ጃንሜዳ:- ማለት በዝርዝር ሲታይ ጃን፣ ጃኖ ከሚለው ጋር ተናቦ የሚገለጽ ቃል ነው:: በቀድሞው ዘመን ነገሥታት ለመሾም ለመሻር፣ ዳኝነት ለማየት፣ ለሊቃ ውንት መዓርግ ለመስጠት፣ በሀገር ጉዳይ ዐዋጅ ሊያስነግሩ ሲያስቡ በቤተ መንግሥታቸው አቅራቢያ በሚገኝ ሰፊ ሜዳ ወይም ከፍታ ቦታ ላይ የጃኖ ድንኳን ይተከላሉ:: በዚህም መኳንንቱን ሰብስበው የሾሙትን የሻሩትን ውሳኔ .... ሌላውንም የሀገር ጉዳይ በዐዋጅ ያስነግራሉ:: ይህ ሥርዐት የሚከናወንበት ሰፊ ሜዳ ከጃኖ ጋር ተናቦ የቦታው መጠሪያ ጃንሜዳ ተብሏል:: በዚህ ስያሜ ይጠሩ ከነበሩት መካከል:- <ጃን ተከል> በጎንደር ነገሥ ታት፣ <ጃን መራቂ> በላስታ ነገሥታት፣ <ጃን ተራራ> በአማራ ሳይንት በዐፄ በእደ ማርያም /1460-1470 ዓ.ም/ ሊጠቀሱ ይችላሉ:: በደብረ ታቦርም ጃን ሜዳ የሚባል ሰፊ ሜዳ እንዳለ ይነገራል::*

*በሌላም በኩል «መሐል ሰፋሪ» የሚባል ጦር አለ:: ይኸውም የጥንቱ የመኳንንት ጉባኤ ወይም መማክርት ማለት ነው:: ጦሩ ንጉሠ ነገሥቱ በሚቀመጥበት ከተማ ከየደምቡ እየተውጣጣ፣ በወር ተራ እየገባ በቅርብ የሚገኝ ጦር ነው:: ይኸውም ጦር ደምቡ:- /1/ ሠናድር ያዥ /2/ ጠመንጃ ያዥ /3/ ፈረስ ዘበኛ /4/ ማለፊያ ጠመንጃ ያዥ /5/ የባለሟል ደምብ የጨዋ ልጅ ተብሎ የሚጠራ /6/ የውኃ ስንቁ ተብሎ የሚጠራ በሊጋባው የሚታዘዝ /7/ የግቢ ሚኒስትርን፣ የገንዘብ ሚኒስትርንና የዕቃ ቤት ባልደረባን ይቀላቅላል:: /ደጃዝማች ከበደ ተሰማ፣* <u>*የታሪክ ማስታወሻ*</u>*፣ 1962 ዓ.ም፣ ገጽ 56/:: ጃን ሜዳ፣ ጃን ተከል፣ ጃን ተራራና ጃን መራቂ ንጉሥን ከሥልጣን ለማውረድ፣ ሌላ ንጉሥ ለማንገሥ በመሐል ሰፋሪው የሚመከርባቸው ቦታዎች ነበሩ:: በመንግሥት ላይ /በንጉሡና በባለ ሥልጣኖቻቸው ላይ/ የሚደረግ አድማ በመኾኑ የጃኖው ድንኳን ከሩቅ እንዳይታይ በማቅ ይሸፈን ነበር:: ... ስለዚህ <ጃን> የሚል ቅጽል የተሰጣቸው በየመንግሥታቱ በዚህ መልክ የተሠራባቸው ቦታዎች ናቸው:: በዚህ መሠረት በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት /1881-1906 ዓ.ም/ ጃንሜዳ:- ንጉሠ ነገሥቱ ከሚሰበሰቡበት፣ የመንግሥት ሥራ ከሚሠራበት ይልቅ መሐል ሰፋሪው በየጊዜው በስውር እየተሰበሰበትና አድማ እያደረገበት አስቸገረ:: በመሆኑም እቴጌ ጣይቱ ይህን የመሰለ ሜዳ የክፉ ምክር መምከሪያ ኾኖ ከሚኖር ተባርኮ ለጥምቀት በዓል ማክበርያ ቢሆን ብለው ለዐፄ ምኒልክ ሐሳብ አቀረቡላቸው:: ዐፄ ምኒልክም <ማለፊያ> ብለው ሐሳባቸውን በመቀበል ጃንሜዳ የጥምቀት በዓል ማክበርያ እንዲኾን አዘዙ::»*

ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ዐልጋ ወራሻቸው ልጅ ኢያሱ መኾናቸውን ግንቦት 10 ቀን 1901 ዓ.ም ጉባኤ ተደርጎ ዐዋጅ ያስነገሩት፣ «ንሥረ ተፈሪ» የሚባለው የመጀመሪያው አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በ1921 ዓ.ም. ያረፈው በጃንሜዳ ነበረ:: ከዚህና መሰል ታሪኮች ጋር በማያያዝ «ጃንሆይ ሜዳ» ተብሎም ይጠራል:: /ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ <u>*ዝክረ ነገር*</u>፣1962 ዓ.ም፣ ገጽ 506-509/::

ጃንሜዳ ከ1887 ዓ.ም ጀምሮ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ተመርጦ የጥምቀት በዓል ማክበርያ ቢሆንም የአድማ ስብሰባው ግን በተለይ ከመጋቢት 10 ቀን 1910 ዓ.ም ጀምሮ በየጊዜው እያየለ ቀጥሎ እስከ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ /1922 ዓ.ም/ ድረስ ይካሄድበት እንደ ነበር ደጃዝማች ከበደ ተሰማ የዐይን ምስክርነታቸውን ጠቅሰው ጽፈዋል:: ለአድማው ምክንያት የኾነው በዐፄ ምኒልክ የተዋቀረው ካቢኔ ሚኒስትሮች «የየራሳቸውን የግል ጥቅም እንጂ ለአገርና ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የሚጠቅም ሥራ አልሠሩምና ከሥልጣናቸው ይሻሩ» በማለት ነበር:: /<u>የታሪክ ማስታወሻ</u>፣ 1962 ዓ.ም፣ ገጽ 56-63/::

በአለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል የታሪክ ምስክርነት መሠረት በ1887 ዓ.ም በዓለ ጥምቀትን ለመጀመሪያ ጊዜ በጃን ሜዳ በኅብረት ያከበሩት:

- የመካነ ሥላሴ በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን /በ1882 ዓ.ም የተተከለ/፣ የገነተ ጽጌ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን /በወቅቱ ዛሬ አዲስ አበባ ሬስቶራንት ተብሎ በሚጠራው ቦታ በመቃኞ-መቃረቢያ ውስጥ የነበረ/ እና የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም /ከ1878-1889 ዓ.ም ድረስ በደብረ መንክራት ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ገዳም ድርብ የነበረ/ ናቸው::ከ1887 ዓ.ም በኋላ አብያተ ክርስቲያናት እየታነፁ፣ ጥንታውያኑ እየፈረሱና ዳግመኛ እየተሠሩ ሄዱ:: በተለይ በ1898 ዓ.ም ያረጁ ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት እንዲ ታደሱ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ዐዋጅ አውጥተው ነበር::

አቶ መብዐ ሀብተ ጊዮርጊስ ይባላሉ:: ከ1920 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ አበባን በሚገባ የሚያውቋት የዕድሜ ባዕለ ጸጋ ናቸው:: የጥምቀት በዓል በጃንሜዳ መከበር የጀመረበትን ዓመት በውል አያስታውሱትም:: ይሁንና በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት /1909-1922 ዓ.ም/ ጀምሮ በጃንሜዳ የጥምቀት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በዓል ሲከበር እንደ ሚያውቁ ይናገራሉ:: ታቦታቱ ወርደው የሚያድሩት በአፄ ንጉሥ ጥላሁን ሰፈር ከፈረንሳይ ኤምባሲ በታች የቀበና ወንዝ ከሚወርድበት መስክ ነበር::

ይኸውም ለሥርዐቱ አፈጻጸም ያመች ዘንድ መጠመቂያውን /ባሕረ ጥምቀቱን በመሻት ይመስላል:: እንደ ሚመስለው የጃንሜዳው ባሕረ ጥምቀት ዘግይቶ ነው የተሠራው:: ከቀበና ወንዝ እስከ ጃንሜዳ የሚደረገው የታቦታቱ ዑደት ሁኔታ ከዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ እንደ ቆየ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ የዐይን ምስክሮችን በመጥቀስ ያስረዳሉ::

ጠዋት ባሕረ ጥምቀቱ ተባርኮ ሥርዐተ ጥምቀት ከተፈጸመ በኋላ ታቦታቱ ወደ ጃን ሜዳ ይገባሉ:: «ኅዲጎ ተስዐ ....» ተብሎ ሙሉ ሥርዓቱ በጃን ሜዳ ይፈጸማል:: አቶ መብዐ ህብተ ጊዮርጊስ በወቅቱ ጃን ሜዳ ያድሩ ከነበሩ አድባራት የዘረዘሯቸው:- ቀበና መካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን /1907 ዓ.ም/፣ ገነተ ኢየሱስ ገነተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን /1918-1926 ዓ.ም/ ፣ ቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን /1903 ዓ.ም/፣ ታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም /1910-1920 ዓ.ም/፣ ገነተ ጽጌ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን /1888 ዓ.ም/፣ መካነ ሥላሴ በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን /1882 ዓ.ም/ እና የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም /1889 ዓ.ም/ ናቸው:: በተለይ በ1925 ዓ.ም ተራው የታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም ነበር:: በዚህ ጊዜ በጃን ሜዳ የተገሰሰው ግስ «ወብዙኀን ኖሎት መፅኡ ወስዕኑ ከሚቶታ ለታዕካ ነገሥት፣ እስከ ይመፅእ ዐቢይ ኖላዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት» ተብሎ መዘመሩን ጭምር አቶ መብዐ ህብተ ጊዮርጊስ ያስታውሳሉ::

ሌሎችም የአዲስ አበባ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በየሰበካቸው በሚገኝ አመች ቦታ በዓለ ጥምቀትን ያከብሩ ነበር:: ለምሳሌ:- ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤልና የካ ደብረ ኀይል ቅዱስ ሚካኤል አድዋ ድልድይ አጠገብ በሚገኘው የፈረስ ባልደራስ ሜዳ /ራስ አባተ ሜዳ/ ያከብሩ ነበር:: ይሁንና ንጉሠ ነገሥቱ በሚገኙበት በጃን ሜዳ እንዲያከብሩ ጥሪ ተደርጎላቸው በ1939 ዓ.ም ጃንሜዳ መምጣት እንደ ጀመሩ በወቅቱ የነበሩ አበው ያስረዳሉ:: ከእነዚህም ጋር ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል፣ ቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም፣ ደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ፣ መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ እና አንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በየጊዜው እየተጨመሩ በጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት እያደሩ በዓሉን ያከብሩ ነበር:: መምሬ ተዘራ ወርቁና ሊቀ ትጉሃን ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም እንደ ሚያስረዱት ከእኒህ ታቦታት መካከል:- የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል፣ የደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል፣ የደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ የየካ ደብረ ኀይል ቅዱስ ሚካኤል አብያተ ክርስቲያናት ከቦታው ርቀትና እና ከወቅቱ የሕዝብ ብዛት ሁኔታ ጋር ታይቶ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በየአቅራቢያቸው ለባሕረ ጥምቀት በተመደበላቸው ሥፍራ እንዲያድሩ ተደርጓል::

በዚህም መሠረት የየካ ደብረ ፀሀል ቅዱስ ሚካኤል እና የደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል አብያተ ክርስቲያናት በክፍለ ከተማ 16 ቀበሌ 03 አካባቢ በሚገኘው የራስ አባተ ሜዳ /ግቢ ውስጥ/፣ የደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ደግሞ ከደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን /በ1948 ዓ.ም የተተከለ/ ጋር በክፍለ ከተማ 18 ቀበሌ 26 አካባቢ በሚገኝ ሥፍራ የሚያድሩ ኾነዋል:: የደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ፣ የመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ እና አንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ታቦታት ወደ ጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት መምጣት የጀመሩት ከዚህ በኋላ ነው:: ይኸውም በየደብሩ በድርብነት የሚገኙትን ጽላት ጨምሮ መሆኑን መምህር ዐሥራት ደስታ ይገልጣሉ::

ዛሬ በገዳመ ኢየሱስ ቅጽር ግቢ በሚገኘው ትንሹ የአቃቂ ወንዝ ከአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ቀደምት የኾነው የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን /በ1826 ዓ.ም በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የተተከለ/፣ የደብረ አሚን ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን /በ1898 ዓ.ም/፣ የደብረ ገሊላ ቅዱስ ዐማኑኤል ካቴድራል /1905 ዓ.ም/፣ የማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን /በ1916 ዓ.ም/፣ የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን /በ1955 ዓ.ም/ እና የጽርሐ ጽዮን ሐዋርያት ጎላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን /1934 ዓ.ም/ እየተገናኙ በዓለ ጥምቀትን ያከብሩበት ነበር:: ከእነዚህ መካከል የቀራንዮ መድኃኔ ዓለምና የደብረ ገሊላ ቅዱስ ዐማኑኤል ካቴድራል አብያተ ክርስቲያናት ዛሬም በዚያው ሥፍራ ሲያከብሩ፤ የማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በጎፋ ሰፈር፤ የደብረ አሚን ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና የጎላ ጽርሐ ጽዮን ሐዋርያት ቅዱስ ሚካኤል አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በክፍለ ከተማ ሦስት ቀበሌ 46 በሚገኘው ስፍራ ያከብራሉ:: ለ1997 ዓ.ም የጥምቀት በዓል አከባበር የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ካወጣው መርሐ ግብር ለመረዳት እንደ ሚቻለው በአዲስ አበባ 39 ያህል አብሕርተ ምጥማቃት (የታቦት ማደርያዎች) ይገኛሉ:: በ39ኙ አብሕርተ ምጥማቃት የሚያድሩት ታቦታት አጠቃላይ ድምር 93 ናቸው:: ይህ ቁጥር በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ በድርብነት ያሉ ታቦታትን አያካትትም:: የጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት ከሌሎች ይልቅ በርካታ ታቦታት ከዐሥራ አንድ በላይ) የሚያድሩበት የበዓለ ጥምቀተ ውሎ የትኩረት ማዕእል ነው::

በጃንሜዳ እስከ 1997 ዓ.ም ሲያገለግል የነበረው ባሕረ ጥምቀት ተሠርቶ በዓለ ጥምቀት ከቀድሞው በበለጠ ሁኔታ መከበር የጀመረው በ1936 ዓ.ም ነበር:: ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በ1936 ዓ.ም በስፍራው የውኃ ቧንቧ እንዲዘረጋ፣ የባሕረ ጥምቀት ገንዳው በግንብ እንዲሠራ፣ የኤሌክትሪክ መብራት በቦታው እንዲገባ አድርገዋል:: ከዚህም ባሻገር መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችንን ሲያጠምቀው የሚያሳየው ከደንጊያ የተቀረጸው ሥዕልና ከሥዕሉ ግራና ቀኝ ያለው ቆመ ብእሲ ዙሪያውን በግንብ ተሠርቶ በቧንቧ የብረት ማገር ውብ ኾኖ እንዲታጠር አድርገዋል:: በሕንፃው ግድግዳ ላይ የአሠራሩን ሁኔታና አፈጻጸም የሚገልጸው ሙሉ ቃል እንደ ሚከተለው ይነበባል፤ *«ስለ ጥምቀተ ባሕረ ዮርዳኖስ መታሰቢያ ይህ ሕንፃ ተመሠረተ:: <የምወደው የባሕርይ ልጄ ይህ ነው፤ በእርሱ ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤> ጥር 11 ቀን 1936 ዓ.ም፤ ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ::»*

በተጨማሪም ወደፊትም ኾነ ወደ ኋላ ላለው የታሪክ ገጽታ ማስረጃ ይሆን ዘንድ የባሕረ ጥምቀቱ ዙሪያ በዐጸድና በልዩ ልዩ አበባዎች እንዲያጌጥ አስደርገዋል:: ይሁንና ከጊዜ በኋላ:- የብረት አጥሩ፣ በደንጊያ ሰሌዳ ላይ የተሠራው የመጥምቁ ዮሐንስና የጌታ ሥዕል፣ በውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳው ላይ የነበረው ጽሑ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

**ቤተ ክርስቲያናችን የጃንሜዳን ባሕረ ጥምቀት አክብራ፣ ባርካ፤ ታቦታቱ በቦታው ላይ ማደር ከጀመሩበት፤ ቅዳሴ፣ ማኅሌት በአጠቃላይ ሥርዐተ ጸሎት ከደረሰበት ጊዜና ሰዓት አንሥቶ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ባሕረ ጥምቀቱ እንደ አንድ ቤተ ክርስቲያን ነበር የሚቆጠረው።**

ፍ፣ በዙሪያው የተተከለው አትክልትና የጥድ ዛፍ ኾን ተብሎ እንዲጠፋና እንዲበላሽ ተደርጎ ነበር። ይህም ከንጽሕና አያያዝና ከጽኑ ጥበቃ ጉድለት የተነሣ የመጣ ነበር። በመሆኑም ለ1991 ዓ.ም በዓለ ጥምቀት አከባበር የተሠየመው ኮሚቴ ባቀረበው ሪፖርት መሠረት፡- ከጠቅላይ ቤተ ክህነት፣ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከትና በቦታው ላይ የጥምቀት በዓልን ከሚያከብሩት አድባራትና ገዳማት ተውጣጥቶ በተቋቋመ ኮሚቴ አማካይነት በተደረገው የ262,000.00 ወጪ የባሕረ ጥምቀቱን ይዞታ በአጥር የማስከበር፣ የፈረሰውን የመጠገንና የተጨማሪ ግንባታዎች ሥራ ተከናውኗል። ይህም በ1994 ዓ.ም ጥር ወር በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ተመርቋል። ለጊዜውም ሁለት የጥበቃ ሠራተኞች እንዲመደቡበት መደረጉ በወቅቱ ተገልጸ ነበር።

ቀደም ባለው ጊዜ ታቦታት ከመንበራቸው ተነሥተው ወደ ባሕረ ጥምቀት ሲወርዱም ይሁን ሲመለሱ ከብፁዓን አባቶች ባለመለየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ፣ መኳንንቱ፣ መሳፍንቱ፣ ልዕልታቱ፣ ሠራዊቱና የሠራዊቱ አዛዦች፣ አምባሳደሮች፣ ታላላቅ የከተማው ነዋሪዎች፣ በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ የከተማው ምእመናን በጃን ሜዳ እየተገኙ በዓለ ጥምቀትን ሲያከብሩ ኖረዋል። እስከ 1958 ዓ.ም ድረስ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም የተምሮ ማስተማር ማኅበር እና በጠቅላይ ቤተ ክህነት የታሪክ፣ ድርሰትና ስብከት ክፍል /በኋላ የስብከተ ወንጌልና ማስታወቂያ መምሪያ/ አማካይነት በባሕረ ጥምቀቱ የስብከተ ወንጌል፣ የመዝሙርና የድራማ መርሐ ግብሮች ይቀርቡ ነበር። በታቦታቱ ጉዞ ወቅት በአብዛኛው የመዝሙር ትርኢት እያቀረቡ ያጅቡ የነበሩት መዘምራን /ደብተሮች/ ነበሩ። በባሕረ ጥምቀቱ ዙሪያ ይሰጥ በነበረው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት /ቢያንስ ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ/፡- አባ መዓዛ ቅዱሳን ገብረ ሕይወት/ ዛሬ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ/፣ መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ፣ ንቡረ እድ ኤርሚያስ ከበደ፣ አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ፣ ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ፣ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ .... የሚታወሱ ናቸው።

በ1958 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት በአዲስ አበባ አድባራት፣ በሌሎችም ጠቅላይ ግዛቶችና አውራጃዎች ወጣቶችን ከአባቶቻቸው ጋር የሚያገናኝ መንፈሳዊ ማኅበር የሚያስፈልጋቸው መኾኑ ታመነበት። ስለሆነም በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ የስብከተ ወንጌል ድርጅት ሥር የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር እንዲቋቋም ተደረገ። በ1959 ዓ.ም ደግሞ በመንበረ ፓትርያርኩ ዋና ጽ/ቤት ውስጥ በየደብሩና በየአካባቢው የተቋቋሙትን የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር የሚቆጣጠር፡- «የወጣቶች አንድነት ማእከላዊ ጽ/ቤት» ተቋቋመ። ማእከላዊ ጽ/ቤቱ እስከ 1961 ዓ.ም ሚያዝያ ወር ድረስ 39 ማኅበሮችን በሥሩ አቅፎ ነበር። ማእከላዊ ጽ/ቤቱ የሚመራው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የታሪክ፣ ድርሰትና ስብከት ክፍል ነበር። በወቅቱም የበላይ ሐላፊው አባ ገብረ መድኅን ገብረ ዮሐንስ /ዛሬ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት/ ነበሩ። *«ከዚያ በኋላ በደንብ ልብስ የሚታዩ ጥቂት የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች እና ነጠላ የለበሱቱም ቢሆኑ ታቦታቱን አጅበው አውጥተው አጅበው በመመለስ የበዓሉ ድምቀት እየኾኑ መጡ»* ይላሉ ትዝታቸውን ያወጉን መሪጌታ ተስፋ ጥሩነህ እና መምህር ዐሥራት ደስታ። ዛሬ በኢትዮጵያ ከ20,000 በላይ ከኾኑት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በ8676ቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ ሲሆን እኒህም ከሁለት ሚልዮን በላይ ወጣቶችን፣ አዳጊዎችንና ሕፃናትን በአባልነት መያዛቸውን የ1997 ዓ.ም የ24ኛው መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሪፖርት ይጠቁማል።

ከከተራ /ጥር 10 ቀን/ ጀምሮ እስከ ቃና ዘገሊላ /ጥር 12 ቀን/ ድረስ ለሦስት ተከታታይ ቀናት በባሕረ ጥምቀቱ /ጃንሜዳ/ በመፈራረቅ ይሰጥ በነበረው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት፥ ቀድሞ ከነበሩት አካላት ጋር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት፣ የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ደቀ መዛሙርት ተጨምረዋል። «በ1951 ዓ.ም በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ነበርኩ። ከከተራ እስከ ቃና ዘገሊላ በዓል ድረስ በትምህርት ደረጃቸው ከፍ ያሉ፣ የሥነ ጽሑፍና የቅኔ ተሰጥዎ ያላቸው ደቀ መዛሙርት ከእኛና ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ይመረጣሉ። እነርሱም በአዲስ አበባና ለከተማዋ አቀረብ በኾኑ የገጠር ከተሞች አብሕርተ ምጥማቃት ይሠማራሉ። ቅኔዎቻችንና፣ ግጥሞቻችን፤ የጥያቄና መልስ፣ የድራማና የውይይት መርሐ ግብሮቻችን በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛና በጉራጊኛ ቋንቋዎች የሚተላለፉ ኾነው፡- ጋብቻን፣ የወጣትነት ሕይወትን፣ ሃይማኖትን፣ ባህልን የተመለከቱ ነበሩ። የድምፅ ማጉያ ከፊልፕስ ካምፓኒ፣ ከባህል ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር... በትብብር እየጠየቅን ይሰጠናል። በእውነቱ ዝግጅቶቻችን ለአክብሮ በዓል ብቻ ሳይሆን ወጣቱን ከዘፈንና ከጭፈራ እየሰበሰቡ ለመልካም ማኅበራዊ አባልነትና ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሚያበቁ ነበሩ።» ያሉን ለረጅም ዓመታት በጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የመርሐ ግብር መሪ (Master of Ceremony) ኾነው ያገለገሉት መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን ናቸው።

በዚህ ወቅት ከነበሩት መምህራን መካከል፡- አለቃ ኃይለ ጊዮርጊስ ጀማነህ፣ አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል፣ አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ፣ አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ሊቀ ኅሩያን ልሳነ ወርቅ በዛብህ፣ ቀሲስ /ዛሬ ንቡረ እድ/ ኃይለ ልዑል ወልደ ገሪማ፣ ቀሲስ መክብብ አጥናው፣ ቀሲስ (ዛሬ መልአከ ሰላም ዶክተር) ፣መርዐዊ ተበጀ ፣ ቀሲስ (ዛሬ ዶክተር) ፍሥሐ ጽዮን ካሣዬ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ መልአከ አሚን ዓምደ ብርሃን፣ መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን፣



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



*የመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት መዘምራን በጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት ወረብ ሲያቀርቡ*

መልአከ ታቦር ተሾመ ዘርይሁን፣ ሊቀ ትጉኃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኜ፣ መምህር ታዬ አብርሃም፣ መሪጌታ ተስፋ ጥሩነህ፣ መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ፣ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ....ጥቂቶቹ ናቸው:: የልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ መጽሔት ዋና አዘጋጅ የኾኑት ሊቀ ልሳናት ነቅዐ ጥበብ ወንድም ደግሞ:- በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው፣ በአቶ አእምሮ ወንድማገኘው ይቀርቡ የነበሩቱን ግጥሞች፣ በአቶ አእምሮ ማንደፍሮ ይሰሙ የነበሩትን መዝሙሮች ያስታውሳሉ::

በወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት በኩልም ከተምሮ ማስተማር ማኅበር ሌላ መሠረተ ሃይማኖት ዘታዕካ ነገሥት /የወንዶቹ ማኅበረ በኵር እና የሴቶች ማኅበረ ደናግል በአንድነት/፣ ዓምደ ሃይማኖት ዘመንበረ መንግሥት፣ ማኅበረ ክርስቶስ /የሴቶች/ እና ማኅበረ እስጢፋኖስ /የወንዶች/ ዘመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል.... ወዘተ ተጨምረዋል:: ከእነዚህ መካከል በወቅቱ የደንብ ልብስ /ለምሳሌ:- አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሕብር ያለው ሞጣሕት የመሰለ የነበራቸው የተምሮ ማስተማር ማኅበርና የማኅበረ እስጢፋኖስ ወንዶች መዘምራን ነበሩ:: ሴቶቹ ነጠላ ነበር የሚለብሱት::

በ1960 ዓ.ም የታተመው የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ *«መንፈሳዊነት በልጅነት»* በሚል ርእስ የጻፈው ርእሰ አንቀጽ በጊዜው መንፈሳውያን ማኅበራቱ በባሕረ ጥምቀቱ አገልግሎታቸው የነበሩበትን ሁኔታ፣ ያሳደሩትን ስሜት፣ የደረሱበትን ደረጃና የተጣለባቸውን ተስፋ ያሳያል፤ እንዲያውም «ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በይፋ የታወቀበት ነው» ይለዋል:: እንዲህ ይነበባል:-

*«...በዘንድሮው ዓመት በጃንሆይ ሜዳ በተከበረው የጥምቀት በዓል የሕዝቡን እንተውውና በመንበረ ፓትርያርኩ የስብከት ክፍል ሥር የሚካሄደው፣ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማእከላዊ ጽ/ቤት ያደረገው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ለቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ተስፋ ነው:: ማእከላዊ ጽ/ቤቱ ባወጣው ፕሮግራም መሠረት መንፈሳዊውን ዝግጅት በልዩ ልዩ መልክ አዘጋጅቷል:: ከከተራው ዕለት ጀምሮ እስከ ቃና ዘገሊላ ማለትም ለሦስት ቀናት ያህል የጃንሆይ ሜዳን ሕዝብ በስብከት ሲያፈካ ውሏል:: ስለ ዘፈንና ጭፋሮ ያለውን ሕዝባዊ ስሜት ቀንሶበት ነበር:: ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ያደረጉት እንቅስቃሴ ቀደም ያለ ቢሆንም በይፋ የታወቀው በዘንድሮው ዓመት ነው:: አፈጻጸሙ ቤተ ክርስቲያንን እጅግ በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው:: ወንዶች ወጣቶችና ደናግሉ በኅብረት የቅዳሴ ተሰጥዎ በመቀበል የቀሳውስትንና የዲያቆናትን ግዳጅ በመጠኑ ፈጽመዋል::*

*ሴቶች ሳይቀሩ እንደ ማርያም እኅተ ሙሴ ከበሮውን አንግተው ቸብቸቦውን ሲያቀልጡት የመዘምራኑን ድካም አቃለውላቸዋል::*

*<ወጣቶች ከቤተ ክርስቲያን ርቀዋል> እየተባለ የወሬ ነጎድጓድ በሚነጉድበት ወቅት ይህ ዐይነቱ አማናዊ ድርጊት እንኳን ላላዩት ላዩነውና የሥራው ተካፋይ ለነበርነውም ራእይ ይመስላል:: ሌላው በውስጥ ኹኖ÷ ሮኬቱ፣ ሃይድሮጅኑ፣ ቴሌቪዥኑ በተፈለሰፈበት ዘመን ወይም ማየትና መስማት ተዋሕደው በተገኙበት ሌላውም ዘመን አመጣሽ ባህልና ትርእይት በረከሰበት በዚህ አደናጋሪ ክፍለ ጊዜ ለሦስት ቀን ቀርቶ የወጣቶች በመንፈሳዊ ሥራ ለአንድ ቀን መገኘት በእሳትና በስለት ደምን በማፍሰስ እንደ ተገኘ የረጅም ዘመን ሰማዕትነት ይቆጠራል:: አስተያየታችንን በአንክሮ ብቻ አንጨርሰውም:: ሁለት አስፈላጊዎች ነገሮችን እናሳስባለን:: ....የአንዳንድ ደብር ልጆች ለብቻቸው የቁሪት ድንኳን ተክለው ሲሠሩ ተመልክተናል:: ወጣቶች የመንፈሳዊ ሥራቸው መጀመሪያ ሊያደርጉት የሚገባው መተባበርን ነው:: ይህን ሳደረጉት ለክርሞ እንዳይደገም የማስጠንቀቂያ ምክር ቢሰጣቸው መልካም ነው:: ሁለተኛው አሳሳቢ ጉዳይ ደግሞ ከእንግዲህ ወዲህ ቤተ ክርስቲያን በወጣቶች ለማመካኘት አትችልም:: ....የጊዜውን ሁኔታ በመመልከት ለወጣቶች በሚገባቸው መልክ የሚያስተምሩ ጠለቅ ያለ ችሎታ ያላቸው ወጣቶች መምህራን በብዛት ካልተገኙ፣ የደብር አለቆችም የጊዜውን መንፈስ ተከትለው ካላስተማሩ በወጣቶች በኩል ያለው ደስታ ዘላቂ ሊኾን አይችልም:: ...»*

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በባሕረ ጥምቀቱ ዙርያ በሰንበት ትምህርት ቤቶችና በመንፈሳውያን ማኅበራት የሚዘጋጁ የመንፈሳዊ አገልግሎት እና የምርት ውጤቶች ማስተዋወቂያ ዐውደ ርእዮች፣ ባዛሮች እየተዘወተሩ ናቸው:: በዓሉ ለቀናት የሚቆይና ከተለያዩ ማእዝናት የሚተሙ ሰዎች የሚታደሙበት በመኾኑ ጅምሩ ግንዛቤ ከመፍጠርና መንፈሳዊ ግብይትን ከማጠናከር አኳያ ሊበረታታ የሚገባው ነው::

በ1956 ዓ.ም የአዲስ አበባ ሕዝብ ብዛት 500,000 ያህል እንደ ነበር የሚያስታውሱት መሪጌታ ተስፋ ጥሩነህ:- «ክብረ በዓሉ ከነበረው ድምቀት የተነሣ የእስልምና እምነት ተከታዮች ሳይቀሩ የጥምቀትን በዓል ሥነ ርእይ ለመመልከት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ወደ ጃንሜዳ ይመጡ እንደ ነበር አስታውሳለሁ::» ብለዋል:: በዚያው ዓመት የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ሪፖርተር የነበሩት ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ ደግሞ ለየት ያለ ትዝታ አላቸው:: ወቅቱ ከጉባኤ አፌሶን /431ዓ.ም/ በኋላ የኦርየንታል /ምሥራቅ/ ኦርቶ ዶክሳውያን አብያተ ክርስተያናት ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ጉባኤ ያደረጉበት ነው:: ለስ ምንት ቀናት በዘለቀው ጉባኤ የአምስ ቱም አኀት አብያተ ክርስቲያናት ርእሰ መናብርት /የኪልቂያው አቡነ ኮሬን፣ የመላው አርመን አቡነ ቫስኪን፣ የሕንዱ አቡነ ባስልዮስ፣ የሶርያው አቡነ ያዕቆብ አግናጥዮስ፣ የግብጹ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ የእስክንድርያ መንበረ ማርቆስ ፖፕና የመላው አፍሪቃ ፓትርያርክ፣ የኢትዮጵያው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ተገኝተዋል:: ታድያ አጋጣሚውም የጥምቀት በዓል ሰሞን ነበር:: በባሕረ ጥምቀቱ በተደረገው ጸሎተ ወንጌል:-

ሀ/ ማቴ.3÷1-17... በግእዝ ቋንቋ /የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን/

ለ/ ማር.1÷11... በቅብጥ ቋንቋ /የግብጽ ቤተ ክርስቲያን/

ሐ/ ሉቃ.3÷15-22... በሱርስት ቋንቋ /የሶርያ ቤተ ክርስቲያን/

መ/ ዮሐ.1÷29-40...በአርመንኛ ቋንቋ /የአርመን ቤተ ክርስቲያን/ አድርሰዋል::

### *ቃና ዘገሊላ-የውኃን በዓል ከውኃ*

ጌታ በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ዕለቱን /ማክሰኞ/ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄዷል:: አርባው ቀን ሲፈጸም ወደ አየሩሳሌም ተመልሶአል:: ኢየሩሳሌም የገባው እሑድ ሲኾን፣ በሦስተኛው ቀን /ማክሰኞ/ የገሊላ አውራጃ ክፍል በምትሆን በቃና ሰርግ ተደርጓል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም እና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሰርግ ቤቱ ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ የመጀመሪያውን ተአምር አድርጓል:: ዮሐ.2÷1-12:: ይህ ተአምር የተደረገው የካቲት 23 ቀን /ከጥር 11 ቀን ጀምሮ 43 ቀን ወደፊት ስንቆጥር/ ነው:: አበው «የውኃን በዓል ከውኃ ለማገናኘት» ሲሉ በጥምቀት ማግሥት ጥር 12 ቀን እንዲከበር ወስነዋል:: በዓሉ የሰው፣ የቤተሰብና የኅብረተሰብ መሠረት የኾነው የጋብቻ ክቡርነት የተገለጸበት፣ የጌታችን ቀዳሚ ተአምር የተፈጸመበት ስለሆነ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት እናከብ ረዋለን::

ከ1966 ዓ.ም በፊት የቃና ዘገሊላ በዓል በሚከበርበት ጥር 12 ቀን ማንኛውም ሥራ ዝግ ኾኖ ይውል ነበር:: በዚህ ቀን በባሕረ ጥምቀቱ በዋናነት የሚገኙት ታቦታት የቅዱስ ሚካኤልና ጥር 13 ቀን የሚከበረው የእግዚአብሔር አብ ታቦታት ናቸው:: «በአዲስ አበባ÷ የእግዚአብሔር አብ አብያተ ክርስቲያናት የቅርብ ዘመን (ከ1969 ዓ.ም ወዲህ) ታሪክ ያላቸው ናቸው» ይላሉ መምህር ዐሥራት ደስታ:: የቅዱስ ሚካኤል ታቦት በሚያድርባቸው ቦታዎች ከዋዜማው ጀምሮ ስብሐተ እግዚአብሔር ሲከናወን ያድራል:: በበነጋው እስከ ረፋዱ ድረስ በዓሉን የተመለከተ ትምህርተ ወንጌል ይሰ ጣል:: መዘምራኑ የዕለቱን ስብሐተ እግዚአብሔር ካደረሱ በኋላ ጸሎተ ቡራኬ ተሰጥቶ ታቦቱ ካደረበት ድንኳን ወደ ደብሩ ጉዞ ይጀምራል:: ታቦቱ ከቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረት እንደ ደረሰ መዘምራኑ ለክፍለ ጊዜው የተዘጋጀውን ያሬዳዊ ዝማሬ ያደርሳሉ:: የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች መንፈሳዊ መዝሙር ያቀርቡና ተገቢው ትምህርት ከተሰማ በኋላ ጸሎተ ቡራኬ ተሰጥቶ የበዓሉ አከባበር ፍጻሜ ይሆናል::

የየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት ማደር የጀመረው ከ1939 ዓ.ም አንሥቶ ነው:: ከቦታው ርቀት የተነሣ በጃንሜዳ አራተኛ በር ገብቶ ባሕረ ጥምቀቱ ጋር እስኪደርስ ቀደም ብለው በተለያዩ በሮች የገቡት ሌሎች ታቦታት መጠበቅ ነበረባቸው:: ..... በቃና ዘገሊላ ዕለት ( ጥር 12 ቀን) ታቦቱ ወደ ደብሩ ጉዞ ሲጀምር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ለተወሰነ ርቀት ይሸኛሉ:: ከዚያ በኋላ ተሰናብተው በመኪና ይቀድሙና መንበረ ዳዊቱ /ዙፋኑ/ ተዘርግቶ፣ መድረኩ ተዘጋጅቶ ወደ ሚጠብቃቸው የእንግሊዝ ኤምባሲ ደጃፍ አካባቢ አምርተው በዚያ ታቦቱ እስኪደርስ ቆይታ ያደርጋሉ:: ታቦተ ሚካኤል ከስፍራው ሲደርስ ክቡር ዘበኛው ግራና ቀኝ ተሰልፎ፣ ድባብ ተዘርግቶላቸው አጅበው በቤተ ክርስቲያኑ መግቢያ በር ላይ በሚገኘው የሾላ ዛፍ ሥር /ማርገጃ ላይ/ ቆይታ ይደረጋል:: መዘምራኑ ስብሐተ እግዚአብሔር አድርሰው ትምህርት ይሰጥና ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ያሳርጋሉ:: ታቦቱ ሦስት ጊዜ ዑደት አድርጎ ወደ መቅደሱ ይገባል:: «መላው የአዲስ አበባ ሕዝብ የካ ሚካኤልን ይከተላል» ይላሉ ሊቀ ትጉሃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኜ፤ በዕለቱ ታቦቱን አጅቦ የሚሸኘውን ሕዝብ ብዛት፣የበዓሉን ድምቀት ለመግለጽ::

*ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በባሕረ ጥምቀቱ ዙርያ በሰንበት ትምህርት ቤቶችና በመንፈሳውያን ማኅበራት የሚዘጋጁ የመንፈሳዊ አገልግሎት እና የምርት ውጤቶች ማስተዋወቂያ ዐውደ ርእዮች፣ ባዛሮች እየተዘወተሩ ናቸው::*

### ጃንሆይ ሜዳ እንደ ቅርስ

ቤተ ክርስቲያናችን የጃንሜዳን ባሕረ ጥምቀት አክብራ፣ ባርካ፤ ታቦታቱ በቦታው ላይ ማደር ከጀመሩበት፤ ቅዳሴ፣ ማኅሌት በአጠቃላይ ሥርዐተ ጸሎት ከደረሰበት ጊዜና ሰዓት አንሥቶ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ባሕረ ጥምቀቱ እንደ አንድ ቤተ ክርስቲያን ነበር የሚቆጠረው:: በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ክብካቤ እየተደረገለት በክብር ዘበኛ ይጠበቅ እንደ ነበርም ከታሪክ መዝገብ መረዳት ይቻላል:: ጃንሜዳ ዙሪያውን በአጥር ታጥሮ የተከበረው የክብር ዘበኛ አዛዥ በነበሩት ጀነራል ደበበ ኃይለ ማርያም አማካይነት እንደ ነበር የሊቃውንት ጉባኤው አባል ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ ያስታውሳሉ:: በየዓመቱም ከጥር 10 እስከ 12 ቀን የሚከበሩት በዓለ ጥምቀትና የቃና ዘገሊላ በዓል ከመድረሳቸው በፊት የመንግሥት ድርሻ ጎልቶ የሚታይ ነበር:: ይኸውም በጀት አስቦለት፣ ሐላፊ መድቦለት፣ አስፈላጊውን ሁሉ አሟልቶ፣ ዐጽድቶና አዘጋጅቶ በዓሉን ያስከብር እንደ ነበር መምሬ ተዘራ እና ሊቀ ትጉሃን ገብረ ክርስቶስ አስረድተዋል:: በርግጥም ከጥር 10 ቀን እስከ 12 ቀን ባሉት ቀናት የሚውሉት በዓላት /ከተራ ግማሽ ቀን፣ ጥምቀት፣ ቃና ዘገሊላ/ ክብር ተሰጥቷቸው ማንኛውም ሥራ ዝግ ኾኖባቸው ይውል ነበር::

በአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላን ላይ የጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት ማክበርያ÷ አሁን ያለው ሥፍራ÷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮት ማስፈጸሚያ መኾኑን አረጋግጧል:: ይኸውም በይዞታ ማረጋገጫ ፕላን /7.5/ላይ «ለሥርዐተ አምልኮ የተያዘ ወይም የተፈቀደ» መሆኑን ያስጠ ረዳል:: ከዚህ ጋር በማያያዝ: - «የጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት በአዲስ አበባ ከተማ ከተተከሉት አብያተ ክርስቲያናት እንደ አንዱ ስለሆነ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



*በጃንሜዳ ባሕረ ጥምቀት የሚያድሩ ታቦታት*

በቅርስነት ተመዝግቦ በአስረጅነት ሊጠቀስ እንደ ሚገባው» መምሬ ተዘራ ወርቁና ሊቀ ትጉሃን ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም ይመክራሉ።

### *«ከቤተ መቅደስ ውጪ ያሉ ቤተ መቅደሶቻችን»*

የበዓለ ጥምቀት አከባበር፥ በኢትዮጵያም ይሁን በአዲስ አበባ፥ ሃይማኖታዊ ሥርዐቱንና ትውፊታዊ ወጉን ሳይለቅ ለእኛ እንዲደርስ አባቶቻችንና እናቶቻችን ትልቅ ዋጋ ከፍለዋል። የበዓሉን አከባበር ሥነ ሥርዐት ትውልዱ ከአባቶቹ እና ከእናቶቹ በተግባር፣ በቃልና በመንፈስ አግኝቶታል። ይህ ዋጋ በገንዘብ የሚተመን አይደለም። በጦርነት፣ በረኀብና በድርቅ ውስጥ እየተፈተነ ዛሬ ላይ የደረሰ የሕይወት ዋጋ ነው። በመናፍቃን ቅሰጣና ወረራም ሳይረታ የተከፈለ ብድራት ነው። ስለዚህ በዓልን በደስታና በነጻነት ማዘከር፣ብቻ ሳይሆን የተከፈለውን መሥዋዕትነትና የሕይወት ዋጋ ማሰብ፣ የበረከት ቦታዎችን ማክበር፣ ማስከበርና መጠበቅ ይገባል። ይሁንና አሁን አሁን በበዓለ ጥምቀት ማክበርያ ቦታዎች በአስነዋሪ ተግባሮች የታጀቡ ትዕይንቶችን ማየት እንግዳ ነገር አይደለም። ይህም በበረከት ፈንታ



*«የጥምቀቱ በረከት እኔንም አይለፈኝ»*

መርገምን መሸመት ነው። ሁሉም የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አባልና አካል ሁኔታውን በመከላከል ረገድ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል።

የጥምቀት በዓል ማክበርያዎቻችን *«ከቤተ መቅደስ ውጪ ያሉ ቤተ መቅደሶቻችን»* ስለሆኑ በንጽሕና ልንይዛቸው፣የይዞታቸውን ሕጋዊነትና አስተማማኝነትም በየጊዜው ልናረጋግጥ ይገባል። አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም በዓለ ጥምቀትን ለማክበር በሚያድሩባቸው ቦታዎች በቅንጅት አስበው በጋራ ለልማት ቢንቀሳቀሱ አዎንታዊ ተቀባይነት ይኖራቸዋል። በርግጥም ቦታዎቹን የማልማት እንቅስቃሴ፥ ሐዋርያዊ ዓላማን በማይቃረን፣ ክብረ በዓሉን በማያደናቅፍ መልኩ፥ ቢካሄድ ለሀገራችን ዕድገት የበኩሉን ሚና ሊጫወት ይችላል። እንዲህ በማድረጋችን የአብሕርተ ምጥማቃት ይዞታዎቻችን ጽዳታቸውና ክብራቸው ተጠብቆ የቅርስ ጥበቃ፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ማእከላትም እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምሮ ለሀገራችን ዕድገትና ሥልጣኔ ስታበረክት የኖረችውን አስተዋፅኦም የሚያጠናክር ይሆናል። ለተግባራዊነቱም ምእመናን፣ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰባካ ጉባኤያትና አህጉረ ስብከት የየድርሻቸውን ቢወጡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል። የብርሃነ ጥምቀቱ ጸጋ እና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በታሪክ ጥናት ትልቁ ወንጀል

/ አቶ አበባው አያሌው
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥነ- ትምህርት ኮሌጅ
የታሪክ ትምህርት ክፍል ሐላፊ/

*በሰው ልጅ ረጅም የታሪክ ሂደት ከተፈጠሩት እጅግ ከፍተኛ ክሥተቶች ዋነኛው የክርስትና ሃይማኖት መጀመርና መስፋፋት ነው:: የክርስትና ሃይማኖትን መጀመርና መስፋፋት ተከትሎ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እንደ የሃይማኖት ተቋም ተመሥርታ በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና መጫወት ጀምራለች:: ጥንታዊነትና ያልተቋረጠ ህልውና ካላቸው ቀደምት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንደኛዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ተጨባጭ የታሪክ መረጃዎች እንደ ሚያመለክቱት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ /330 ዓ.ም/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ ሥር የኤጲስ ቆጶስነት መንበር አግኝታለች:: ከዚህ ዘመን አንሥቶ እስካለንበት ዘመን ድረስ በርካታ ችግሮችን ተቋቁማና ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፋ ህልውናዋን በመጠበቅ እልፍ አእላፍ ምእመናንን በማገልገል ኑራለች::*

*ያለንበት ዘመን ባመጣቸው የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የዕድገት ፅንሰ ሐሳቦች የተነሣ ላለፉት አምስት ወይም ስድስት ዐሥርት ዓመታት በርካታ ሂሶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ በመሰንዘር ላይ ይገኛሉ:: ሂሱን የሚሰነዝሩ ወገኖች በአብዛኛው የሀገር ውስጥና የውጭ ምሁራን ናቸው:: እነዚህ ወገኖች ቤተ ክርስቲያኗን ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ መቆርቆዝና ለዕድገቷ መጓተት ግንባር ቀደም ተወቃሽ ያደርጓታል:: ባሳለፍነው ዓመት ክረምት ወራት ግን መንግሥት እና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በኀትመትና በሕዝባዊ መድረክ ባለፉት ዘመናት ለተፈጠሩት በርካታ አስተዳደራዊ፣ ፖለቲካዊና ልማታዊ ችግሮች በቀጥታ ቤተ ክርስቲያኗን ተወቃሽ አድርገዋል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንድ ራሷን የቻለች ተቋም ሳይሆን የዘውዳዊ አገዛዝ ሥርዐት ዋነኛ ተቀጽላ አድርገው በማያወላውል ሁኔታ ፈርጀዋታል:: ይህ ታድያ ታሪካዊ ሐቅ ወይስ መሠረት አልባ የፖለቲካ ቅስቀሳና አስተሳሰብ ነው ወይ? የሚለው የብዙ ኢትዮጵያውያን በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ጥያቄ መሆኑ ርግጥ ነው:: እኔንም እንደ አንድ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ ምእመን ብዕሬን አንሥቼ ይህችን አጭር ጽሑፍ እንድጽፍ ያስገደደኝ ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ነው::*

*ባለፈው ክረምት መገባደጃና በያዝነው ዓመት መባቻ አካባቢ የወጡትን የግል ጋዜጦች አንብቤ ነገሩን የአንድ ሳምንት የፖለቲካ ወሬ ነው በሚል ችላ ብየው ነበር:: ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰው ወቀሳ በሐመር መጽሔት ትኩረት ተሰጥቶት ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ከፍተኛ የመንግሥት ባለ ሥልጣን /ክቡር አቶ ተፈራ ዋልዋ/ ከዝግጅት ክፍሉ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ አንብቤያለሁ:: እኔስ ለምን አስተዋፅኦ አላደርግም በማለት እነሆ የሚከተለውን አንተያየቴን አቅርቤያለሁ::*

## እውነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወይም መሪዎቿ የአገሪቱ መሬት ሲሶ /አንድ ሦስተኛ/ ባለቤት ነበረች /ነበሩ/?

ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያለው የመሬት ሥሪት /Land Tenure/ ሥርዐት ባለቤት ናት:: የኢትዮጵያ የመሬት ሥሪት ሥርዐት ከሁለት ዐበይት ነገሮች ጋር የተፈጠረና የተያያዘ ነው:: አንደኛው ከእርሻ መጀመርና መዳበር ጋር በቀጥታ ይያያዛል:: ይህ ዐይነቱ የመሬት ሥሪት ርስት የምንለው ነው:: ሁለተኛው የመሬት ሥሪት ሥርዓት በኢትዮጵያ ከመንግሥት መመሥረትና መስፋፋት ጋር የተሳሰረ ነው:: ከዚህ ታሪካዊ ሂደት ጋር የተያያዘው የመሬት ሥሪት ጉልት የምንለው ነው:: እነዚህ ሁለቱ የመሬት ሥሪት ሥርዐቶች ከቀደመው ዘመን ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ምንም ዓይነት ለውጥና መሻሻል ሳይደረግባቸው ቆይተዋል:: ከነዚህ ከሁለቱ የመሬት ሥሪት ሥርዓቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተጠቃሚ የነበረችው *በጉልት ሥሪት* ነው::

ጉልት የመሬት ባለቤትነት መብት ሳይሆን በተወሰነ መሬት ላይ ሰፍረው ከሚገኙ ባላገሮች ወይም አራሽ ገበሬዎች ግብር በዐይነት ወይም በገንዘብ የመሰብሰብ መብት ነው:: በኢትዮጵያ የተለያየ ክፍል የተመሠረቱና ጠንክረው የወጡ መንግሥታት ከቅድመ አክሱም ጊዜ ጀምሮ ከዜጎቻቸው ግብር የሚሰበስቡት *በጉልት ሥሪት* ነው:: ንጉሠ ነገሥቱ ወይም የመንግሥቱ ቁንጮ የሆነው ገዢ በሥሩ ላሉት የተለያየ ደረጃ ላላቸው ሹማምንት እንዲያደራጃቸው ሹመታቸው የተለያየ መጠን /ስፋት/ ያለው መሬት በጉልትነት ይሰጣቸዋል:: እነዚህ ሹማምንት ለመንግሥት ወይም ለንጉሠ ነገሥቱ /ገዥው/ ለሚያበረክቱት አስተዳደራዊና ወታደራዊ አገልግሎት የሚያገኙት ደመወዝ ወይም መተዳደኒያቸው ከጉልታቸው ሰፋሪዎች የሚሰበስቡት ግብር ነው:: ከሚሰበስቡት ግብር ገሚሱን ለራሳቸው መተዳደሪያ አስቀርተው ገሚሱን ከእነርሱ የበላይ ለሆኑው ሹም ያስተላልፋሉ:: በዚህ ዐይነት ከተራ ወታደር እስከ ራሶችና ራስ ቢትወደዶች የተለያየ መጠን ያለው ጉልት አላቸው:: በዚህ መልኩ ጉልት በኢትዮጵያ በቅድመ አብዮት ጊዜ



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ለነበሩ መንግሥታት የምጣኔ ሀብት መሠረት ነበር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ የሃይማኖት ተቋምነቷ ከመንግሥት ሹማምንት ቀጥላ ዋነኛ የጉልት ተጠቃሚ ነበረች። በተለያዩ ዘመናት ነገሥታት፣ ታላላቅ መሳፍንት እና መኳንንት የተለያየ መጠን ያላቸውን ጉልቶች ለገዳማትና ለአድባራት ለግሠዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ በሺሕ የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ባለጉልት የነበሩት በጣም ጥቂቶች ናቸው። ነገሥታቱና መሣፍንቱ ለቤተ ክርስቲያን ጉልት የሚሰጡበት እንዲሁ በዘፈቀደ አይደለም። አንድ ገዳም ወይም ቤተ ክርስቲያን ጉልት የሚሰጠው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሁሉም ሊሆን ይችላል።

1ኛ. ደረጃውን ከገጠር ቤተ ክርስቲያንነት ወደ ገዳም ወይም ደብር በተለያየ ምክንያት ማሳደግ ሲፈለግ፤

2ኛ. የክርስትና ትምህርት ማእከል ለሆኑ የታወቁ አብያተ ክርስቲያናት መምህራኑና ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መተዳደሪያ ይሆን ዘንድ፤

3ኛ. ነገሥታቱ ወይም መሣፍንቱ ስእለት ተስለው የሠመረላቸው ከሆነ የተወለዱበት ወይም ክርስትና የተነሡበት ወዘተ .... ቤተ ክርስቲያን የሆነ እንደ ሆነ የሚሉት ናቸው።

እንግዲህ እነዚህን በመሳሰሉ ምክንያቶች ነገሥታቱና መሣፍንቱ ጉልት ለቤተ ክርስቲያን ሲሰጡ ኑረዋል። ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ ጉልት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጉልት አይደለም። ጉልት ለአንድ ቤተ ክርስቲያን በሚሰጥበት ጊዜ *«ሥርዐተ ደብር»* አብሮ ይወጣል። «ሥርዐተ ደብር» የምንለው የቤተ ክርስቲያኗን የውስጥ አስተዳደራዊ መዋቅርና የቤተ ክርስቲያኗን ጉልት መሬት ክፍፍል በዝርዝር የያዘ ሰነድ ነው። አንድ ቤተ ክርስቲያን ትንሽም ሆነ ትልቅ ጉልት ሲሰጠው የአገልጋዮችና የደብተሮች ብዛት ይጨምራል። በመሆኑም የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ከአለቃው ጀምሮ እስከ ዲያቆንና ዐቃቢት ድረስ በተዋረድ በቤተ ክርስቲያኗ ቦታ ይሰጣቸዋል። በዚህ መሠረት እንደየ አገልግሎት ቦታቸው ከቤተ ክርስቲያኗ ጉልት እየተከፈለ መሬት ይሰጣቸዋል። ይህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለአገልግሎት የሚሰጣቸው መሬት *ሪም* ይባላል። በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በተሰጣቸው ሪም ላይ ከሚኖሩ ዜጎች ዓመታዊ ምርት /እህል ብቻ ነው/ ሲሶውን ለመተዳደሪያቸው ይቀበላሉ። ከእህል ምርት ውጪ አሞሌ ጨው፣ የበግ ጠቦት፣ ቅቤ፣ ማር፣ ወዘተ... መውሰድ አይችሉም። ነገር ግን እንደ አለቃ፣ ሊቀ ጠበብት፣ ርእሰ ደብር፣ ቄሰ ገበዝ የመሳሰሉት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያኑ ካህናት በዓመት ሁለት ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜ በሪማቸው ውስጥ ከሚኖሩ ዜጐች አንድ የበግ ጠቦት፣ ከ10 የማይበልጥ አሞሌ ጨው ይቀበላሉ። ይህንም መቀበል የሚችሉት በሥርዐተ ደብሩ ከተደነገገ ብቻ ነው።

ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ጉልት ሙሉ በሙሉ ለአገልጋዮቿ በሪም መልክ ተከፋፍሎ አይሰጥም። ከጉልቱ የተወሰነው ተቀንሶ እንደ ዕጣን፣ ጧፍ እና የመሥዋዕት ስንዴ ያሉ ለቤተ ክርስቲያኗ የዕለት ተዕለት ቅዳሴና ሌሎች ተግባሮች ይውላል። በዚህም የተነሣ የጧፍ መሬት፣ የዕጣን መሬት እና የመሥዋዕት መሬት /አጊር የሚባሉ ቦታዎች/ መሬቶች በሥርዐተ ደብሩ ተለይተው ይቀመጣሉ። በእነዚህ መሬቶች ላይ የሚኖሩ ባላገሮች /ዜጎች/ ግዴታቸው የቤተ ክርስቲያኗን የዓመት መሥዋዕት /ጧፍ፣ ዕጣን፣ እና የመሥዋዕት ስንዴ/ መስጠት ነው። ለምሳሌ፡ - በጧፍ መሬት የሚኖሩ ባላገሮች በጋራ ለጧፍ መግዣ የሚያገለግል አሞሌ ጨው ወይም ገንዘብ አምጥተው ይሰጣሉ። ከዚህ ውጭ በዐይነትም ሆነ በገንዘብ የሚከፍሉት ምንም ዓይነት ክፍያ የለም።

አንድ የተወሰነ አገር ወይም መሬት ለቤተ ክርስቲያን በጉልትነት ሲሰጥ ቤተ ክርስቲያኗ በጉልቱ ላይ የሚኖሩትን ዜጎች የማስተዳደር ግዴታ አብሮ ይሰጣታል። በመሆኑም የአስተዳደር ሥነ ሥርዐቱ በሥርዐተ ደብሩ በጥንቃቄ ይቀመጣል። በአብዛኛው ሪም የተሰጠው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በሪሙ ላይ የሰፈሩትን ባላገሮች ያስተዳድራል። በተለያዩ ወንጀሎች እና ጉዳዮች ላይ ፍርድ ይሰጣል። ነገር ግን እንደ ነፍስ ማጥፋት፣ ከፍተኛ ስርቆትና የመሳሰሉት ወንጀሎች ሲፈጸሙ ፍርድ የሚሰጠው የደብሩ አለቃ ነው። ፍርዱም የሚሰጠው በጉባኤ ነው። ዜጎች ወይም ባላገሮች በባለሪሙ በደል ሲደርስባቸውም ለሊቀ ጠበብቱ፣ ርእሰ ደብሩ ወይም ለአለቃው አቤቱታ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ እና ሌሎች ጥቃቅን የአስተዳደር ጉዳዮች በሥርዐተ ደብሩ በዝርዝር ይቀመጣሉ። ይህም በመሆኑ በቤተ ክርስቲያን ጉልት ሥር የሚኖሩ ባላገሮች /ዜጎች/ በቀጥታ በመንግሥት አገልጋይ ጉልት ከሚኖሩ ባላገሮች /ዜጎች/ እጅግ የተሻለ መብትና ጥቅም አላቸው።

ለዚህ ትልቁ ምክንያት ሥርዐተ ደብሩ እንደ መተዳደሪያ ደንብ ሁኖ ከብዙ በደልና ጭቆና ስለሚከላከላቸው ነው። በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን ጉልት የሚኖሩ ዜጎች የሚከፍሉት ግብር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። ባለሪም የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንደ መንግሥት ሹመኞች ወይም ባለጉልቶች ባላገሩን እንደ ፈለጉና እንዳሰኛቸው ግብርና ጥቅም መጠየቅ አይችሉም። በተለይም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ጉልት የሚኖሩ ዜጎች ከውትድርና አገልግሎት በአብዛኛው ነጻ ናቸው። ብዙ ጊዜ ባላገሮች መሬታቸው ለቤተ ክርስቲያን ጉልት ሆኖ ሲሰጥ ትልቅ እፎይታን ያገኛሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና አገልጋዮች በሁለት መልኩ ሊታዩ ይችላሉ። ይህ አከፋፈል ሁለት ገጽታ አለው። አንደኛው ከቤተ ክርስቲያኑ ደረጃ አኳያ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከካህናቱ የግል ውሳኔና ኑሮ አኳያ ነው። ከቤተ ክርስቲያኑ ደረጃ አኳያ ያየን እንደ ሆነ ሁለት የተለያዩ የካህናት ቡድን እናገኛለን። አንደኛው የገጠር ቤተ ክርስቲያኖችን የሚያገለግሉ ካህናትና በደብር ወይም የጉልት መሬት ባላቸው ገዳማት የሚያገለግሉ ካህናትና መነኮሳት ናቸው። በገጠር ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ካህናት ምንም ዓይነት ጥቅም አያገኙም። ለአገልግሎታቸው ዋጋ ጉልት ወይም የተለየ ጥቅማ ጥቅም አይሰጣቸውም። ይህም የሚሆነው የገጠር ቤተ ክርስቲያን ለመሥዋዕት ስንዴ፣ ለጧፍ፣ ለዕጣን፣ ወዘተ.... የሚሆን መሬት ስላለው ነው። በርግጥ ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ይብዛም ይነስም የመሬት ባለቤት ነው። ይሁንና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ያላቸው የመሬት ይዞታ እጅግ በጣም ትንሽ ነው። የቤተ ክርስቲያኑን የዕለት ተዕለት ተግባር ለማከናወን ይቅርና ከካህናቱ አንዱ የሚሰጠውን የሃይማኖታዊ የአገልግሎት ዋጋ የሚሸፍን አይደለም።

የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ካህናትን የሚያስመሰግነው ግን ምንም የጉልትና የግብር ጥቅም ሳይሰጣቸው በዜግነታቸው በርስት ባለቤትነት የያዙትን መሬት በራሳቸው ጉልበትና ጊዜ እያረሱ፣





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

እየጎለጐሉ፣ እያረሙ፣ እያጨዱ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የቤተ ክርስቲያንን መደበኛ አገልግሎት ማከናወናቸው ነው:: በአንክሮ ላስተዋለው የእነዚህ ካህናትና ዲያቆናት አገልግሎት እና አስተዋፅኦ ከታላላቆቹ ጳጳሳትና ሊቃነ ካህናት በእጥፍ ይበልጣል:: ምክንያቱም ራሳቸውን አንቅተውና አትግተው ተነሥተው ኪዳኑንና ቅዳሴውን ሌላም ምእመናን የሚያስፈልጋቸውን የክርስትና፣ የቁርባን ወዘተ... መንፈሳዊ አገልግሎቶች ሰጥተው ረፋድ ላይ ደግሞ በሬ ጠምደው፣ እርፍ ጨብጠው የርስት መሬታቸውን እያረሱ የግል ሕይወታቸውን ባማረ ሁኔታ መምራታቸው ነው::

ከላይ እንደ ተመለከትነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጉልት ባለቤት ነበረች:: ነገር ግን ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የተጎለተው መሬት በጥቅሉ ቢሰላ እንኳ የአገሪቱን መሬት አምስት በመቶ አይሆንም:: በተለምዶ እና በአፈ ታሪክ ግን የሲሶ መሬት ባለመብት ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሆነች በስፋት ይነገራል:: ይህ አፈ ታሪክና አባባል ምንጩ ሁለት ነው:: አንደኛው በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ሦስት የኅብረተሰብ ክፍሎች ለረጅም ጊዜ ኖረዋል:: እነዚህም ገበሬው፣ ካህናቱና ወታደሩ ናቸው::

ገበሬው የኅብረተሰብ ክፍል ሁሉንም በእርሻ የተሠማራ ዜጋ አቅፎ ይይዛል:: የካህናቱ ወገን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የተሠማራውን ዜጋ በጥቅሉ ይይዛል:: የወታደሩ የኅብረተሰብ ክፍል ደግሞ ከተራው ወታደር ጀምሮ እስከ ራስ እና ራስ ቢትወደድ ደረጃ የደረሱትንና በመንግሥት አስተዳደር ያሉትን ዜጐች ይጨምራል:: በተለይም የገበሬው ወገን አራሽ፣ የወታደሩ ክፍል አንጋሽ፣ የካህናቱ ቤተሰብ ደግሞ አወዳሽ /ቀዳሽ/ ተብለው ይጠራሉ:: እንደ ኢትዮጵያ ባለ አገር እንኳንስ ድሮና አሁንም ቢሆን ትልቁ ሀብት መሬት ነው:: እነዚህ ሦስቱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከመሬቱ የየራሳቸውን ድርሻ ይፈልጋሉ:: በመሆኑም በንጉሠ ነገሥቱ ሥር ያለውን መሬት:- «ሲሶ ለአራሽ፣ ሲሶ ለአንጋሽ፣ ሲሶ ለአወዳሽ /ቀዳሽ/ ነው» የሚል የተለምደ አባባል አለ:: ነገር ግን ይህ በተግባር ተተርጉሞ÷ ስቱም የኅብረተሰብ ክፍሎች መሬቱን እኩል ለሦስት የተከፋ ፈሉበት ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ፈጽሞ የለም::

*ሁለተኛው ምንጭ÷ በዐሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ በዛግዌ እና ሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥቶች መካከል በነበረው የሥልጣን ሽኩቻ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሁለቱን ተቃራኒ ወገኖች በማስማማት፣ ዘውድ ከዛግዌ ሥርወ መንግሥት ወደ ሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት በሰላም እንዲ ተላለፍ አድርገዋል:: አስቀድሞ ቃል በገባላቸው መሠረት ዐፄ ይኩኖ አምላክ ሲሶውን /1/3ኛውን/ የግዛታቸውን ክፍል ለቤተ ክርስቲያን ሰጥ ቷቸዋል»* የሚለው አፈ ታሪክ ነው::

ዘውድ ወደ ሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት የተላለፈው በሰላም ሳይሆን ደም ባፋሰሰ ግጭት ነው:: ዐፄ ይኩኖ አምላክም «ሲሶውን የግዛቴን ክፍል ለቤተ ክርስቲያን እሰጣለሁ» ለማለታቸው ምንም የታሪክ ምንጭና ማስረጃ የለም:: ዘውድ ጭነው ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላም እንደ ማንኛውም ንጉሠ ነገሥት ጉልት በመጎለት እና ሕንፃ በማሳነጽ ቤተ ክርስቲያንን ደገፉ እንጂ ከግዛታቸው ሲሶውን ለቤተ ክርስቲያን አልሰጡም:: በእነዚህ በሁለቱ ተለምዶአዊ አነጋገሮችና አፈ ታሪኮች የተነሣ ለዘመናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአገሪቱ መሬት ሲሶ ባለቤት ተደርጋ ስትጠቀስ ኖራለች::



*ጻድቁና ጠቢቡ ንጉሥ ላልይበላ*

ታሪካዊ እውነታው ግን ቤተ ክርስቲያኗ መሬት በጉልትነት ይዛ ኖራለች፤ ነገር ግን ይህ በጭራሽ የአገሪቱን ሲሶ መሬት አይደለም:: የቤተ ክርስቲያን የመሬት ባለቤት መሆን ደግሞ በኢትዮጵያ ብቻ የተፈጠረ ክሥተት አይደለም:: በአውሮፓ ክርስትና የሮማውያን ግዛተ መንግሥት ሃይማኖት ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የሮም ካቶሊክን ጨምሮ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት የመሬት ባለቤቶች ነበሩ:: መሬቱንም የሚለግሡት ልክ እንደ ኢትዮጵያ ነገሥታት መሣፍንቱና መኳንንቱ ናቸው:: የመሬት ይዞታቸውን እስከ አሁን ጠብቀው ያቆዩ አሉ:: እንዲሁም በተለያየ ታሪካዊ አጋጣሚ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ መሬታቸውን ተነጥቀው ባዶ እጃቸውን የቀሩም በርካቶች አሉ::

ነገሥታቱና መሣፍንቱ መሬት ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለመሪዎቿ ይሰጡ የነበሩት «የነፍጠኛው ሥር ዐት ቁንጮዎች በእግዚአብሔር የተ ሠየሙ:- ለእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ለማንም ተጠያቂ እንዳል ሆኑና መሆንም እንደማይገባቸው ለማሳመን ነውን?

በመጀመሪያ «የነፍጠኛው ሥርዐት ቁንጮዎች» እነማን ናቸው? «ነፍጠኛ» የሚለውን በኋላ እንመለስበታለን:: የዘውዳዊው መንግሥት ሥርዐት ቁንጮ የነበሩት ግን ንጉሠ ነገሥታቱ ናቸው:: በተለያዩ ጊዜያት የነገሡ የኢትያጵያ ንጉሠ ነገሥታት ራሳቸውን በእግዚአብሔር የተመረጡ ወይም «ሥዩመ እግዚአብሔር» አድርገው መቁጠራቸው የማይታበል ታሪካዊ ሐቅ ነው:: በአንድ በኩል የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ነገሥታት የዘር ሐረጋቸው "ከእስራኤል ነገሥታት ከዳዊትና ከሰሎሞን በቀጥታ የተያያዘ ነው" ብለው ያምናሉ:: ይህ እውነት ነው ወይስ ሐሰት ÷ ምንም ማረጋገጫ የለውም:: ነገር ግን ኢትዮጵያ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ከግብጽ እና ከእስራኤል ጋር ግንኙነት እንዳላት ይታወቃል:: ከዚህ ግንኙነት በመነሣት ምን አልባት የሰሎ ሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ነገሥታት ከእስራኤል ነገሥታት የዘር ሐረግ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል ለማለት ያስደፍራል:: በተጨማሪም በክብረ ነገሥት መጽሐፍ ላይ ቀጥ ተኛ የዘር ሐረግ ግንኙነት እንዳ ላቸው በዝርዝር ሰፍሯል:: ክብረ ነገ ሥት በኢትዮጵያ የክርስቲያኑ መንግ ሥት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታና ሚና የነበረው መጽሐፍ ነው:: በዚህ መጽሐፍ ላይ ያለውን የታሪክ ትን



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ታኔና መረጃ በደፈናው ውሸት ነው ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል::
በእኔ በኩል ከክብረ ነገሥት እና ኢትዮጵያ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ከእስራኤል ጋር ካላት ግንኙነት በመነሣት የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ነገሥታት ከእስራኤል ነገሥታት ጋር ቀጥተኛም ባይሆን የዘር ሐረግ ግንኙነት አላቸው እላለሁ:: ይህ ከሆነ ደግሞ በቅዱስ መጽሐፍ ላይ እንደ ተቀመጠው ቅዱስ ዳዊትን እግዚአብሔር ነው መርጦ ያነገሠው:: ክርስቶስም የተወለደው ከዳዊት ዘር ነው:: የዳዊትንም ዘር እግዚአብሔር መርጦታል:: የኢትዮጵያ ነገሥታት በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ የሚያምኑ ክርስቲያኖች እስከ ሆኑ ድረስ ራሳቸውን «ሥዩመ እግዚአብሔር» ብለው መቁጠራቸው ስሕተት አይሆንም::



*ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ*

በዚህ መንደርደሪያ ወደ ዋናው ነጥብ ስንመለስ የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ነገሥታት መሬት ለቤተ ክርስቲያን የሚጒልቱት ካህናቱ «ሥዩመ እዚአብሔርነታቸውን» ለሕዝቡ እንዲሰብኩላቸው አይደለም:: አስቀድሞ በተጠቀሱ ሦስት ምክንያቶች ለቤተ ክርስቲያን ጒልት በስጦታ ያበረክቱ ነበር:: ከሦስቱ በተጨማሪ ነገሥታቱ ለቤተ ክርስቲያን መሬት በጒልትነት ሲሰጡ የነበሩባቸው ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ:: አንደኛው ቤተ ክርስቲያን የሕዝብ አገልጋይ እና ለሕዝብ የቆመች ተቋም ናት:: ለክርስቲያኑ ምእመን የተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ትሰጣለች:: ከእነዚህም መካከል ጋብቻ፣ ጥምቀት፣ ጸሎት፣ ፍትሐት... ወዘተ ይገኛሉ:: በክርስቲያኑ ሕዝብ ማኅበራዊ ሕይወትም ቤተ ክርስቲያን የተጣላን በማሠታረቅ፣ ግለሰብንም ይሁን ማኅበረሰብ የሚበድልን በመገሰጽ በአጠቃላይ ክርስቲያኑ ሕዝብ ሰላማዊ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲኖረው ትሠራለች፤ ስትሠራም ኖራለች::

በትምህርት ዘርፍም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ትምህርት እንደ አሁኑ ሳይስፋፋ ፍላጎቱ ላላቸው ወገኖች ሁሉ ማንበብና መጻፍ፣ ሥነ ሥዕልና ሌሎችንም ጥበባት ስታስተምር ኖራለች:: ለንጉሠ ነገሥቱና በሥሩ ላሉ ሹማምንት ከደብዳቤ ጀምሮ ማንኛውንም የጽሕፈት አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ የቤተ ክርስቲያን ውጤት የሆኑ የተማሩ ግለሰቦች ወይም ካህናት ራሳቸው ናቸው:: ለነዚህ ሁሉ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ መተዳደሪያ ሊኖራት የግድ ነው:: ይህም በመሆኑ ነገሥታቱና መሳፍንቱ ለአገልግሎቷ ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ መሬት በመጒለት ረድተዋታል:: የቤተ ክርስቲያኗ መኖርና አገልግሎት መስጠት ለነገሥታቱና ለሕዝቡ እጅግ አስፈላጊ ነበር::

በሌላ በኩል የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ነገሥታት እጅግ ክርስቲያን እና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ነበሩ:: መቼም ቢሆን ሃይማኖት እና እምነት ከሌለው መሪ ይልቅ ክርስቲያንም ይሁን ሙስሊም ሃይማኖት ያለውና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት መሪ ለሕዝብና ለሀገር ጠቃሚ ነው:: በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ነገሥታት ጥሩ ነበሩ:: እጅግ ክርስቲያን ከመሆናቸው የተነሣም ማንኛውም ክርስቲያን ምእመን ለዘላለማዊ ሕይወቱና ለነፍሱ እንዲሁም ለኀሊናውና ለመንፈሱ እርካታ የተለያየ አስተዋፅኦና መባ ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሚሰጠው ሁሉ ባላቸው ሀብት እና ገንዘብ መጠን ለቤተ ክርስቲያን መሬት ሰጥተዋል:: መሬት ብቻ ሳይሆን አልባሳትን፣ ንዋየ ቅድሳትን፣ ምንጣፎችን ወዘተ... ይሰጣሉ:: አብዛኛዎቹ ነገሥታት ዘውዳቸውን፣ ልብሰ መንግሥታቸውን፣ ጋሻቸውን፣ ሾተላቸውን፣ ጦራቸውን፣ የፈረስና የበቅሎ ዕቃቸውን፣ ድባባቸውን ለቤተ ክርስቲያን በስጦታ መልክ ሰጥተዋል:: ብዙውን ጊዜም መጽሐፍ አስጽፈው፣ ሥዕል ዐሥለው ያበረክታሉ:: ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንም በማሠራት የመቅደሱን ግድግዳ ላይ ዐሥለው፣ የቅጥሩን እድሞ አስክበው ወይም አስገንብተው ለስማቸው ማዘከርያ እንዲሆን ያደርጋሉ::

ነገሥታቱ ክርስቲያን በመሆናቸውና ከልጅነት ጀምሮ በክርስትና ትምህርት ታንፀው በማደጋቸው ከላይ የተጠቀሱትን አስተዋፅኦዎች ለቤተ ክርስቲያን ማድረጋቸው ወገናዊ ናቸው አሰኝቶ አያስወቅሳቸውም:: ይልቅስ ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን ከሚገባው በላይ በመወጣታቸው እጅግ ሊመሰገኑበት ይገባል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት ምእመናኑም ጭምር ነገሥታቱን የሚወዱበት፣ የሚያመሰግኑበትና የሚፈሩበት ምክንያቱም ይህ ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን ለጥቅም ነገሥታቱ «ሥዩም እግዚአብሔር» ናቸው ብላ አልሰበከችም::

ቤተ ክርስቲያን በርግጥ የተቀባ ንጉሥ ሁሉ "ሥዩመ እግዚአብሔር ነው" ብላ ታምናለች:: ይህ ደግሞ ትክክል ነው:: ነገሥታቱም ከላይ እንደ ተጠቀሰው «ሥዩመ እግዚአብሔር ነን» ብለው ያምናሉ:: ለዚህ ጥሩ ማስረጃ በዐፄ ቴዎድሮስ ጊዜ በንጉሠ ነገሥቱና በካህናቱ መካከል ጎንደር ላይ የተደረገው ክርክር ነው:: አለቃ ዘነብ ጽፈውት ኢኖ ሊትማን /Enno Littmann/ በ1902 ዓ.ም እ.ኤ.አ ባሳተሙት የዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ገጽ 28 የሚከተለው ይነበባል:-

*«... ንጉሡ ካህናቱን ጥምጥም ጠምጥመው እንዳይቀርቡ ከፊትዎ ከልክለው ነበርና ካህናቱም ጥምጥም ክብራችን ነውና ይበይኑልን አሉ:: ንጉሥ ቴዎድሮስም መለሱ፤ አሉም:*
*- ከታቦት በገባችሁ ጊዜ ስለምን ጥምጥማችሁን ታወልቃላችሁ? አሏቸው:: ካህናቱም እግዚአብሔር አድሮበታልና ብለን ነው አሉ:: ንጉሡም በእኔ እግዚአብሔር አላደረብኝም፤ እግዚአብሔር በ'ኔ አድሮ አይደለም የሚገዛ፤ ባሉ ጊዜ ካህናቱም አዎን አሉ::"*

ሁለቱም ወገኖች በንጉሠ ነገሥቱ «ሥዩመ እግዚአብሔር» መሆን ላይ ቢስማሙም ተቀብቶ ነግሦ «ሥዩመ እግዚአብሔር» የተባለ ንጉሥ ሁሉ መጥፎ ሥራ አይሠራም:- ሕዝብ አይበድልም ማለት አይደለም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ጊዜያት ሕዝብ የበደሉቱን፣ ድኾችን ያስለቀሱትን ነገሥታትን እና መሳፍንትን ስታወግዝና ስትገሥጽ ትኖራለች:: ካህናቱና ታላላቅ የቤተ




© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ክርስቲያኗ መሪዎችም እንዲሁ።

ከሁሉም የበለጠ ሊታወቅ የሚገባው ታሪካዊ ሐቅ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችው ክርስትናን ለማስፋፋት፣ ወንጌልን ለመስበክ ነው እንጂ ንጉሥ እየቀባች በማንገሥ "እግዚአብሔር የሾመው ነውና ስጥ ለጥ ብላችሁ ተገዙለት" ለማለት አይደለም። በእርግጥ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት በመሆኑ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ሁለቱም ከየራሳቸው ዓላማ በመነሣት ሲደጋገፉ ቆይተዋል። የዚህ አንዱ መገለጫ መንግሥስት ግዛት በማስፋፋት በሚያደርገው ሂደት ቤተ ክርስቲያኗ ክርስትናን ማስፋፋቷና በተገባቢጦሹ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗ መነኮሳትና ካህናት ክርስትናን በተስፋፋባቸው አካባቢዎች መንግሥት ግዛቱንና ሥልጣኑን ማስፋፋቱ ነው። እንዲህ ዓይነት እርስ በርስ የመደጋገፍ ሁኔታ በሁለቱ መካከል ቢኖርም ላለፉት 1600 ዓመታት ቤተ ክርስቲያኗ ትልቁና ዋነኛ ተግባሯ ክርስትናን በሐዋርያዊ ተልእኮ (Apostolic Missions) ማስፋፋት ነበር። በዚህም ደግሞ ከፍተኛ ስኬት አሳይታለች። ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን በኢትዮጵያ ምድር ብቻ ሳይሆን በአውሮፓ፣ በካሪቢያን፣ በሰሜን አሜሪካና ሌሎችም የዓለማችን ክፍሎች አስፋፍታለች። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያውያን ትልቅ ኩራትና የመንፈስ እርካታ ነው።

*«ቀድሞ ይኽ ሃይማኖት /ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ/ «የመንግሥት ነው» ተብሎ ስለ ነበር የፖለቲካ ሥርዓቱ በሕዝብ ላይ በደል ሲያደርስ ወደድንም ጠላንም የመንግሥት ሃይማኖት የተባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አብሮ ተጠያቂ ነው የሚደረገው።»*

**[አቶ ተፈራ ዋልዋ ለሐመር መጽሔት የሰጡት ቃለ ምልልስ፣ ሐመር 13ኛ ዓመት ቁጥር 6፣ ገጽ 10/።**

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሕዝብ ላይ ያደረሰችው በደል አለን?

ይህ ጥያቄ ሲነሣ በብዛት አብሮ የሚነሣው «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የተለያዩ ሕዝቦችንና ማኅበረሰቦችን በማስገደድ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን እንዲቀበሉና እንዲከተሉ አድርጋለች» የሚለው ወቀሳ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ1600 ዓመት ታሪኳ ማንኛውንም የኅብረተሰብ ክፍል እና ሕዝብ በግዴታ ክርስትናን እንዲቀበሉ ያደረገችበት ጊዜ የለም። እንዲያውም በተቃራኒው የተለያዩ ሕዝቦች ክርስቲያን እንሁን፣ በክርስትና ሃይማኖት የሚያጠምቀንና ክርስትናን የሚያስተምሩን ካህናት ላኩልን» በማለት ለነገሥታቱና ለቤተ ክርስቲያን አባቶች ይልኩ ነበር። ከነዚህም መካከል ብንወስድ በ1554 ዓ.ም ገደማ በቢዛሞ ይኖሩ የነበሩ የሺናሻ ሕዝቦች ለክርስቲያኑ መንግሥት ሹማምንትና ለንጉሠ ነገሥቱ /ዐፄ ገላውዴዎስ/ በተደጋጋሚ ክርስትናን ለመቀበል እንደ ሚፈልጉና ካህናትን እንዲልኩላቸው መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ተማፅነዋል። ነገር ግን በወቅቱ ክርስቲያኑ መንግሥት /የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት/ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በነበረባቸው ከፍተኛ ውጥረት ካህናት ወደ ቢዛም መላክ አልቻሉም።

***የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ1600 ዓመት ታሪኳ ማንኛውንም የኅብረተሰብ ክፍል እና ሕዝብ በግዴታ ክርስትናን እንዲቀበሉ ያደረገችበት ጊዜ የለም። እንዲያውም በተቃራኒው የተለያዩ ሕዝቦች «ክርስቲያን እንሁን፣ በክርስትና ሃይማኖት የሚያጠምቀንና ክርስትናን የሚያስተምሩን ካህናት ላኩልን» በማለት ለነገሥታቱና ለቤተ ክርስቲያን አባቶች መልእክት ይልኩ ነበር።***

በተመሳሳይ መልኩ በ1580 ዓ.ም በዐፄ ሠርጸ ድንግል ዘመነ መንግሥት የእናርያው ንጉሥ በዳንቾ እርሱና የሚገዛው ሕዝብ ክርስትናን መቀበል እንደ ሚፈልጉ ለንጉሠ ነገሥቱ በማሳወቅ በዚያኑ ዓመት ክርስትናን ተቀብሎ በሕዝቡም ዘንድ አስፋፍቶአል። የንጉሥ በዳንቾ አባት ንጉሥ ጉማንቾም እንዲሁ ለረጅም ጊዜ ለክርስቲያኑ መንግሥት በተደጋጋሚ ክርስትናን መቀበል እንደ ሚፈልግ ጽፎና አሳውቆ ነበር። ወቅታዊ ሁኔታዎች ባለመፍቀዳቸው ሳይሳካለት ቀረ እንጂ። ሻጥ በተባለው አካባቢ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ የጋፋት ሕዝቦች እንዲሁም ለዐፄ ሠርጸ ድንግል ክርስትናን መቀበል እንደ ሚፈልጉ ጽፈውና ልከው በ1573 ዓ.ም ክርስትናን /የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን/ ተቀብለዋል። እንደነዚህ ዓይነት በርካታ ጥያቄዎች ለክርስቲያኑ መንግሥት ነገሥታት እየቀረቡ የተለያዩ ሕዝቦች በፍላጐታቸው ክርስትናን ሲቀበሉ ኑረዋል።

በእርግጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን የክርስቲያኑ መንግሥት በአንዳንድ ወቅታዊ ሁኔታዎች የተነሣ የተወሰኑ ሕዝቦችን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ሃይማኖትን እንዲቀበሉ ያደረገበት ጊዜ አለ። ከነዚህ ሊጠቀስ የሚችለው በዐፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት /1399-1414/ ዓ.ም ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መግባትና በዐፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመነ መንግሥት ደግሞ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ይኖሩ የነበሩ ሙስሊሞች ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ለመመለስ የተካሄዱት ዘመቻዎች ናቸው።

በበጌምድር ይኖሩ የነበሩ ቤተ እስራኤላውያን በተደጋጋሚ በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ያምፁ ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት ቤተ እስራኤላውያን በክርስቲያኑ መንግሥት ሥር ሆነው መገበር ስላልፈለጉ ነው። ይህንንም ምኞታቸውን በሃይማኖት በማሳበብ ክርስትናን በአካባቢያቸው እንዳይስፋፋ ብዙ ጥረት አደረጉ። ይህን ያስተዋለው ዐፄ ይስሐቅም ክርስትናን ካልተቀበሉ መሬታቸውን /ርስታቸውን/ ለቀው እንዲሄዱ ስለ ዐወጀ የፈለገ ክርስትናን ተቀበለ ያልፈለገ ለቅቆ (ፈልሶ) ሄደ። ይህን የክርስቲያኑ መንግሥት ለራሱ ዓላማ ማሳኪያ ያደረገው ዐዋጅ እና ርምጃ እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠንስሳ አሳቧ ያደረገችው አይደለም። አጥምቁ ተብለው ሲታዘዙ ያጠመቁ ካህናትና የቤተ ክርስቲያን አባቶችም



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

አይወቀሱበትም::

በዐፄ ዮሐንስ ፬ኛ ዘመነ መንግሥትም ቦሩ ሜዳ ላይ 1871 ዓ.ም በተደረገው ጉባኤ በኢትዮጵያ የሚገኙ ሙስሊሞች ክርስትናን እንዲቀበሉ ታውጇል:: ይህንም ዐዋጅ ያወጀውና የተገበረው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት እንጅ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ፍላጎትና ሥልጣን አይደለም:: ዐፄ ዮሐንስ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እየተከፋፈለ የመጣው የእስልምና ሃይማኖት እጅግ አስግቷቸው ነበር:: በሱዳን እና በሰሜን አፍሪካ ከፍተኛ የእስልምና የማንሠራራት እንቅስቃሴ ነበር:: ይህን ተከትሎ በኢትዮጵያም መጠነኛ የሆኑ እንቅስቃሴዎች በወሎ እና ሌሎች አካባቢዎች ማቆጥቆጥ ጀመሩ:: በወቅቱ የነበረው የእስልምና ማንሠራራት (Islamic Revivalism) ከሃይማኖታዊ ገጽታው ይልቅ ፖለቲካዊ ገጽታው ያመዝን ነበር:: በዚህም የተነሣ ነው ዐፄ ዮሐንስ እንደ ትልቅ ጽናት የቆጠሩት:: በመሆኑም እንቅስቃሴውን ለማዳከም በርካታ ሙስሊም ወገኖችን ወደ ክርስትና የመመለስ ዘመቻ ተደርጓል::

ከዚህ እንደ ምንረዳው የክርስቲያኑ መንግሥት ከራሱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት በመነሣት አንዳንድ ሕዝቦችን ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንዲመለሱ ቢያስገድዱ ቤተ ክርስቲያኗን የሚያስጠይቅና የሚያስወቅስ አይደለም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት አባቶች፣ መነኰሳትና ባሕታውያን ክርስትናን ያስፋፉ የነበሩት በዐዋጅ (በሰይፍ) ሳይሆን ከተለያዩ ሕዝቦች ጋር ሰላማዊ ግንኙነት በመፍጠር፣ በማስተማርና በመስበክ ነው:: በግዴታ ቢያጠምቁ ኖሮ ቤተ ክርስቲያኗን የሚያስጠይቃት ይሆናል::

### *ኢትዮጵያ «የክርስቲያን ደሴት» ስለ መባሏ*

አስቀድመን ከላይ ከጠቀስነው ጋር ተያይዞ የሚነሣው ደግሞ:-

*«የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያን እንደ 'ክርስቲያን ደሴት' በመቁጠር ለሌሎች ሃይማኖቶች በተለይ እስልምና እንዳይስፋፉ አድርጋለች::»*

የሚለው ወቀሳ ነው:: የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የመንግስት ሃይማኖት በመሆኑ «በመንግሥት ግዛት የሚኖረው ሕዝብ በሙሉ ክርስቲያን ይሁን» ብላ የተሟገተችበት ጊዜ የለም:: በአንድ ወገን ነገሥታቱን የወሰድን እንድሆን ግዛታቸውን ባስፋፉ ቁጥር የሚይዙትንና የሚያስገብሩትን አገር ግብር እስከ ገበረ ድረስ የሃይማኖትና የአስተዳደር ነጻነት ይሰጡታል:: በ14ኛውና በ15ኛው የነበሩትን የኢፋት ሙስሊም መንግሥት እና የሐድያን መንግሥት ብንወስድ በክርስቲያኑ መንግሥት ሥር ሲገቡ ከዓመታዊ ግብር በስተቀር ሙሉ ነጻነት በሃይማኖትና በውስጥ አስ ተዳደር ተሰጥቷቸዋል:: የነዚህ ጥቃቅን መንግሥታት ገዥዎችም ሆኑ ሕዝቦ ቻቸው የክርስትናን ሃይማኖት እንዲቀበሉ አልተገደዱም::

**በታሪክ ጥናት አንድ ትልቅ ወንጀል አለ:: ይኸውም በእንግሊዝኛ "Anachronism" ይባላል:: "Anachronism" ለሚለው ቃል መሳ የሆነ የአማርኛ ቃል ወይም ሐረግ ማግኘት ያዳግታል:: ትርጉሙ ግን ያለፈን ጊዜ ታሪክ አሁን ባለንበት ጊዜ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ አስተሳሰብና ሁኔታ መመልከትና መመዘን ነው:: የአሁን ጊዜ ዕድገት ያመጣቸውን ለውጦች እየመዘዝን ያለፈውን ጊዜ መኮነን እና ማውገዝ እጅግ ተገቢ አይደለም::**

ኢትዮጵያ «የክርስቲያን ደሴት» ተብላ የተሰየመችው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት በመሆኗ አይደለም:: ከሰባተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ ጠረፋማ ቦታዎችና በአጎራባች አገሮች እስልምና እጅግ መስፋፋት ጀመረ:: ከ10ኛውና ከ11ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ /የክርስቲያኑ መንግሥት/ በአብዛኛው በአጎራባቹ ያሉ መንግሥታትና ሕዝቦች በመሆናችው ኢትዮጵያ እንደ ክርስቲያን ደሴት መቆጠር ተጀመረች:: ይህም በአውሮፓውያን ዘንድ እጅግ የታወቀ ነበር:: በተለያዩ ወቅቶች ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱ የሃይማኖት ተጓዦች /Pilgrims/ አማካይነት ኢትዮጵያ በሙስሊም መንግሥታትና ሕዝቦች የተከበበች የክርስቲያን ሀገር መሆኗ ታወቀ::

የመስቀል ተዋጊዎችም (Crusaders) ስለ ኢትዮጵያ በርካታ ዜናዎችን ለአውሮፓውያን የክርስቲያን መንግሥታት አሳውቀዋል:: በዚህም ምክንያት ነው ኢትዮጵያ «የክርስቲያን ደሴት» ተብላ መቆጠር የጀመረችው:: የመስቀል ጦርነቶችን አስመልክቶ "... በአውሮፓ 'ክሩሴድስ' የሚባለው ጦርነት ነበር:: የክርስትና ሃይማኖትን በመላው ዓለም ለማስፋፋት የተካሄደ ጦርነት ነው::" ብለዋል:: የመስቀል ጦርነቶች በተለያዩ ዘሮች የተካሄዱት ኢየሩሳሌምንና አካባቢዋን /T.he Holy Land/ ከሙስሊሞች (ከተማን ቱርኮች) ይዞታ ለማስለቀቅ ነው እንጅ ክርስትናን በመላው ዓለም ለማስፋፋት አይደለም::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትወቀስበትና ጨቋኝና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ተብላ የምትፈረጀው «በተለያዩ ቋንቋዎች ስብከት አለማካሄዷ፣ አንድ ቋንቋ ብቻ ለስብከትና ለማስትማር በመጠቀም የሌሎችን መብት ተጋፍታለች» የሚለው ነው:: ይህን ሐሳብ በብዛት የሚስነዝሩት ወገኖች የኢትዮጵያ ኦርቶኮክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን «አንድ ሕዝብ፣ አንድ ሀገር፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ቋንቋ» የሚል ዓላማ ይዛ ይህን ስትተገብር የኖረች አድርገው ይመጠለከቷታል:: በርካታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች በተለያየ ቦታ ክርስትናን በሚያስተምሩበት ወቅት የአካባቢውን ቋንቋ በመጠቀም ነው:: በተለይ ከ13ኛው እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በተለያዩ ቦታዎች ክርስትናን ያስፋ የሕዝቡን ወግና ባሕል መሠረት አድርገው፣ ቋንቋውን አጥንተው ነበር::

የአማርኛ ቋንቋን መስፋፋት ያመጣው የክርስትና መስፋፋት አይደለም:: የመንግሥት መስፋፋት እና የአማርኛ በጽሑፍ ደረጃ መስፋፋት ነው:: አማርኛ በተለያዩ ቦታዎች ሊታወቅ የቻለው እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለጽሑፍ በብዛት የምትጠቀመው የግዕዝን ቋንቋ ነበር:: የአማርኛ ቋንቋ መስፋፋት በማያወላውል ሁኔታ ከኢትዮጵያ መንግሥት መስፋፋት ጋር የተያያዘ ታሪካዊ ክሥተት እንጂ ቤተ ክርስቲያን ሆን ብላ የፈጠረችው አይደለም::

*«ነፍጠኝነትንና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያገናኘው ምንም ጉዳይ በታሪክም ባለንበት ጊዜም የለም::»*



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

«ነፍጠኛ» የሚለው ቃል በአሁኑ ጊዜ በየቀኑ የምንሰማው ቃል ነው ። ነፍጠኛ የሚለው ቃል «ነፍጥ» ከሚለው ስያሜ የመጣ ነው ። የቃሉ ምንጭ የሆነው ቋንቋ የቱርክ ወይም ዐረብ ቋንቋ ነው ። በቱርክና ዐረብ ቋንቋ «ነፍጥ» ማለት የሚቀጣጠል፣ የሚነድ እሳትነት ያለው ነገር መጠሪያ ነው። ይህም በመሆኑ በመጀመሪያ «ነፍጥ» የሚለው ቃል ለባሩድ የወጣ ስያሜ ነው። በባሩድ የሚተኮስ ጠመንጃ ሲሠራ ነፍጥ የጠመንጃው መጠሪያ ሆነ። ወደ ኢትዮጵያ ነፍጥ ከገባበት ከዐፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ነፍጥ፡- ባሩድ፥ ባፉ ጎርሶ ባፉ የሚተፋ ጠመንጃ መጠሪያ ነው። ነፍጥ የታጠቀ ወታደርም ነፍጠኛ ተብሎ ይጠራ ነበር። ከጊዜ በኋላም ነፍጠኛ «ለመንግሥት አገልጋይ የሆነ ወታደር» መጠሪያ ሆነ። ነገር ግን ከሥር ከመሠረቱ ነፍጠኛ ከወታደርና ከተኳሽ ሰው ውጭ ምንም አይነት ትርጉም አልነበረውም ። ነፍጠኛ ከብሔር ጋር የተያያዘ ትርጉም የለውም ። ከመሬት ጋርም እንዲሁ።

በመንግሥት አገልጋይነቱ መሬት የያዘ ማንኛውም ሰው ጉልተኛ ወይም መልከኛ በመባል ይጠራል። ነፍጠኛን ከአንድ ብሔር ጋር ብቻ የሚያያይዘው ምንም ዓይነት ታሪካዊ ክሥተት የለም።

ነፍጠኝነትንና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያገናኘው ምንም ጉዳይ በታሪክም ባለንበት ጊዜም የለም ። ክርስትናን የፈጠረው በኢትዮጵያ ውስጥ ተንሰራፍቶ የነበረው ዘውዳዊ ሥርዓት አይደለም። ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማትን አማራ አልፈጠረውም እንደማንኛውም ሕዝብ ተቀበለው እንጂ። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን በኢትዮጵያ የነበረው ዘውዳዊ ሥርዓት ቢፈጥረው ወይም የአማራ እና የጉራጊ ሃይማኖት ብቻ ቢሆን ኖሮ የአንድን ወገን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፍላጎት ለማራመድ የተፈጠረ ሃይማኖት ነው ማለት ይቻላል ። ነገር ግን ክርስትና በዓለማችን የቢሊዮኖች እምነት ነው ። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ደግሞ የትግራይዋ፣ የአገው፣ የዛይ፣ የኦሮሞ ፣የአማራ ... ወዘተ ሕዝቦች እንደ ፍላጎታቸው የተቀበሉት ሃይማኖት ነው።

*«እስተውሎ መናገርና ቂጣ መጋገር ከመሸ ይደርሳል።»*

«የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የነፍጠኛ ሃይማኖት ነው» እና «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በተለያዩ ቋንቋዎች ስብከት አላካሄደችም» ሲባል ትልቅ የታሪክ ስሕተት ነው። በታሪክ ጥናት አንድ ትልቅ ወንጀል አለ። ይኸውም በእንግሊዝኛ "Anachronism" ይባላል። "Anachronism" ለሚለው ቃል መሳ የሆነ የአማርኛ ቃል ወይም ሐረግ ማግኘት ያዳግታል። ትርጉሙ ግን ያለፈን ጊዜ ታሪክ አሁን ባለንበት ጊዜ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ አስተሳሰብና ሁኔታ መመልከትና መመዘን ነው። የአሁን ጊዜ ዕድገት ያመጣቸውን ለውጦች ችየመዘዝን ያለኘፈውን ጊዜ መኮነን እና ማውገዝ እጅግ ተገቢ አይደለም። ያለፈውን ጊዜ በአሁኑ ጊዜ ለይን ብንመለከተው ታሪክ ትርጉም አልባ ይሆናል። የፖለቲካ ሰው ግን ለፖለቲካ ጥቅም ሲል ያለፈውን ጊዜ አሁን ባለንበት ደረጃ በመመዘንና በመገምገም ያለፈውን ማውገዙና መኮነኑ የተለመደ ነው ።

## *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ያህል ታላቅና የብዙ ምእመን ባለቤት መንግሥት ብቻዋን ትሂድ ብሎ የሚተዋት አይደለችም። ቤተ ክርስቲያኗ በሕዝቡ ማኅ በራዊ ሕይወት ትልቅ ሚና አላትና*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በረጅም ታሪኳ በመንግሥት ከፍተኛ በደል የደረሰባት ተቋም ናት። ነገሥታቱ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያኗ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ሲገቡ ኑረዋል። በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ሃይማኖታዊ ጉባኤዎች ነገሥታቱ ከካህናቱ የበለጠ ሚና ነበራቸው። በእርግጥ ነገሥታቱ ቤተ ክርስቲያንን በተለያዩ ቁሳዊ ስጦታዎች ይደግፋሉ። የዚያን ያህል ደግሞ በማያገባቸው የሃይማኖት ልዩነት እና ክርክር ውስጥ ጣልቃ ሲገቡ ኑረዋል። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያኗ ሐዋርያዊ ተልእኮዋን በሚገባ እንዳትወጣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መሰናክሎች ነበሩ። የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ከሥልጣን መውረድ ተከትሎ «መንግሥትና ሃይማኖት ተነጣጥለዋል» እየተባለ ይነገራል። በእርግጥ በወረቀትና በሕግ ደረጃ ተነጣጥለዋል።

የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት በኢትዮጵያ የይስሙላ ድርጊት ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ያህል ታላቅና የብዙ ምእመን ባለቤት መንግሥት ብቻዋን ትሂድ ብሎ የሚተዋት አይደለችም። ቤተ ክርስቲያኗ በሕዝቡ ማሕህበራዊ ሕይወት ትልቅ ሚና አላትና።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱን ታሪክ ከሞላ ጎደል ጠብቃ ያቆየች ናት። ታላላቅ የቱሪስት መስሕብ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት፣ ታሪካዊ ቦታዎች እና የሕዝብ በዓላት ባለቤት ናት። በመሆኑም በኢትዮጵያ ካሉት ሃይማኖቶች ሁሉ ለየት ያለ ቦታ ይገባታል።

ትልቅና ታሪካዊ በሆነችው በዚህች ቤተ ክርስቲያን ላይ ሂስና ወቀሳ ከየትኛውም ወገን ይሰነዘር ይሆናል። ይሁንና ከሁሉም በፊት ታሪኳን ጠንቅቆ መመርመርና ማወቅ ይገባዋል። አበው እንደ ሚሉት:

- *«አስተውሎ መናገርና ቂጣ መጋገር ከመሸ ይደርሳል።»*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዲ/ን ደረጀ ጅማ

# ቅድስና እና ፈለገ ቅዱሳን

## በኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሕይወት ውስጥ

አምላካችን እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ዘሌ19÷2። ቅዱስ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ከመውደዱ የተነሣ የእርሱ የሆኑትን ባሕርያዊ ሀብታት የሰው ልጆች በጸጋ ገንዘብ ያደርጓቸው ዘንድ ፈቅዷል። የሰው ልጆች ገንዘብ ያደርጓቸው ዘንድ እግዚአብሔር ከፈቀደላቸው የእግዚአብሔር ባሕርያዊ ሀብታት መካከል ቅድስና አንዱና ዋነኛው ነው። "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነው" ተብሎ እንደ ተጻፈ። 1ተሰ4÷3።

ነገር ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንዲሆኑ ብቻ ፈቅዶ ዝም አላላቸውም። በኑሮአቸው ሁሉ የቅድስናን ሕይወት እንዲመሩ "ቅዱሳን ሁኑ" አላቸው እንጂ። ዘሌዋ19÷3። ሁሉን የሚያውቅ ጌታ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን "ቅዱሳን ሁኑ" ብሎ ያዘዘው የሰው ልጆች ሁሉ ቅድስናን ገንዘብ ማድረግ የሚያስችል ተፈጥሮአዊ ዝንባሌና መንፈሳዊነት እንዳላቸው ስለሚያውቅ ነው። በእርግጥ ይህም የእርሱ የማይቋረጥ መግቦት ውጤት ነው።

በዚህ የተነሣ እርሱ ብቻ ማንነታቸውንና ቁጥራቸውን የሚያውቃቸው ባለሟሎቹ የቅድስና ሕይወትን ለመምራት ወስነው በመጋደልና የእግዚአብሔርን ርዳታ አጋዥ በማድረግ ለቅድስና በቅተዋል። ይሁን እንጂ እያንዳንዷን የቅድስና ሕይወት ለመራመድና ደረጃዎቹን ለመወጣጣት በርካታ መሰናክሎች ገጥመዋቸዋል። የገጠማቸው ፈተና ግን እንደ የዘመኑና እንደ የፈተናው ምንነት የተለያየ ነበር። ረድኤተ እግዚአብሔርና የቅድስናን ሕይወት ለመምራት ያላቸው የመንፈስ ልዕልና ግን ለድል አብቅቷቸዋል።

ሰዎች የቅድስናን ሕይወት እንዲመሩ እግዚአብሔር በመፍቀዱና ተፈጥሮአዊ የሆነ መንፈሳዊ ዝንባሌ በውስጣቸው ስላለ ቅድስናን ዘመን አይገታውም በየዘመኑ በተነሡ ጽኑዐን ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ሲንጸባረቅ ይኖራል እንጂ።

ዛሬም ቢሆን የቅድስና ሕይወትን ለመምራት ምቹ የሆኑ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አሉ። በአንጻሩም ይህን ሕይወት ለመምራት የሚፈታተኑ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ሰዎች እግዚአብሔር የፈቀደላቸውንና ውስጣቸው የሚሻውን የቅድስና ሕይወት እንዳይመሩ ሊያደርጋቸው ይችላል።

ነገር ግን ቅድስና ከየዘመኑና ከየፈታኙ የመጡትን መሰናክሎችና ፈተናዎች ማለፍ ነው። የበረቱት ይኖሩበታል፤ የደከሙትም የሚናፍቁት ሆነዋል። ለመኾኑ ዛሬ ቅድስና በማኅበረሰባችን ዘንድ ያለው ግንዛቤና እውነታው ምን ይመስላል? ይህን ሕይወት ለመምራትስ ሰዎች ጉዞ ሲጀምሩ የሚፈታተኗቸው መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ምንድን ናቸው? ለነዚህና ለሌሎች ጥያቄዎች ይህ ጽሑፍ የተለያዩ ምእመናንን ተሞክሮዎች መሠረት በማድረግ ክርስቲያኖች ስለ ቅድስና ያላቸውን እይታና ተሞክሮ ለመዳሰስ ይሞክራል። የጽሑፉ ዓላማ ቅድስናን ዛሬ ባለው ማኅበረሰብ ደረጃ ማሳየት፣ መሰናክሎቹን ማሳወቅና መጠቆም ነው። ይህም በዘመኑ ያለን ክርስቲያኖች በቅድስና ዙሪያ ያለንን እይታና የሕይወት ተሞክሮ ዘወር ብለን ለመመርመር ያስችለናል። እንዲሁም በዘመናችን የቅድስና ሕይወትን በተቻላቸው መጠን እየኖሩ ያሉ ሰዎች የገጠማቸው መሰናክልና መሰናክሎቹን ለማለፍ ያደረጉትን ጥረት ይህን ሕይወት ለመኖር መንፈሳዊ ግዴታ ላለብን ክርስተያኖች መልካም ማስተማርያ ይሆናል፡፡ የምናያቸውና የምንሰማቸው ነገሮች ሁሉ ፈታኝ በሆኑበት ወቅት ሰዎች የቅድስና ሕይወትን እንዳይዘነጉ ማበረታታትና የበረቱትን ማጠናከር ደግሞ ተገቢና ወቅታዊ ነው።

### መግቢያ

ዲ/ን ዘርዐ ዳዊት መንግሥቱ ይባላል። የማይጨው ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰባኬ ወንጌል ነው። ስለ ቅድስና ሲናገር እንዲህ ይላል፡- "ቅድስና ጥሪ ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ወደ ቤቱ ሲያመጣህ ለቅድስና ነው። ምክንያቱም ሰው በራሱ ኃይል ወደ እግዚአብሔር መጥቶ የእግዚአብሔርን ቃል ለመማርና ሕጉን ለመፈጸም አይችልም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ጥሪ ተቀብሎ የሚኖር ሰው ሕይወቱን በቅድስና መምራት ይችላል። ስለዚህ ቅድስና ለእኔ የእግዚአብሔር ጥሪ ነው።"

በኢትዮጵያ፣ በሕንድ፣ በሶርያና በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ አራት መጻሕፍትን ጽፋለች። የቅዱሳት ሥዕላትን ክብርም በተመለከተ የጻፈችው መጽሐፍ አለ። ቻይሎት ክርስቲና ትባላለች። ስለ ቅድስና የሰጠችው ሐተታ የዲ/ን ዘርዐ ዳዊትን አስተያየት ያጠናክራል። "ቅድስና በተለይ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥሪ ነው።" በሥርዓተ ቅዳሴ ላይ እንደ ሚደመጠው ቅድስና ጥሪ ነው።

ምሁረ አሪት በነበረው ገማልያል እግር ስር ተቀምጦ ሲማር የነበረውና በደማስቆ ጎዳና ላይ ሳለ በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠራው ቅዱስ ጳውሎስ ሁለቱ ሰዎች ከላይ የሰጡትን ማብራርያ በዚህ ቃል ያትመዋል፡- "እግዚአብሔር ለቅድስና ጠርቶናል።" 1ተሰ4÷7። የሮሜ ክርስቲያኖችንም "በእግዚአብሐር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ..." ማለቱ "የቅድስናን



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ጥሪነት" በግልጥ ያስረዳል::

የዕድሜ ባዕለ ጸጋና የአቋቋም መምህር የሆኑት መምህር ሐዲስ አበበ ደግሞ:- "ቀደሰ ማለት አመሰገነ ማለት ነው:: ቅዱስ ሲል ምስጉን እያለ ነው:: ስለዚህ ቅድስና ማለት የተመሰገነ ወይም ምስጉንነት ማለት ነው" ብለዋል:: ቤተ ክርስቲያን ካሏት ከድጓ መምህራን አንዱ የሆኑት ሊቀ መዘምራን መንግሥቱ ገብረ አብ ደግሞ ቅድስናን ሲያብራሩ እንዲህ ነው ያሉት፤ "ቀደሰ ማለት ለየ ማለት እንደሆነ ዕወቅ:: ቅዱስ ስንል ልዩ ማለታችን ነው:: በመሆኑም ቅድስና ስንል ልዩ መሆንን÷ ልዩነትን ያመላክታል::"

በአርሲ ሀገረ ስብከት የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ረዳት ፕሮጀክት አስተባባሪና የሒሳብ ሠራተኛ ነች:: ወ/ት የትም ወርቅ ዓለም ትበላለች:: ከሊቀ መዘምራን መንግሥቱ ጋር ተባብራ "ቅድስና መለየት ነው" ትላለች:: ልዑለ ባሕርይ ቅዱስ እግዚአብሔር «አብርሃም አባታችንን ከአገርህ፣ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ውጣ::" ብሎታል:: ዘፍጥ.12÷1:: የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችም "ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፤ ርኩስንም አትንኩ" ተብለዋል:: 2ቆሮ6÷17–18:: በዚህ መሠረት ቅድስና "ለእግዚአብሔር ልዩ መሆን" ነው:: ለሥርዐት አምልኮና ለመንፈሳዊ ሕይወት ከማይመች ቦታ፣ ማኅበረሰብና ኃጢአት መለየት ነው–ቅድስና::

የሕንድ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህን ናቸው:: በአሁኑ ጊዜ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አካዳሚክ ዲን ሲሆኑ በኮሌጁ «የመሠረተ እምነት ሥነ–መለኮት» /Dogmatic Theology/ እና «ንጽጽራዊ ትምህርተ መለኮት" /Comparative Theology/ መምህር ናቸው:: ቅድስና የእግዚአብሔር መለያና ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር የተያያዘ ነው:: የእግዚአብሔር መለያ ነው ስል የእግዚአብሔር ባሕርያዊ ገንዘብ ነው ለማለት ፈልጌ ነው:: ወሰን የለሽና የማይናወጥ ቅድስና ባለቤት እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ከፀሐይ ብርሃን እንደ ሚገኝ ቅድስናም ከእግዚአብሔር ይገኛል:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አምላክ የባሕርይ ገንዘቡ የሆነውን ቅድስና ዘወትር ለሰዎች በልግሥናውና ስለ ተጋድሎአቸው ጽናት በጸጋው ብዛት ይሰጣል::

ስለዚህ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ቅዱሳን መላእክት፣ ቅዱሳንና ለእግዚአብሔር ቅርብ የሆኑ ወገኖች የእግዚአብሔርን ባሕርያዊ ቅድስና በጸጋና በተጋድሎ ገንዘብ ከማድረጋቸው የተነሣና የአምላክ ባለሟል በመሆናቸው ቅድስናን ወደ ሌሎች ያስተላልፋሉ:: ለምሳሌ:- ፀሐይ ብርሃንን ከእግዚአብሔር አግኝታለች፤ ጨረቃም ከፀሐይ:: ፀሐይም ሆነች ጨረቃ የተቀበሉትን ብርሃን እንደ ሚያንጸባርቁና እንደ ሚያስተላልፉ ሁሉ ቅዱስ ከሆነው እግዚአብሔር ቅድስናን የተቀበሉ ቅዱሳን ሁሉ ቅድስናን ሲያንጸባርቁና ሲያስተላልፉ ይኖራሉ::"

እንደ ተጠቀሰው ቅድስና ለእግዚአብሔር የባሕርዩ ነው:: ሰዎችም ይህን ያውቁ ዘንድ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝ" ሲል አስቀድሞ ነግሯቸዋል::ዘሌ.19÷2:: እመ ሳሙኤል ሐናም "እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና" ያለችው ለዚህ ነው:: 1ሳሙ.2÷2:: ክብር ይግባውና የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የባሕርይው የሆነውን ቅድስና ሰዎች በጸጋ ገንዘብ ያደርጉ ዘንድ ፈቅዶላቸዋል:: "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነው::" እንዲል:: 1ተሰ4÷3:: ምክንያቱም እርሱ ካልረዳንና የቅድስናን ሥራ እንፈጽም ዘንድ በጎ ፈቃዱን ካልሰጠን በራሳችን ትግል ብቻ የቅድስና ሕይወትን መምራት አንችልም:: «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» የተባለው ለዚህ ነው::ዮሐ15÷5::

በዚህ ጽሑፍ ስማቸው የተጠቀሱትም ሆኑ ሌሎች ቅድስናን ጥሪ፣ መለየት፣ ምስጉንነት፣ ስጦታ፣ ክብርና ቡሩክነት ሲሉ ገልጠውታል:: ለቅድስና ካላቸው ግንዛቤ፣ ከሕይወት ተሞክሮአቸውና በተለያየ ማእዝን ከመመልከት አንጻር ከላይ በተመለከትነው መልኩ ገልጸውታል::

በዚህች ፈታኝ ዓለም ሕይወታቸውን በቅድስና መርተው እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላቸው ቦታ የተወሰዱ ቅዱሳን ብዙ ናቸው:: ዛሬም ቢሆን ልዑል እግዚአብሔር የቅድስናን ሕይወት የሚኖሩ ብዙ ልጆች አሉት:: በአንጻሩ የቅድስና ሕይወት የማይሞከርና ሌሎች ብቻ እንዲኖሩት የተደነገገ አድርገን የምንቆጥር ጥቂቶች አይደለንም:: ቅድስና የክርስቲያን ዋነኛና መሠረታዊ ተግባር የማይመስላቸው ሰዎች አሉ:: "በዓለም ላይ እየኖሩ የቅድስና ሕይወትን መምራት አይቻልም" የሚሉም ይኖራሉ:: የእግዚአብሔር መንግሥት ያለ ቅድስና ልትወረስ እንደ ማትችል አለማወቅም ሌላው ምክንያት ነው:: ሌሎች ብዙ ምክንያቶችም ይቀርባሉ::

መ/ር ሐዲስ አበበ ግን "ቅድስና የክርስቲያን ዋና ተግባር ነው» ይላሉ:: ወ/ሪት ክርስቲናም የመ/ር ሐዲስን ሐሳብ በመጋራት "በተቻለን መጠን ወደ ቅድስና ለመድረስ መትጋት ይጠበቅብናል" /We are supposed to reach as far as possible to the state of holiness/ ብላለች:: እርግጥ አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ምግባር ከመጠመድ ይልቅ በኃጢአት ግብር ሠልጥነው ይታያሉ:: ይህ ጊዜ ነው ክርስቲያኖችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው «ሥራ ፈት" የሚያሰኛቸው:: ለሁሉ አሳቢ እግዚአብሔር ግን ከመንፈሳዊ ምግባር መራቃቸውንና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው «ሥራ ፍት» መሆናቸውን «ሥራ ፈትታችሁ ቀኑን ሁሉ በዚህ ስለምን ትቆማላችሁ" በማለት ይነግራቸዋል:: "እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ፤ የሚገባውንም እሰጣችኋለሁ" ሲል ወዳልጀመሩትና ወዳልገቡበት መንፈሳዊ ምግባር (በጎ ሥራ) ያሰማራቸዋል:: ማቴ22÷6 "በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል:: ይገባልም ይወጣልም፣ መሰማርያም ያገኛል::" ብሎ የለ::

በመሆኑም የቅድስናን ሕይወት ለመምራት እግዚአብሔርን አጋዥ ማድረግ ዋነኛ ተግባር መሆኑን ማመን ይገባል:: የቅድስና ሕይወት ዋና ተግባር መባሉ ሰዎች የተጠሩበት ዓላማ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስም ቁልፍ ተግባር ስለሆነ ነው:: ነገር ግን የቅድስና ሕይወት መወጠን፣ መኀልበት ያለበት በዚህ ዓለም ላይ ነው:: ምክንያቱም ከሞትና ከምጽአት በኋላ ያለው ጊዜ የደመወዝ (የዋጋ) ወይም የፍዳ መቀበያ ጊዜ እንጂ ሥራ ለመሥራት የሚቻልበት አይደለም :: በዚህ ዓለም ላይ እየኖሩ የቅድስና ሕይወትን መምራት ስለ መቻሉ የቅዱሳን ታሪክ ዐይነተኛ አስረጅ ነው:: ዛሬ ያለው ክርስቲያን በዚህ ዙሪያ ምን ይላል?

ወ/ሮ ንግሥት አኀናፍር የልጆች እናትና በማይጨው (በትግራይ ደቡባዊ ዞን) የሴቶች ጉዳይ ሐላፊ ነች:: በዚህ ዙሪያ ስትናገር ይህን ብላለች:– "በዚህ ዓለም ውስጥ

***በዓለም ውስጥ እየኖርን የቅድስና ሕይወትን መምራት ሊከብደን ይችላል:: ይሁን እንጂ ቅድስና በእግዚአብሔር የተደረገልን ጥሪ ነውና የቅድስናን ሕይወት ማጽናት ይገባናል:: በእርግጥ እንወድቃለን፤ ይሁን እንጂ መነሣት አለብን::***



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ሆኖ የቅድስናን ሕይወት መምራት በጣም ከባድ ነው:: ብዙ ፈተናም ያጋጥማል:: እንዲያውም የቅድስና ሕይወት የመሰላል ላይ ሩጫ ነው:: ነገር ግን ዓላማ ካለን እንችላለን:: እርግጥ ይህን ሕይወት ለመኖር መሰናከልም፣ መውደቅም ይኖራል:: ነገር ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደካሞችና ለኃጢአተኞች የመጣ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: በኃጢታችን ተስፋ ሳንቆርጥ የቅድስናን ሕይወት ለመኖር መታገል አለብን:: እስከ መጨረሻው የምንጸና ከሆነ እግዚአብሔር አምላክ ከጎናችን ሆኖ ይረዳናል::"

የወ/ሮ ንግሥት አጎናፍርን ገለጻ የምታጠናክረው ወ/ሪት ቻይሎት ክርስቲና ሰዎች በዓለም ውስጥ እየኖሩ ሊመሩት የሚገባውን የቅድስና ሕይወት አስመልክታ ስትናገር:- «እኛ ኃጢአተኞች ነን:: በብዙ ሥጋዊና መንፈሳዊ ድርጊታችን ደካሞች ነን:: በዚህ የተነሣ በዓለም ውስጥ እየኖርን የቅድስና ሕይወትን መምራት ሊከብደን ይችላል:: ይሁን እንጂ ቅድስና በእግዚአብሔር የተደረገልን ጥሪ ነውና የቅድስናን ሕይወት ማጽናት ይገባናል:: በእርግጥ እንወድቃለን፤እ ይሁን እንጂ መነሣት አለብን::" ብላለች::

"በዓለም ስንኖር ብዙ ፈተና አለ:: ይሁን እንጂ ያን ፈተና አሸንፈን መኖር አለብን" የምትለው ደግሞ ወ/ት ነጻነት አበረ የተባለች የአዲስ አበባ ነዋሪ ነች::" ሊቀ መዘምራን መንግሥቱም:- "እችለዋለሁ ብሎ በእግዚአብሔር ላመነና በትዕግሥት ለጸና ሰው ይቻላል፤ ለእግዚአብሔር ምን የሚሳነው ነገር ይኖራል? እግዚአብሔር ከረዳን የማይቻል ነገር የለም" በማለት ለራሳቸው ጥያቄ ምላሹን ይሰጣሉ::

የቅድስናን ሕይወት ኖረው የፈጸሙትም ሆኑ እየኖሩ ያሉት ግን እንደኛው በዓለም ላይ የነበሩና ያሉ መሆኑን እንርሳ:: እነሱ በእምነት ዓለምን ድል ነስተው የቅድስናን ሕይወት ኖሩ:: እኛም ዓላማ ካለን ዓለምን በእምነት አሸንፈን የቅድስና ሕይወትን በዓለም ላይ ሳለን መምራት እንችላለን ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ከበረታን እንችላለን:: "ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው::" ተብሏልና::

ቅድስና በስውርም በገሀድም ነው:: ይህንንም የቀደሙት ዛሬም እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቃቸው ሰው የማያውቃቸው ቅዱሳን ኖረውና እየኖሩ አሳይተውናል:: የቅድስናን ሕይወት እንደ አቅሙ ለመምራት የወሰነ ሰው በግል ሕይወቱ የሚታዩና የቅድስናን ሕይወት ለመጀመሩ ምልክት የሚሆኑ መንፈሳዊ ምግባራትን ይተገብራል:: የባንኪንግ ባለሞያ የሆነችው ወ/ት ነጻነት አበረ አንድ ሰው የቅድስና ሕይወትን በአቅሙ መኖር ጀምሯል ለማለት ማሳያዎች ናቸው የምትላቸውን ጠቅሳለች– "በእግዚአብሔር ቤት መኖር አለበት– በእግዚአብሔር ቤት ሲኖር ደግሞ እንዴት መኖር እንዳለበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲመላለስ አስተምሮናል:: ጌታ ባስተማረው መንገድ የሚኖር ሰው የቅድስና ሕይወትን እየኖረ ነው:: ቅድስና ለእኔ ሰውነትን ከኃጢአት አርቆ ውድቀት ቢገጥም እንኳን በንስሐ እየተነሡ እንደ ቃሉ መኖር ነው::"

መ/ር ሐዲስ አበበ ደግሞ "በትዳር ሕይወት ያሉቱ አንዱ በሌላው ተወስኖ፣ በንስሐ ሕይወት፣ በሥጋ ወደሙ እየታተሙ በምክረ ካህን፣ በፈቃደ ካህን የሚኖሩ ሰዎች የቅድስናን ሕይወት እየመሩ ያሉ ናቸው:: ካህንም ቢሆን ሥልጣነ ክህነቱን ጠብቆ፣ አስተምሮ፣ ፈጣሪውን አመስግኖ በትሕትናና በትዕግሥት እያገለገለ የሚኖር ከሆነ ይህ በራሱ ቅድስና ነው:: ሌላው ንጽሕና ጠብቆ ከትዕቢትና ከትዝህርት ርቆ ከሐሜትም ተጠብቆ መኖር ቅድስና ነው:: ብለዋል" በደሴ መሐል ከተማ ያገኘነውና በንግድ የሚተዳደረው ወጣት አበባው ደስታም "ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ነው:: መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ በእምነት ውስጥ ሆኖ ማድረግ ቅድስና ነው::" ይላል::

"ራስን ከመጥፎ ነገር ቆጥቦ ሥጋን ቀጥቶ መኖር በራሱ የቅድስና ፍሬ ነው» ባለችው የንግሥት ሐሳብ ላይ የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት ሊቀ መዘምራን መንግሥቱ ገብረ አብ የሚከተለውን ማጠናከሪያ ሰጥተዋል– "ሌላው ሰው ኖሮትም ሆነ በችግር ያገኘውን እንደ ልቡ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲዘፍንና ሲጨፍር እንደ አገባቡ በአቅማቸው የሚኖሩ፣ አንድ ለአንድ ተወስነው፣ ሰግደው፣ ጹመው፣ ጸልየው፣ አስቀድሰውና ቆርበው የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የቅድስናን ሕይወት እየኖሩ ያሉ ናቸው::"

ሕንዳዊው ካህን ዶ/ር ጆሲ ያዕቆብ ደግሞ ቅድስና በእምነትና በንጽሕና ተቀድሞ የሚጀመር ሕይወት መሆኑን ገልጠዋል:: (Purity in man and Faith of man are a precondition to a cquire holiness.) እንዲሁም ጨረቃ ከፀሐይ የምታገኘውን ብርሃን እንደ ምታንጸባርቅና እንደ ምታስተላልፍ ሁሉ ለእግዚአብሔር ቅርብ የሆኑ ሰዎች /የቅድስናን ሕይወት እየመሩ ያሉቱ/ የእግዚአብሔርን ቅድስና ያንጸባርቃሉ::" ብለዋል::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" ሲል ማስተማሩ እዚህ ላይ መዘንጋት የለበትም:: ማቴ.5÷14–16:: በዚህ ዓለም ላይ ስንኖር ከሰዎች ጋር መስተጋብር ማድረግ ግድ ነው:: በዚህ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጉድኝት ውስጥ ደግሞ የቅድስና ሕይወት መንጸባረቅ አለበት:: ቦታና ሁኔታ የማይወስነውን አምላክ እያዘከሩ ቦታና ሁኔታ ያቀረቡትን የፈተና ፍሪዳ መጎምጀትና መነካካት ታማኝነትን ማጉደል ነው:: የቅድስና ሕይወት ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለ ጉድኝት ውስጥ እንዴት ባለ መልኩ ይገለጣልን አስመልክታ ወ/ሮ ንግሥት አጎናፍር ስታስረዳ:– "ለሰዎች ቀና አስተሳሰብ ይዞ፣ በጎ ነገር አድርጎ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እየተሳተፉ መኖር ነው::" ብላለች::

መምህር ሐዲስ ደግሞ "አፍቅር ቢጽከ፤ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" ብለው ይጀምራሉ:: "አፍቅር ቢጽከ ከመ ነፍስከ ነውና ከሰው ጋር ተስማምቶ መኖር፣ ነዳያንን መርዳት፣ የሥራ ጓደኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር በትሕትናና በትዕግሥት እያገለገሉ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እየተሳተፉ መኖር ከሰዎች ጋር በሚኖር ጉድኝት የሚገለጥ የቅድስና ሕይወት ነው::"

የቅድስና ሁሉ መገኛ እግዚአብሔር እንደ መሆኑ የሰው ልጅ በራሱ ሕይወት ውስጥ ለሚያሳድጋቸውና ከማኅበረሰቡ ጋር ሳለ ለሚያንጸባርቃቸው የቅድስና ፍሬዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው አንድነት ወሳኝ ነው:: "የቅድስና ሕይወትን መኖር ጀምሯል" ለማለትም በእግዚአብሔርና በእርሱ መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት የሚጠቁሙ ምልክቶች ይኖራሉ:: ይሁን እንጂ ይህ ሕይወቱ በሌሎች ዘንድ ሊታወቅም ላይታወቅም ይችላል::

ወ/ት ነጻነት አበረና ወ/ሮ ንግሥት አጎናፍር "አንድ ሰው በኃጢአት የበደለውን አምላክ ንስሐ ገብቶ ይቅርታ ሲጠይቅ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት በኩል የሚገለጠውን የቅድስና ሕይወት ጉዞ ጀምሯል ይባላል" ይላሉ:: «ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ጥሪና ጸጋ በአኮቴት መቀበል በራሱ የቅድስና ሕይወትን ለመኖር የጀመሩ ሰዎች መገለጫ ነው" የሚለው ደግሞ ዲ/ን ዘርዐ ዳዊት መንግሥቱ ነው::

"እንደ ቃሉ መኖር" ስትል ነጻነት አበረ የጠቀሰችውን መ/ር ሐዲስ አበበ በዚህ መልኩ ገልጸውታል:– "ዐሥርቱ ቃላተ ኦሪትንና ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ተግብሮ መኖር ነው:: በተጨማሪም እግዚአብሔርን ማመስገንና "ብሉ፤ ጠጡ" ያለንን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን እየተቀበሉ መኖር ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ውስጥ የሚንጸባረቅ ጅምር የቅድስና ሕይወት ፍሬ ነው::" ብለዋል:: ወ/ሮ ንግሥት አጎናፍርም ይህን ሐሳብ ይጋራሉ::

ወ/ሮ ግብፂት ለማ በበኩላቸው:
– "ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት

[ወደ ገጽ ፳፰ ዞሯል]



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ሰባቱ ኪዳናት

(መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው)

*ባለፈው እትማችን ኪዳን የሚለው ቃል ትርጉም፣ኪዳናት የተጻፉበትን ጊዜ፣የተጻፉበትን ምክንያትና በእነማን እንደ ተጻፉ ተመልክተናል:: ተከታዩን ክፍል እነሆ፣ መልካም ንባብ::*

መጻሕፍተ ኪዳን በሁለት ይከፈላሉ:: እነርሱም:– መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ እና መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ ይባላሉ:: እነዚህን መጻሕፍት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት መሠረታውያን ከሆኑ ሰማንያ አንድ መጻሕፍት አምላካውያት ተመድበው ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ይቆጠራሉ::

• **መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ**

መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ:– ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሚደነግጉ 59 አንቀጾችንና ሰባቱ ኪዳናትን ያካተተ ትልቅ የሥርዐት መጽሐፍ ነው:: ሰባቱ ኪዳናት የሚባሉት የዘወትር ኪዳናት፣ ትምህርተ ኅቡአት፣ እግዚአብሔር ዘብርሃናት፣ ቅዳሴ እግዚእ፣ በእንተ ቅድሳት፣ ፍትሐት ዘወልድ፣ ቅዱስ ሥሉስ ናቸው:: እነዚህ ሰባቱ ኪዳናት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የጎላ ድርሻ አላቸው:: የአገልግሎታቸውን ዝርዝርና ይዘታቸውን በቀጣይ የምንመለከተው ይሆናል::

• **የዘወትር ኪዳናት**

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የዘወትር ኪዳናት በሦስት የኪዳን ጊዜያት ተከፍለው ይደርሳሉ:: እነርሱም ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት፣ ኪዳን ዘነግህና ኪዳን ዘሠርክ ናቸው:: እነዚህ የዘወትር ኪዳናት በዜማም ሆነ በድጋም የሚደረሱት ሕጋውያን በሆኑ ቀሳውስት ብቻ ነው:: ጸሎተ ኪዳንን ዲያቆናት ማድረስ አይችሉም:: እንደ ማንኛውም ምእመን ሕዝቡ ሊሉት የሚገባውን አብረው ይላሉ እንጂ የዘወትር ኪዳናትን በዜማም ሆነ በድጋም አያደርሱም:: ይህ ሥርዐት ካህናት የሚያደርሱትን÷ ዲያቆናት የሚሉትንና ምእመናን የሚቀበሉትን ለያይቶ ይደነግጋል:: በዚህ መሠረት ምንጊዜም ካህናት የዲያቆናትን ተልእኮ ተክተው ማገልገል ይችላሉ:: ዲያቆናት ግን የካህናትን ተልእኮ ተክተው ለማገልገል ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድላቸውም::

<u>ለምሳሌ</u>:- በቅዳሴ ጊዜ ሰሞነኛው ዲያቆን እክል አጋጥሞት ለማስታኮት ባይደርስ በምትኩ ቄሱ በዲቁና ገብቶ ሊቀድስ ይችላል:: ነገር ግን እክል አጋጥሞት የቀረው ቄሱ ከሆነ ዲያቆኑ ቄሱን ተክቶ መቀደስ አይችልም:: ይኸውም የካህናት ሥልጣን ከዲያቆናት ሥልጣን እጅግ መብለጡን ያመለክታል::

የዘወትር ኪዳናት /ጸሎተ ኪዳን ዘሠለስቱ ጊዜያት/ በውስጣቸው ዘጠኙን ሥርዓተ ጸሎታት /ዘጠኙ ኪዳናት/ ይይዛሉ:: እነርሱም:-

1/ ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት

ሀ. ለከ እግዚኦ ለገባሬ ኵሉ /አቤቱ ሁሉን ለፈጠርህ/

ለ. አምላከ ብርሃን ወላዴ ሕይወት /የብርሃን አምላክ የሕይወት መገኛ/

ሐ. ንሤልስ ለከ ዘንተ ስብሐተ /ይህን ምስጋና ሦስተኛ ጊዜ ለአንተ እናቀርባለን/

2/ ኪዳን ዘነግህ

ሀ. እግዚአብሔር አብ ወሀቤ ብርሃን /ብርሃንን የሚሰጥ እግዚአብሔር አብ/

ለ. እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ /አቤቱ! ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ

ሐ. ንሤልስ ለከ ዘንተ ቅዱሰ /ክብር ምስጋና ሦስተኛ ጊዜ እናቀር ብልኻለን/

3/ ኪዳን ዘሠርክ

ሀ. ለከ ለአብ ዘኢይማስን መድኃኔ ነፍስነ /የማትለወጥ አንተን የነፍሳችን መድኃኒት/

ለ. ንዌድሰከ እግዚኦ /አቤቱ አንተን እናመሰግናለን/

ሐ. ለከ ዘእም ልብነ /ከልባችን ምስጋናን ሦስተኛ ጊዜ ለአንተ እናቀርባለን/ ናቸው::

1.6 አደራረስ:–

ኪዳን:– በሌሊት፣ በነግህ፣ በሠርክ ሊደርስ እንደ ሚገባ ሆኖ በሦስት ዓይነት እንደ ተዘጋጀ ተመልክተናል:: አደራረሳቸው÷ በሦስቱ የዜማ ስልቶች የሚደረስበት ወቅት አለ:: ይሁንና አብዛኛውን ጊዜ ግን የሚደረሰው በዕዝል ነው:: ሦስተኛው የኪዳን ክፍል /ኪዳን ዘሠርክ/ ምን ጊዜም በዜማ ከሆነ የሚደረሰው በአራራይ ብቻ ነው:: ነገር ግን በዓመት ውስጥ ለዐሥራ ዐራት ጊዜያት በግዕዝ ይደረሳል:: እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው::

1.ታኅሣሥ 28 ቀን የዐማኑኤል ዋዜማ
2.የገብር ኄር ሳምንት ከሰኞ እስከ ዐርብ በአሉት በአምስቱ ዕለታት
3. የሆሳዕና ዋዜማ
4. የዕርገት ዕለት
5. የደብረ ታቦር ዋዜማና ዕለት
6. ቅዱስ ዮሐንስ /መስከረም አንድ/
7. መስቀል
8. የኅዳር ሚካኤልና ሰኔ ሚካኤል
9.ስብከት

<u>ምንጭ</u>:- <u>ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት÷</u> ገጽ 98 - 99

በእነዚህ ዕለታት ኪዳኑ በግዕዝ ይደረሳል:: ይህ በመሆኑ ህየንተ ዕዝሉ በግእዝ ይገባል::

ደወል ተደውሎ ቤተ ክርስቲያን ሲከፈት በነግህ ጸሎተ ዕጣን ደግሞ የታቦቱን መንበር እየዞረ የሚያጥን አገልጋይ ካህን «ተሠሃልከ እግዚኦ ምድረከ፣ አቤቱ ምድርህን /ሕዝብህን/ ይቅር አልክ» በማለት እግዚኦታውን ያደርሳል:: እግዚኦታው ከተደረሰ በኋላ ቅዱስ በማለት የዘወትር ኪዳናት የምስጋና ጸሎት ይደረጋል:: በታላላቅ አድባራትና ገዳማት አጣኙ ካህን በዕለቱ ሊቀ ጳጳስ ካለ ሊቀ ጳጳሱ «ቅዱስ» እንዲል ያደርጋል:: ሊቀ ጳጳስ ከሌለ የደብሩ አለቃ እንዲሁም በዕድሜ አረጋዊ የሆኑ አባት ካሉ አጣኙ ካህን «ቅዱስ» እንዲሉ በአክብሮት ይጋብዛቸዋል:: ፈቃዳቸው ከሆነ «ቅዱስ» ይላሉ:: ያም ባይሆን ያጠነው ካህን «ቅዱስ» እንዲል በአክብሮት ይመልሱታል::

ቅዱስ ከተባለ በኋላ ካህናቱ የታደለቸውን ጸሎተ ኪዳን በንባብና በዜማ ሲያደርሱ በዕለቱ ቤተ ክርስቲያን ስመው÷ ጸሎተ ኪዳን አድርሰው በረከት ለመሳተፍ በቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰቡ ምእመናን ካህናቱን ተከትለው ሕዝቡ ሊል የሚገባውን ተሰጥዎ ይቀባላሉ:: ለምሳሌ ካህኑ «ቅዱስ» ሲል ምእመናንም ካህኑን ተከትለው «ቅዱስ» ይላሉ:: ካህኑ :– «እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌ ክሙ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን» ሲል ሕዝቡ ደግሞ «ምስለ መንፈስከ፣ ከመንፈስህ ጋር» በማለት ይከተሉታል:: ጸሎተ ኪዳን÷ እንደ ሥርዐተ ቅዳሴ ምእመናን ይሳተፉበታል::

በየዕለቱ ቅዳሴ ካለ ቅዳሴ ከመግባቱ አስቀድሞ ኪዳን ይደርሳል:: እንዲሁም በቅዳሴው መሐል ቅዱስ ወንጌል ከመነበቡ አስቀድሞ ከዘጠኙ ኪዳናት ሦስቱ ይባላሉ:: ቅዳሴው የጠዋት ቅዳሴ ከሆነ «እግዚአብሔር አብ፣ እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ንሤልስ ለከ ዘንተ ቅዱሰ» የተባሉት በንባብ ወይም በዜማ ይባላሉ:: ቅዳሴው የቀትር ቅዳሴ ከሆነ ደግሞ ለከ ለአብ፣



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ንዌድሰከ፣ ለከ ዘእም ልብነ» የተሰኙት ይባላሉ:: በሠርክ፥ ምህላ በሚደረስባቸው ገዳማት ደግሞ «ለከ ለአብ ዘኢይማስን መድኃኔ ነፍስነ፣ ንዌድሰከ እግዚአ ለከ ዘእም ልብነ» /ኪዳን ዘሠርክ/ የተባሉ በዜማ ወይም በንባብ ይባላሉ::

ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል የቀረቡ ዲያቆናት በትምህርት ከሚጠየቁት አንዱ የዘወትር ኪዳናትን በቃላቸው አጥንተው መያዝ አለመያዛቸው ነው:: የዘወትር ኪዳናትን ሳያጠኑ የቅስና ሥልጣን አይሰጥም:: የቅስና ሥልጣን የተቀበሉ ቀሳውስት ተራቸው ዘወትር ከሆነ በቤተ ክርስቲያን፥ ሰሞነኛ ካልሆኑ ደግሞ በቤታቸው ዘወትር ጸሎተ ኪዳን መድገም ይጠበቅባቸዋል:: ካህናት ደዌ ዘሥጋና ደዌ ዘነፍስ ያገኛቸውን ምእመናን ጸሎተ ኪዳን በመድገም ያጠምቃሉ፣ ንስሐም ይሰጣሉ::

ሕፃናት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ሲያገኙ ጸሎተ ኪዳን ይደገማል:: (ምእመናን በሥላሴ፣ በጻድቃን፣ በሰማዕታትና በመላእክት፣ ዝክር ሲያደርጉ ካህናት ተገኝተው ጸሎተ ኪዳን ያደርሱላቸዋል:: ምእመናን ቤታቸው በቅዱስ ጠበል እንዲረጭ ሲፈልጉ ጸሎተ ኪዳን ከሌሎች ውዳሴያት ጋር አብሮ ተደግሞለት ጠበል ይረጫል:: በመጨረሻም ምእመናን ከዚህ ዓለም ተሰናብተው ሲጓዙ:- ጸሎተ ፍትሐት ሲደረግላቸው ጸሎተ ኪዳን አይታጎልም:: በጠቅላላው ጸሎተ ኪዳን የማይደረስበት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የለም ለማለት ይቻላል::

### 59ኙ አንቀጾች

መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ 59 አንቀጾች እንዳሉት በመነሻችን አመልክተናል:: እነዚህ ዝርዝር አንቀጾች በቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: የአንቀጾቹ ዝርዝር ይዘት ከዚህ እንደ ሚከተለው ይሆናል::

አንቀጽ 1:- ስለ መንፈስ ቅዱስ /አምላክነት/
አንቀጽ2:- ስለ ኋለኛው ዘመን ትምህርት
አንቀጽ3:- በሰማያት ስላለው ነገር
አንቀጽ4:- ስለ ተመረጡ ሰዎች
አንቀጽ5:- በሀገሮች ላይ ስለ ተነገረ ትንቢት
አንቀጽ6:- ስለ ሐሳዌ መሲሕ ትምህርት
አንቀጽ7:- ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ስላስተማራቸው ትምህርት
አንቀጽ8:- ኢየሱስ ክርስቶስ ለማርያም፣ ለማርታና ለሰሎሜ ስለ መለሰላቸው
አንቀጽ9:- በሃይማኖትና በምግባር ስለ ጸኑ ሰዎች
አንቀጽ10:- ስለ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና
አንቀጽ11:- ስለ ጳጳሳት ሹመት
አንቀጽ12:- ስለ ጳጳሳት ሹመት የሚደረግ ሥርዓተ ጸሎት
አንቀጽ13:- ኤጲስ ቆጶሳት ለጸሎትና ለመሥዋዕት ስለ ሚያደርጉት ዝግጅት
አንቀጽ14:- በቤተ ክርስቲያን ስለሚያስተምሩ ሰዎች
አንቀጽ15:- በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ መቆሚያ ቦታዎች ስለ መኖሩ
አንቀጽ16:- ስለ ሥርዓተ ቁርባን
አንቀጽ 17:- ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ
አንቀጽ 18:- ለበሽተኞች ስለ ሚደረግ ቅብዕ
አንቀጽ 19:- ስለ ማኅበር ምስጋና
አንቀጽ 20:- ስለ ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን
አንቀጽ 21 እስከ 24 :- ስለ ቀሳውስት ሹመትና ሥርዓተ ጸሎት
አንቀጽ25:- የካህናትን ቃል ስለ ሚሰሙ ሰዎች
አንቀጽ26:- ስለ ድኅነትና ስለ ጥፋት
አንቀጽ27:- በሽተኞችን ስለ ሚጎበኙ ካህናት
አንቀጽ 28:- ስለ ዲያቆናት ሹመት
አንቀጽ29:- ስለ ዲያቆናት መላላክና እንግዳ መቀበል
አንቀጽ 30:- ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መቆም እንዲገባቸው
አንቀጽ31:- ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት
አንቀጽ32:- ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ስለ ሚቆሙ ሰዎች
አንቀጽ33:-ስለ ዲያቆናት አገልግሎት
አንቀጽ34 እስከ 36:- ስለ ምእመናን ሹመትና ሊደረግላቸው ስለ ሚገባ ጸሎት
አንቀጽ37:- ስለ ጧት አገልግሎት
አንቀጽ38:- ስለ ንፍቅ ዲያቆን ሹመት
አንቀጽ39:-
አንቀጽ40:-መሾም ስለ ማይገባው ሰው
አንቀጽ41:- ስለ ሕዝባውያን
አንቀጽ 42:- አገልጋዮችን ስለ መቀበል
አንቀጽ43:- ስለ ዘማውያን ሥርዓተ ጥምቀት
አንቀጽ44:- ሰላምን ስለ መቀበል
አንቀጽ45:- ሴቶች ራሳቸውን መከናነብ እንዳለባቸው
አንቀጽ46:- ንዑስ ክርስቲያንን ስለ መባረክ
አንቀጽ47 እስከ 48:- ንዑስ ክርስቲያንን በመከራቸው ጊዜ ስለ መቀበል
አንቀጽ 49:- ስለ ሥርዐተ ጥምቀት
አንቀጽ50:- ስለ ሜሮን አቀባብ
አንቀጽ51:- ስለ ምሥጢረ ቁርባን
አንቀጽ52:- በበዓለ ኀምሳ ጾምና ስግደት እንደ ማይገባ
አንቀጽ53:- ከኤጲስ ቆጶሳት ጋር ስለ ሚጠሩ ሰዎች
አንቀጽ54:- ለቤተ ክርስቲያን መባ ስለ ሚያገቡ ሰዎች
አንቀጽ 55:- ስለ ሙሽሮች ሥርዐት
አንቀጽ 56:- ለበሽተኞች ስለ ሚፈጸም ተግባር
አንቀጽ 57:- ስለ ሞተ ድኻ ሰው የሚደረግ ሥርዓተ ጸሎት
አንቀጽ 58:- ሁል ጊዜ ስለ ሚጸልዩ ሰዎች

ይቆየን

# ቅድስና እና....

/ከገጽ ፳፮ የዞረ/

የቅድስናን ሕይወት መኖር ጀምረዋል ሊባል የሚችለው የሃይማኖትን ሥራ እየሠሩ የሚኖሩ ከሆነ ነው" ይላሉ:: ካህኑ ዶ/ር ጆሲ ያዕቆብ ግን የሃይማኖት ሥራ ለመሥራት እግዚአብሔርን ማመን ቀዳሚነት እንዳለው በሚጠቁም ምልክት ይጀምራሉ፤ "እግዚአብሔርን ማመን ወደ እርሱ መጸለይና ትእዛዙን መጠበቅ" ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት መልካም የሆነና የቅድስና ሕይወትን መኖር የጀመሩ ሰዎች ምልክት ነው::» ብለዋል::

ሰዎች ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጋር በሚኖራችው ግንኙነት እንኳን ሳይቀር የቅድስና ሕይወትን መኖር ለመፈለጋቸውና ለመጀመራቸው ጥቋምታ የሚሰጡ ምግባራትን ይከውናሉ:: ወ/ሮ ግብፂት «ወደ ቤተ ክርስቲያን መመላለስ፣ ለቤተ ክርስቲያን መልካምና አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ ናቸው» ሲሉ ይህ እንዳለ ሆኖ ትላለች ወ/ት ነጻነት አበረ ደግሞ "በእግዚአብሔር ቤት ጸንቶ መኖር ያስፈልጋል::»

የእግዚአብሔርን ቤት ባከበረው ነቢዩ ሳሙኤልና በተዳፈሩት የዔሊ ልጆች መካከል ያለውን የቅድስና ሕይወት ልዩነት ስንመረምር:- ቅድስና ለቤተ ክርስቲያን በሚደረግ ክብር እንደ ሚንጸባረቅ እንረዳለን:: የነቢይት ሐናን በቤተ መቅደስ መጽናትና መመስገን ስናስታውስም በንስሐና በሥጋ ወደሙ እየኖሩ በቤቱ መጽናትም ለመመስገን እንደ ሚያበቃ እንረዳለን:: ቅድስንና ምስጉንነት ነውና::

ከዚህ በተጨማሪ «መንፈሳዊ ምግባራትን ገንዝብ ከማድረግ ጋር በሃይማኖት መጽናት፣ ለሃይማኖት መቅናት፣ ስለ ሃይማኖት ሰማዕትነትን መቀበል፣ አሕዛብና መናፍቃን በሃይማኖት፣ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ የሚነዙትን የክሕደትና የኑፋቄ ቃል ሐሰትነት ለማጋለጥ የተለያዩ መጻሕፍትን የጻፉና የሚጽፉ የእግዚአብሔር ልጆች የቅድስና ሕይወትን እንደ የደረጃቸው መኖር የጀመሩ ናቸው» የሚል አስተያየት የሰጡ ክርስቲያኖች አሉ::

በመግቢያችን ላይ ለመግለጽ እንደ ሞከርነው የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ዛሬ ባሉት ክርስቲያኖችና የማኅበረሰቡ አካላት ደረጃ ቅድስናን በመሠረታዊነትና በተጨባጭ የሕይወት ተሞክሮዎች ማሳየት ነው:: ስለ ቅድስና ዛሬ እየኖሩ ያሉ ሰዎች ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር በማሳያነት ማቅረብ ነው:: በጽሑፉ ውስጥ ቅድስና ጥሪ፣ ስጦታ፣ ልዩ




© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደባ ቴአትር ሲቃኝ




ዲ/ን ኤርሚያስ በዛብህ
ቢ.ኤ ዲግሪ በቴአትር ጥበብ

የቴአትር ጥበብ በኢትዮጵያ ሲጀመር እንደ ሌሎቹ ጥበባት ሁሉ በእግሩ ያቆሙት የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ነበሩ– እነቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ:: እንዲያውም ኀምሳኛ ዓመቱን በቅርቡ ያከበረው የአሁኑ ብሔራዊ ቴአትር÷ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ቤት ተብሎ በ1948 ዓ.ም ሲመረቅ የቀረበው ቴአትር -የዳዊትና አርዮን ታሪክ ነበር::

ነገር ግን በሂደት በተለይም ከ1966ቱ የአብዮቱ ፍንዳታ ጋር ተያይዞ መንፈሳዊ ቴአትር ከቴአትር ቤቱ መድረክ ጠፋ እንጂ ቀደም ባሉት ዓመታት በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እየተዘጋጁ በመድረኩ ላይ ተስተናግደዋል::

የቴአትር ቤቶቹ መድረኮች የሚያስተናግዱት ዓለማዊ እና አብዮታዊ ተውኔቶችን ነበር:: ቢሆንም የተውኔት ጥበብ ክርስትናን ማስተማሪያነቱ እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ በየሰንበት ትምህርት ቤቶች መድረኮች ዛሬም ቀጥሎአል::

ሆኖም ሰንበት ት/ቤቶቹ ጠንካራ ጭብጥ ሐሳብ ያላቸው ቴአትሮች ቢደርሱም ባለባቸው የገንዘብ እና የባለሞያ እጥረት ብዙዎቹ ተውኔቶች ቴክኒካዊ ብቃታቸው ደካማ ነው ለማለት ይቻላል::

ነገር ግን በያዝነው ዓመት መስከረም ወር መግቢያ ላይ አንድ የቴአትር ማስታወቂያ በማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት አጥር ላይ ተሰቅሎ ነበር:: ማስታወቂያው «ደባ» የሚባል ቴአትር በየሳምንቱ እሑድ በፑሽኪን አዳራሽ እንደ ሚቀርብ ያውጃል:: ደስታ ተሰማኝ:: ምክንያቱም የተሻለ መድረክ፣ የተሻለ መብራት እና የድምጽ መሣሪያ፣ የተሻለ የተመልካች መቀመጫ /ለቴአትር ተብሎ የተዘጋጀ ማለቴ ነው/ የተሟላለት ነበር::

የመክፈቻው ዕለት ሄድኩ፤ መስከረም 22 ቀን 1998 ዓ.ም:: የመግቢያ ትኬት ገዝቼ ወደ አዳራሹ ገባሁ:: አዳራሹ ሞልቷል:: ሆኖም ዕድል ቀንቶኝ አንድ ወንበር ፊት ለፊት አካባቢ አገኘሁኝ::

ቴአትሩ ከመጀመሩ በፊት የባህል ማዕከሉ ምክትል ዳይሬክተር ደራሲና ባለቅኔ አቶ አያልነህ ሙላቱ የመግቢያ ንግግር አደረገ:: መንፈሳዊ ቴአትሩ በአዳራሹ እንዲታይ መፈቀዱ አስደስቶኛል:: አቶ አያልነህ ደግሞ በመግቢያ ንግግሩ የተፈቀደበትን ምክንያት ሲያብራራ:- *«በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኢትዮጵያ የምጠ ትባለው ሀገር አለች:: የኢትዮጵያ ጥበባት መነሻ እና ማደጊያ ቤተ ክርስቲያን ናት:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያኒቱ ብዙ ለመድረክ ሊበቁ የሚገባቸው ታሪኮች፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያውቃቸውና ሊማርባቸው የሚገቡ እውነታዎች ባለቤት ስለሆነች»* ማዕከሉ የማኅበረ ቅዱሳንን ጥያቄ በደስታ እንደ ተቀበለው ተናግሮአል::

የአቶ አያልነህን ሐሳብ በውስጤ አመላለስኩት:: እውነት ነው:: የብዙ መንፈሳዊና ቁሳዊ ቅርሶች ባለቤቶች ነን፤ ብዙ ታሪክ አለን:: ይህን ሀብት ግን በአስተማሪነቱም ኾነ በሌላ ጠቃሚ መልኩ ቴአትር ወይም ፊልም አድርገን ማቅረብ አልቻልንም:: አልያም አላሰብንበትም ወይም አስፈላጊነቱን አላመንበትም:: ግን ሰው ዓለማዊ ቴአትሮች ወይም ፊልሞችን ይታደም መተቸቱን እንችልበታለን::

ለማንኛውም «ደባ» መንፈሳዊ ቴአትር እስከ አሁን በሰንበት ት/ቤቶች መድረክ ከታየው ባልተለመደ መልኩ በፑሽኪን አዳራሽ ሳምንታዊ መርሐ ግብር ተዘርግቶለት በመታየት ላይ ይገኛል:: ጥሩ ጅምር÷ ጥሩ ተሞክሮ ነው:: በተለይ ዕውቀቱም አቅሙም እያላቸው በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ላልቻሉ ሰዎች የሚያመለክተው ነገር አለ::

ደኅና:: እኔም «ድሬ»ን ተመለከትኩት:: አንዳንድ ጊዜ በድምጽ እና በመብራት አጠቃቀም ቴክኒክ ላይ ከሚፈጠረው ችግር እና የገጸ መድረኩ /Scenery/ መስሕብነት በመጠኑ ቀርነት ያለበት ከመሆኑ ውጪ ጥሩ ቀርቦአል:: በአቅጣጫ ደረጃ ጅምር እንደ መሆኑ መጠን ሊበረታታ የሚገባው ነው::

ከላይ ያነሣኋቸውን ቴክኒካዊ ግድፈቶች የተውኔቱ ይዘት እና የመሪ ተዋንያኑ የትወና ብቃት ይሸፍነዋል:: የተውኔቱ ይዘት ተመልካችን÷ እኔን ጨምሮ÷ ቴአትሩን በትችት ዐይን ከማየት ይልቅ ከታሪኩ ጋር አብሮ እንዲፈስ አድርጎታል:: ተውኔቱ ጉልበት አለው:: በተቃራኒ ጫፍ የቆሙ ሁለት ባለጋራዎችን አጋጭቶ ትክክለኛውን ፍትሕ ሲሰጥ አይቻለሁ:: በርግጥ ብዙ ተመልካች ስለ ታደመበት የተለያየ አተያይ ሊኖር ይችላል:: የጥበብ ሥራ ነውና:: ሁሉም እንደ ልምዱ አተያዩን ሊያንጸባርቅ ይችላል:: በእኔ በኩል ግን አስተውሎቴን እነሆ ብያለሁ::

ዓለምና ቤተ ክርስቲያን ይታገላሉ በደባ ተውኔት ውስጥ:: ነገር ጠንሳሿም የተንኮል ባለመረቧ ዓለም ናት:: ረጃጅም የተንኮል ጥፍር ያላቸው እጆቿን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስገባት ጥረት አደረገች:: በዚህም ቤተ ክርስቲያኒቱ ታወከች:: ማዕበሉ አናወጣት:: የልጆቿን ልብ ከፋፈለ:: በመጨረሻው የታሪክ ምዕራፍ እውነቱ ሲገለጥ ዓለም በሀፍረት ተሸረከርካ ወደቀች:: ቤተ ክርስቲያን የልዕልና ደውሏን አሰማች:: ታሪኩ ባጭሩ እነሆ ....

ውስን ተውኔታዊ መቼቱ የተወሰነ ሥፍራ ባልተጠቀሰ ጥንታዊ ደብር ውስጥ፣ሚ በቅርቡ አንድ ለጉልበቱ፣ ለገንዘቡ፣ ለጊዜው ... የማይሳሳ ለጋሥ መንፈሳዊ በጎ አድራጊ ክርስቲያን ተከሥቷል:: የቤተ ክርስቲያኑን ዙሪያ አሳጠረ፤ መንፈሳዊ ጉባኤያት እንዲካሄዱ አደረገ፤ በሁሉም የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት ውስጥ ራሱን በማሳተፍ ጥረቱን በማሳየት በየሰው ልቡና ነገሠ:: ዝናው ናኘ:: በብዙው ምእመን ዘንድ ለደብሯ ትንሣኤ የተላከ አስፈላጊ ሰው ሆኖ ታመነበት:: ይህ ሰው በሰው ፊት እጅግ ትሑት ነው:: ንግግሩ እና ተግባሩ ሁሉ ቅንነት የተሞላበት ነው:: በዚህም ተግባሩ ብዙ ደጋፊዎችን በአጭር ጊዜ ሊያፈራ ችሏል::

በአንጻሩም በደብሯ ውስጥ በመንፈሳዊ አገልግሎቱ የታወቀ፣ ለተፈላጊው መሥዋእትነት ግንባሩን የማያጥፍ ሚክያስ የሚባል ምእመን





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

አለ። ይህ ሰው እንደታምሩ ብዙ ብር የለውም። ገንዘቡ ሕይወቱ ነው። ጥሪቱ አገልግሎቱ ነው። ክብሩን የሚገልጸው *«በቅድስና ሕይወት እና ለእውነት በመቆም»* ነው። እና እውነትን ይዘምራል። ቅንነትን ያቀነቅናል። ነገሮችን በጥልቀት እና በጥርጣሬ የመመልከት፣ አንድን ጉዳይ እሬት ወይም ማር መሆኑን በትክክል ሳያረጋግጥ ለመዋጥ አይከጅልም።

ይህ ወጣት በታምሩ የተንኮለኛ ዐይኖች ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። ነገር ግን እርሱም ታምሩን በጤንነት አይመለከተውም። የሁለቱም ግንኙነታቸው አፍአዊ ሆኖአል። ውስጣዊ አስተሳሰባቸው አንዱ ሌላውን በመከታተል፣ በማጥናትና በመጠላለፍ ላይ የተመሠረተ ሆነ።

እንዲያውም በተለያየ የትግል ጎራ ተሰልፈው ውጊያ ጀመሩ። ታምሩ ገንዘብ ስላለው መታመኛውም ማንቀሳቀሻውም የስለላ ጥበብና ገንዘብ ነው። ..... ግን ገንዘቦቹ እውነት እና ቅንነት ናቸው። የሚክያስ ዋና ዓላማ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ገብቶ አንድ ታላቅ መንፈሳዊ ቅርስ ይዞ መጥፋት ነው። ሚክያስ ግን ደግሞ ለሚያየው ወገን የሚቃትተው ቅርስ እንዳይዘረፍ ነው። ስለዚህ ለ... መሳካት ሚክያስ በተቻለ መጠን መጥፋት አለበት። ስለሆነም ሌላ አካባቢ የስብከተ ወንጌል ጉባኤ አመቻችቶ ሚክያስን ወደ ስፍራው ለማስተማር አገልግሎት በመላክ ከፊቱ ካራቀው በኋላ ባሰባሰባቸው ደጋፊዎቹ አስተባባሪነት በተካሄደ የሰበካ አስተዳደር መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት ምርጫ የሰበካ ጉባኤው ምክትል ሊቀ መንበር መሆን ችሏል ታምሩ።

ሚክያስ ደግሞ ስለ ሰውየው ከሚያውቀው መረጃ አንጻር ይህ ዕረፍት አልሰጠውም። ይህንም ተንኮል ገሀድ አድርጎ ስውር ዓላማውን ለማኮላሸት ቢሮጥም የፈለገውን ያህል መራመድ አልቻለም። እንዲያውም የታምሩ በረቂቅ የተንኮል ጥበቡ ጨምድዶ ያዘው። እውነትና ሐሰት አንገት ላንገት ተናነቁ። ነገር ግን የሚክያስ ፍጥነት በቀላሉ የሚታለፍ ባለመሆኑ የግድያ መረቡን ጣለበት።

ነገር ግን *«ደባ ራሱን ስለት ድጉሡን»* ነውና ወጥመዱ አልያዘ ለትም። ለሚክያስ የሰነዘረው ስለት ተቀለበሰበት። መከራው አልተሳካለትም። ሆኖም ቴአትሩ የሚጠናቀቀው እነዚህ ሁለት ተዋጊዎች እንደ ተፋጠጡ ነው። ሁለቱም ሕይወታቸው አላለፈም። ለጊዜው ግን የታምሩ የተቀነባበረ ተንኮል ተኮላሽቶበታል። ደጋ ፊዎቹን አጥቶ እርቃኑን ቀርቷል። ገንዘቡ /የተንኮሉ መርዝ/ እና አንደበቱ ከእርሱ ጋር ናቸው።

የተውኔቱ የጊዜ መቼት በአሁኑ

> ***የብዙ መንፈሳዊና ቁሳዊ ቅርሶች ባለቤቶች ነን፤ ብዙ ታሪክ አለን። ይህን ሀብት ግን በአስተማሪነቱም ኾነ በሌላ ጠቃሚ መልኩ ቴአትር ወይም ፊልም አድርገን ማቅረብ አልቻልንም። አልያም አላሰብንበትም ።***

ጊዜ የተወከለ ነው። በታሪኩ ውስጥ የተነሣው አውራ ጉዳይ፥ የቅርስ ዘረፋ ከተውኔቱ ጊዜ ጋር ምን ያህል የተሳለጠ ነው ብለን ስናይ ቅርሶቻችን በአሁኑ ጊዜ ያሉበትን ሁኔታ መገንዘብ ያስፈልጋል። አዎ፥ ዛሬ የአገራችንም የቤተ ክርስቲያናችንም መለያ የሆኑት የማንነታችን ማኅተሞች ለከፍተኛ ጉዳት ተጋልጠዋል። በተለያየ መንገድ እየተመዘበሩ ነው። ይህ ደግሞ በተለያዩ መገናኛ ብዙኀን ገሀድ የሆነ ሐቅ ነው። በየጉምሩክ ጣቢያው፣ በየፖሊስ ጣቢያው በኤግዚቢትነት ተይዘው የተቀመጡ የቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን ሀብቶች በየጊዜው ቁጥራቸው እየጨመረ ነው። እንዲያውም አምልኮ የሚፈጸምባቸው ንዋያተ ቅድሳት እንደ ተራ ዕቃ ለማይገባቸው ሰዎች በጨረታ እየተሸጡ፣ ለዚያውም ያልደረሱት በየመንገዱ እንደ ሸቀጣ ሸቀጥ እንደ ሚሸጡ ዘገባዎች አመልክተዋል። ለሃይማኖታዊ ቅርስ ከዚህ የባሰ ችግር የለም። ስለሆነም ጉዳዩ አንገብጋቢ ነው። የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ሊወያዩበትና የየራሳቸውን አስተዋፅኦ ሊከፍሉለት የሚገባ ስለሆነ ቴአትሩ በዚህ ጊዜ መመድረኩ አስፈላጊ ነው።

የቦታን መቼት በተመለከተ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ከመሆኑ ውጪ የተጠቀሰ ነገር የለም። ይህም የችግሩን ስፋት /ምልዓት/ የሚጠቁም ነው። ደራሲው ጥንታውያን ከሆኑት ገዳማት ወይም አድባራት መካከል አንዱን በስም ጠቅሶ የተውኔቱ ውስን መቼት ቢያደርገው ኖሮ የተመልካቹ ትኩረት ወደዚያ ቦታ ብቻ ይሆንና የቴአትሩን ቀስቃሽነት አቅም ይቀንሰው ነበር። ስለዚህ መቼቱ ዝርው መሆኑ ሁሉም በየአጥቢያው ስላለው የቤተ ክርስቲያን ጥበቃ እንዲያስብ ያደርገዋል። ከዚህ ባሻገር አንድ ውስን አካባቢን ለማንሣት ጉዳዩ ስለ ቅርስ ስለሆነ ንግግር ቀስቃሽ ይሆናል። የተጨበጠ ታሪክ ሁነት /historical fact/ ከሌለ በቀር በልቦለዳዊ መነሻ አንድን ደብር ወይም ገዳም የታሪኩ ቦታ አድርጎ ማቅረብ ክርክር ቀስቃሽ መሆኑ

አይቀሬ ነው። የታወቀ ታሪካዊ ሁነት ቢኖር እንኳን ያንን ጉዳይ ዋና የታሪክ መነሻ ለማድረግ ሰፋ ያለ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል። ስለዚህ ደራሲው ቦታን የትኩረት ማእከል ማድረግ ሳይሆን ሁሉም በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያኑን ነቅቶ እንዲጠብቅ የሚያደርግ ነው።

የባለታሪኮቹን አሰላለፍ ስናይ የአቀንቃኙ እና የፀረ አቀንቀኙ ገጸ ባሕርያት ጎራ በትክክል ተለይቶ ተቀምጦአል። ሚክያስ እውነተኛ ሰው ነው። ለአገልግሎት የማይሰንፍ ቀን ተሌት ዕረፍት የሌለው ትጉህ ነው። በዚህ አገልግሎቱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉ ሁሉ ያውቁታል። ነገሮችን ጠለቅ ብሎ የመመልከት አቅም አለው። በተለይ የመናፍቃንን ሴራ አሸትቶ ነው የሚደርስበት።

ይህ ጠባዩ እና አቅሙ ነው ከታምሩ ጋር የሚያጣላው። ታምሩ ደግሞ በተውኔቱ ውስጥ ተወስኖ ባልተገለጸ አካል ስውር ተልእኮ ተሰጥቶት ያን ለማስፈጸም የተለያዩ ማንነቶችን ተላብሶ የመጣ ሰው ነው። ታምሩ የስለላን ጥበብ ያውቃል። ተናግሮ የማሳመን ብቃቱ ከፍተኛ ነው። የተባ አንደበት አለው። ከቀረበው ሰው ጋር ሁሉ ራሱን ለውጦ የተለያየ ዐይነት ሰብእና መላበስ የሚችል ነው።

በዚህ ጠባዩ ተጠቅሞ መንፈሳዊ ሰው ሆኖ ታይቶ ነበር። ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ መሆኑን ለማሳመን በአንደበቱ ይመሰክራል፤ አንገቱን ሰበር በማድረግ ትሕትናን ያሳያል፤ ገንዘቡን እና ጉልበቱን ምንም ሳይሰስት ያወጣል። ይህ ሁሉ ግን ከቤተ ክርስቲያኗ መዝረፍ የሚፈልገው ጥንታዊ ጽሌ በእጁ እስኪገባ ነበር።

ለዚህ ዓላማው የመለመላቸው ሁለት ባለታሪኮች አሉ። ዘገየ እና ታሪኳ ይባላሉ። ለሁለቱም ተልእኮ ተሰጥቷቸዋል። ይኸውም ዘገየ በማኅበረ ካህናቱ እና በማኅበረ ምእመናኑ ዘንድ የታምሩን *«መልካም ስም»* እንዲሰብክ፤ ታሪኳ ደግሞ ሚክያስን *«ትምህርተ ሃይማኖት አስተምረኝ»* በሚል ምክንያት ቀርባ እርሱን እንድትሰልል ነበር። ከዚህ ባሻገር ለተልእኮው መሳካት ይጠቅሙኛል ላላቸው ሰዎች ሁሉ እጁ አይታጠፍም። በትምህርተ ሃይማኖት ብዙ ያልበሰለውንና በመንፈሳዊ ሕይወት ያልጠነከረውን ግርማን ከጎኑ ለማሰለፍ የቻለው በገንዘብ ኀይል እና በሚያሳየው የተሸፈነ ሰብእና ነው።





© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በመሆኑም በአካባቢው በአጭር ጊዜ ገንኖ ለመውጣት ችሎአል። እንዲያውም ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማገልገል የቀን ዕረፍት የሌት እንቅልፍ የሌለው ሚክያስ በታምሩ የተንኮል ሥራ ምክንያት በቤተ ክርስቲያኒቱ ማኅበረሰብ ዘንድ የነበረው ታማኝነት እና ተቀባይነት እያጣ መጥቷል።

ሚክያስ የታምሩን ስውር ተልእኮ ቀደም ብሎ ይሁንና በርግጠኝነት የደረሰበት ግን ታምሩ በአቀነባበረው መርሐ ግብር ሚክያስ ለስብከተ ወንጌል ሌላ ቦታ በሄደበት ዕለት የሰበካ ጉባኤ ምርጫ ተካሂዶ ታምሩ በነዘገየ ቀስቃሽነት፥ በነግርማ አጫፋሪነት የሰበካ ጉባኤው ምክትል ሊቀ መንበር ሆኖ ከተሾመ በኋላ ነበር።

አሁን ታምሩ ከመታወቅ አልፎ ይደልዎ ይደልዎ ተብሎ ተሾሞአል። ይህ ደግሞ ለሚክያስ ትግሉን ከባድና ውስብስብ ያደርግበታል። በርግጥ ከኀኑ የተሰ ለፉት የደብሩ መነኮስ አባትና ሡናይ አሁንም በመንፈስ ቢረዱትም የታምሩ ገንዘብ በርካታ ኃይሎችን አሰባስቦለታል። ከእነዚህ ከሁለቱ ሌላ ያልተታለለ የለም። ሁሉም የታምሩ አጨብጫቢ ሆኖአል። አባ እና ሡናይ ይኼ ነው የሚባል የገንዘብ እና የሥልጣን ኀይል የላቸውም። አባ ቅን አገልጋይ ናቸው። ሡናይም በእናቱ ሞት ምክንያት ራሱን የሳተ እና አንዳንዴም «ነካ የሚያደርገው» /የአእምሮ ሕመም ያለበት/ ሰው ነው። ነገር ግን ሁለቱም ከፍ ያለ ቅንዐተ ቤተ ክርስቲያን አላቸው።

የተውኔቱ ከፍተኛ ውጥረት የሚጀምረው ሚክያስ የታምሩን ማንነት አረጋግጦ ወደ ኋላ ሊያፈገፍግበት በማይችለው ጦርነት ውስጥ ሲገባ ነው። ታምሩም ሊያመልጥበት የማይችልበት ፍጥጫ ውስጥ ነው የገባው። አሁንም ምርጫው ሁለት ነው። ሚክያስ የያዘውን ተጨባጭ ማስረጃ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ይፋ ሲያደርግ የሚነሣውን ውዝግብ በዲፕሎማሲ ወይም የሚክያስን ማንነት በማብጠልጠል የማንነቱን ክብር ማስጠበቅ፤ ወይም ደግሞ ሚክያስን ከገጸ ምድር አስወግዶ ተልእኮውን በፍጥነት ማስፈጸም ነበር።

እርሱ ግን የመረጠው «አረሙን» መንቀል ነው፤ ሚክያስን መግደል። በዚህ የሐሳብ ውጥረት ውስጥ ሆኖ ሚክያስን እንድትሰልል የተመደበችው ታሪኳ በትምህርቱ ተማርካ ታምሩን ክዳዋለች። ይህ ደግሞ በታምሩ ላይ የቁጣ እሳት አነደደበት። አሁን የተፈለገውን ጥፋት አድርሶ፤ የተፈለገውን ሰው ገድሎ ተልእኮውን ማሳካት መርጦአል።

ሁለቱም ወገኖች የቆሙት በቋፍ ነው። የትግላቸው መጨረሻ ላይ ደርሰዋል። ታምሩ ከታሪኳ ውጪ ያሰባሰበው ኀይል ከኀኑ ነው። የደብሩ መነኮስ አባት ግን ያለውን ውጥረት በማየት ሚክያስ ይህን ጉዳይ እንዲተው መከሩት።

አሁን ብቸኝነት ተሰምቶታል። ውስጡ ታወከበት። ከኀኑ ማንንም አጣ። በተለይ ልትሰልለው የተላከችው ታሪኳ ማንነቷን ገልጣ ይቅርታ ስትጠይቀው ራሱን መቆ ጣጠር አልቻለም። አንድ የቀረው ወዳጅ ሡናይ ነበር። እርሱንም ሳያስበው ከሌሎች ተቃዋሚዎቹ ጋር ደርቦ በስሜት ስለ ሰደበው ተቃቃሩ። ምን እንደሚያደርግ ግራ ገባው። መንፈሱ ግን ጠንካራ ነው። ብሶቱን ለእግዚአብሔር አሰማ።

ታምሩ ደግሞ በአንድ ሌሊት ሚክያስን ገድሎ፤ አዲስ በቀጠረው የቤተ ክርስቲያን ዘበኛ ርዳታ የሚፈልገውን ቅርስ ሰርቆ ደብዛውን ሊያጠፋ ወስኖአል። ሚክያስን እንዲገድል የተመረጠው ዘገየ ነው።

ደራሲው የገጸ ባሕርያቱን ማንነት ለተውኔቱ መቋጫ ተጠቅሞበታል። ዘገየ ቀዥቃዣ ነው። ይቸኩላል። ድንጉጥ ነው። በራሱ የመተማመን አቅም የለውም። ይበረጠግጋል። ከዚህ በፊት የፈጸመው ኃጢአትና ወንጀል ብዙ ነው። የወንጀሎቹና የኃጢአቶቹ ማስረጃዎች ሁሉ በታምሩ እጅ አሉ። ይህም ዘገየን እንዳሻው ለማሽከርከር ኃይል ሆኖለታል። ዘገየም ማንነቱ እንዲጋለጥ ስለ ማይፈልግ ከባድ ወንጀል መፈጸምን መርጧል። ይኸውም ሚክያስን መግደል ነው።

ተልእኮውን ለመፈጸም ወደ ሚክያስ ቤት ከመምጣቱ በፊት «እብዱ» ሡናይ ሰፈር ውስጥ በፈጠረው ግርግር ምክንያት የነሚክያስ ቤት በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ሆኖአል። በዚህ መሀል ዘገየ ዘው ብሎ ገባ። ችኩል ስለኾነ አካባቢውን ሳይቃኝ ሽጉጡን ደገነ። በር አጠገብ የነበረው ፖሊስ ግን አፈፍ አደረገው፤ እርብትብት ነው። ተብረከረከ። እጁን ለመስጠት ጊዜ አልወሰደበትም። በፖሊሶች እጅ ከገባም በኋላ ታላቁን ምሥጢር ለመናገር ብዙ መጨነቅ፤ ብዙ መጠበቅ አልፈለገም - በርጋጋ ነዋ፤ ድንጉጥ።

ስለዚህ ፖሊሶቹን «እብዱ» ሡናይ አስመጣቸው። የዘገየ ርብትብት ጠባይ፤ በራስ ያለመተማመን እና ተቀልባሽነት የታምሩን ጥልቅ ምስጢር ገሀድ አወጣው። የታሪኩ መዘውር ተቀየረ። አሁን ተፈላጊው ታምሩ ነው። ታምሩ ግን ከባድ ሰው ነው። እስከ መጨረሻው ዳናው አልተያዘም። አሁንም «ሚክያስን ሳልገድል እጄን ፖሊስ አይይዘውም» ባይ ነው።

እንዲህ ዓይነት ሴራ፥ እንዲህ ዓይነት ተንኮል ብዙ ቦታዎች ተከሥቷል። አሁንም እየተከሠተ ነው። ብዙ ሰዎች የእንደበታቸውን ርቱዕነት ወይም የገንዘብ አቅማቸ ውን ተጠቅመው ብዙ ሁከት ሲፈጥሩ፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለያየትን ሲዘሩ እናያለን። በዚህም ምክንያት እውነተኞች ተገልለው ተንኮለኞች ሐሳባቸውና ዕቅዳቸው እስኪሞላ ገነው ይወጣሉ። በተለይም ከመናፍቃን ድርጅቶች የሚጣል ላቸውን ቁራሽ ለማግኘት ያደጉባትን ቤተ ክርስቲያን በቀሚስና በካባ ከለላ ለመውጋት የተነሡ ቁጥራቸው በርክቷል። እኒህ ሰዎች ገጽታቸው ብዙ ነው። አቀራረባቸውም በደካማ ጎን የመግባት ነው። የታመመውን እንፈውስህለን፤ የቸገረውን ገንዘብ እንሰጥሀለን፤ ግራ የገባውን እንመክርሃለን... በሚል ነው። በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያኒቱና በየቤቱ የደረሰውን ባለቤቱ ይቁጠረው። ለመፍትሔው ግን ውይይት ያስፈልገዋል።

«ድፎ» ተውኔት ቋንቋው ውብ ነው። ባለታሪኮቹ የሚናገሩት ነገር ከማንነታቸው ጋር የተመጣጠነ ነው። ውስጣቸው ሲቆጣ ቃላቱም ይናዘራሉ። በተለይ ሚክያስ ለብቻው የሆነ በመሰለው ጊዜ የሚናገራቸው ቃላት፤ በተነጻጻሪም ታምሩ ዘገየን ለተልእኮው እንዲሰማራ ለማሳመን የተጠቀማቸው ንግግሮች የተውኔቱን ውጥረት ከፍተኛ እመርታ ላይ ያደረሱ ናቸው። የተመልካችን ትኩረት ሰብስቦ ለመያዝ ያስቻሉ ናቸው። ቋንቋው ግልጽና ቀጥተኛ መሆኑ ተመልካች በቀላሉ እንዲከታተለው አድርጎታል።

የቴአትሩን አጠቃላይ መልእክት ስንመለከት *«የሚያብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ አይደለም፤ ወርቅ መስለው ከሚመጡ ተንኮለኞች ሁሉም ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቅ»* የሚል ነው።

በተይም በአሁኑ ሰዓት መናፍቃኑም ይሁኑ ለቅርስ ዘረፋ የሚመጡ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚጠጉት ያለባትን ደካማ ጎንና ክፍተት እያጠኑ ሆኖአል።

ስለሆነም ማንኞቹም የቤተ ክርስቲያን አካላት ርዳታዎች እና ድጋፎች ከተለያዩ አካላት ሲመጡ ከርዳታው ጀርባ ያሉ ሰዎች እነ ማን መሆናቸውንና ምን ዓይነት ፍላጎት እንዳላቸው በትክክል አጢኖ በጥበብ መጓዝ እንዳለብን የሚቀሰቅስ እና የሚያስጠነቅቅ መልእክት አለው።

ይህ በተለይ በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ያለው አስተዳደራዊ ሥርዐት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያወጣቻቸውን ሕጎችና ሥርዐቶች ተከትሎ የሚፈጸም መሆን አለመሆኑን ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አካል በያለበት እንዲመረምር የሚያስገነዝብ ነጥብ ነው። በአጭር ቃል «ደባ ቴአትር»ን ሁሉም በየአካባቢው ያለውን ተሞክሮ በመንተራስ ሐሳብ ሊሰጥበት፤ ልምድ ሊለዋወጥበት ይገባል እላለሁ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አቡነ ዮሐንስ እና ከሣቴ ብርሃን

/ካለፈው የቀጠለና የመጨረሻ ክፍል/

በቅዱስ ፍሬምናጦስ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ኮሌጅ በቂ የመምህራን ቁጥር እንደ ሌለና የልምድ እጥረት እንዳለ ሊቀ ትጉሃን አልሸሸጉም:: መፍትሔውም:- «የእኛን መምህራን ውጭ አገር ልኮ ማስተማር አይደለም:: የራስን ሳይጠንቅቁ የሌላውን በጥራዝ ነጠቅነት ይዞ አጉል ንቀትና ትችት ያመጣል:: እንደ እኔ እምነት ቤተ ክርስቲያኒቱ የራስዋ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤቶች ማቋቋም አለባት:: በሌሎች የእምነት ተቋማት በኾኑ ትምህርት ቤቶች አስተምረን በእኛ ኮሌጆች ጥሩ ትምህርት እንዲያስተምሩልን መጠበቃችን ግራ ያጋባኛል:: ልከናቸው ተመልሰው የሚመጡቱም በመጠን ናቸው:: የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት እስከ ሌላን ድረስ የመምህራን እጥረትን በዋዛ የምንቀርፈው አይደለም:: በእኛ በኩል በድኅረ ምረቃ ትምህርታቸውን ለሚቀጥሉ መምህራን ተፈቅዶላቸው፣ ደመወዛቸው እየተከፈላቸው እንዲማሩ በቦርዱ ተወስኖአል:: ጥረቱ ተመልሰው መጥተው ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያገለግሉ ነው::

የቤተ ክርስቲያናችንን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያስተባብር አካል ያስፈልገናል:: ሁሉም ለየብቻው ስላሰበ ውጤታማ አንሆንም:: በመምሪያም ይሁን በኮሚሽን ደረጃ የምሁራን ኃይል ያለው፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችንን የሚያስተባብር አካል ያስፈልገናል:: በትክክለኛው ሞያ በተካነ ሰው ተገቢው የትምህርት አመራር መሰጠት አለበት:: ኮሌጆቹ ወደ ዩኒቨርስቲ ማደግ ይኖርባቸዋል፣ ሌሎቹም ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የኾኑ ክፍለ ትምህርቶች /የትምህርት መርሐ ግብሮች/ መከፈት አለባቸው::

ሊቀ ትጉሃን ላእከ እንደ ገለጹልን:- የአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ኮሌጅ በአሁኑ ወቅት የሚከተለው አስተዳደራዊ መዋቅር አለው:: በአስተዳደራዊ መዋቅሩ የኮሌጁ የበላይ ጠባቂ ቅዱስ ሲኖዶስና ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ናቸው:: በመከተል የአስተዳደር ቦርድ አለ:: የአስተዳደር ቦርድ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ከሊቃነ ጳጳሳት መካከል ነው የሚኾኑት:: የሚሾሙትም በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ነው:: በስድስቱ የትግራይ አህጉረ ስብከት የሚገኙ ሊቃነ ጳጳሳት የቦርድ አባላት



አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን



ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ

ይኾናሉ:: ቦርዱ ምሁራን ከኾኑ ምእመናን የተመረጡ ሁለት ተወካዩች ይኖሩታል:: በክልሉ ካሉት የመንግሥታዊ ተቋማት /ትምህርት ቢሮ፣ መቐለ ዩኒቨርስቲ/ ቤተ ክርስቲያናችን በልጅነታቸው የመረጠቻቸው በቦርዱ አባልነት ይካተታሉ:: አጠቃላይ የቦርዱ አባላት ቁጥር ዘጠኝ ነው:: ከአስተዳደር ቦርዱ ቀጥሎ የኮሌጁ የበላይ ኀላፊ የሚኾኑት የወቅቱ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ናቸው:: ከሊቀ ጳጳሱ ቀጥሎ ዲኑና በዲኑ የሚመራ የሥራ አመራር /ማኔጅመንት/ ኮሚቴ አለ፤ ኮሌጁን ያስተዳድራል:: በሌላ በኩል አካዳሚክ ኮሚሽን አለ:: እርሱም በተመሳሳይ በዲኑ የሚመራ ነው:: ከዲኑ ጀምሮ እንደ የሥራ ደረጃቸው የክፍሉ ኀላፊዎች አሉ::

የኮሌጁ ተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርታቸው ውጭ /በተጓዳኝ/ በሌሎች ዘርፎች ያላቸው ተሳትፎ /አገልግሎት/ ምን እንደ ሚመስል ሊቀ ትጉኃን ላእከ ሲያስረዱ:- «ይህ በይበልጥ ወደ ኮሌጁ ከመግባትህ በፊት በነበረህ እንቅስቃሴ ሊወሰን ይችላል::» ይላሉ:: የኮሌጁን ተሞክሮ ሲያመለከቱ በአንድ ወቅት የተወሰኑ ገዳማት ተመርጠው ለተመራቂ ደቀ መዛሙርት ተሰጥቷቸው በእነርሱ ላይ የጥናት ወረቀት እንዲያቀርቡ ይታዘዛሉ:: አንዳቸውም ሊጽፉ ግን አልቻሉም:: ከዚያ በኋላ ሁኔታውን ለማሻሻል ጥረት ተደርጓል::

በሌላ በኩል የክልሉ ማረሚያ ቤት ከኮሌጁ ጋር በጣም የቀረበ ግንኙነት አለው:: ደቀ መዛሙርቱ ብዙ አስተዋፅዖ እያደረጉ ነው:: ውጤታማ ኾኖም አግኝተነዋል:: እንዲያውም አንድ ጊዜ የወኅኒ ቤቱ ኀላፊ ደውለው:- «መኪና ብንሰጣችሁና በትግራይ ያሉ ወኅኒ ቤቶችን በአገልግሎታችሁ ብታዳርሱልን?» ብለው ነበር:: ወደ ኸኤስ.ኦ.ኤስሽ የሕፃናት መንደር እንሄዳለን:: ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለን:: በኮሌጁ እንቀስቃሴዎችን የማያስተባብሩ የተለያዩ ኮሚቴዎች አሉ:- «የስብከተ ወንጌል ኮሚቴ»፤ «የፀረ-ኤች.አይ.ቪ-ኤድስ ኮሚቴ»፣ «የስፖርት ኮሚቴ» .... አሉን:: በተለይ በስብከተ ወንጌል ደኅና እንቅስቃሴ እያደረግን ነው:: በየሳምንቱ ቅዳሜ በኮሌጁ ደቀ መዛሙርት መሪነት በደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል የሚካሄድ መርሐ ግብር አለ:: ገና በመደራጀትና በመቋቋም ላይ ለሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ በሠርክ የዐውደ ምሕረት መርሐ ግብሮች አገልግሎት ይሰጣል:: በማኅበረ ቅዱሳን የመቐለ ንዑስ ማእከል ጋርም መልካም የአገልግሎት ግንኙነት አለ:: እስከ አሁን ድረስ ደቀ መዛሙርቱ በየዓመቱ አንድ ጉዞ ያደርጋሉ:: ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም ወደ ላሊበላ ሄደው ነበር:: በጉዟቸው ላይ ፀረ - ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የተመለከቱ መልእክቶች ተላልፈዋል:: በመንገዳቸው ላይም በአላማጣ፤ በወልዲያ በመሳሰሉት አስተምረዋል፤ ሲመለሱም እንዲሁ:: በዘንድሮ ዓመት በመቐለ ከተማ የተከበረው የጥቅምት በዓል የደቀ መዛሙርቱ ተሳትፎ ስለ ነበረበት ከወትሮው የተለየ ድምቀት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነበረው፤ ደቀ መዛሙርቱ ሌሊቱን በሙሉ ሲያስተምሩሚ ሲዘምሩ አድረዋል፡፡ ይኸውም ከተወሰኑ አጥቢ ያ አብያተ ክርስቲያናት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ጋር በመቀናጀት በተደረገ ትብብር የተመቻቸ መድረክ ነበረ፡፡ ለታየው ለውጥ በማኅበረ ቅዱሳን የመቐለ ንኡስ ማእከልም የበኩሉን አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡ «የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኅብረት» ዓይነት የጋራ መድረክ ቢ ኖር መልካም ነው፡፡ ይኸውም ሥራ ዎችን ለመሥራት፣ ድጋፍና ርዳታ ለመጠየቅና ለመቀበል ይመቻል፡፡ የኮሌጁን ደረጃ በማሻል ሂደት ከሌሎቹ የቤተ ክርስቲናችን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር መሠረታዊ ሊባል የሚችል ግንኙነት አለን፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- ቀደም ሲል እንደ ጠቀስነው ኮሌጁን ለማቋቋም የተጠናውን ጥናት የመጨረሻ ይዘት የገመገመው የቅድ ስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ቦርድ ነው፡፡ ሥርዐተ ትምህርቱም ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በመጡ ባለሞያዎች ነው፡፡ የታየው፤ ይኸውም ራሳችንን ችለን ቦርድ እስከናቋቁም ድረስ ነው፡፡ ትልቁ ግንኙነታችን ግን በክረምት ወራት ለኮሌጁ መምህራን ሥልጠና ይሰጡልናል፡፡

የሥልጠናው ዓላማው የአስተማ ሪዎችን የማስተማር ክሂል ማዳበር፣ በሂደቱም ግንኙነታችንን ለማጠናከር ነው፡፡ እስከ አሁን ለሁለት ጊዜያት ያህል ሥልጠናው ተሰጥቷል፡፡ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅን ለኮሌጃችን አስተባባሪና አባት አድርገን ነው የምንቆጥረው፡፡ መምህራን እዚያው ሄደው ነው የሚሠለጥኑት፡፡ አሁን ቤተ ክርስቲያናችን ካሏት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተጨማሪ በየቦታው ተከፍተው የተለያዩ ነገር ግን የተደራጀ ሚና የሚጫወቱ ተቋማት ያስፈልጉናል፡፡

የኮሌጁ መምህራንና ተማሪዎች ከመደበኛው የመማር ማስተማር መርሐ ግብር ውጭ በጋራ በመኾን የሚያዘጋጇቸው የጥናትና የውይይት መድረኮች አሉን፡፡ አንዳቸው በስብከተ ወንጌል ዙሪያ ኾኖ የመቐለ ካህናትና የህገረ ስብከቱ ሠራተኞች ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር በመኾን የተካኼደው ዓውደ ጥናት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የመቐለ ዞን መስተዳድር፣ ሀገረ ስብከቱና ኮሌጁ በመተባበር በመቐለ ከተማ «ቤተ ክርስቲያንና ልማት ቤተ ክርስቲያንና ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ» በሚሉና በመሳሰሉት ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ዓውደ ጥናት ተካሂዶ ነበር፡፡ በቅርቡም ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በተመለከተ በኮሌጁ አስተባባሪነት ሌላ ዐውደ ጥናት ተከናውኗል፡፡

*ሐመር- ጥር/የካቲት፲፱፻፺፰ ዓ.ም.*

በክልል ትግራይ የድምፀ ወያነ ሬድዮ ኮሌጃችን በሚያከናውነው ተግባር ሁሉ ብዙ ጊዜ የአየር ሽፋን እናገኛለን፡፡ በስፖርት ዘርፍ ሳይቀር ተሳትፎ አለን፡፡ ለምሳሌ፡ጠ በእግር ኳስ እስከ ዓዲግራት ድረስ ሄደን ተጫውተናል፡፡ ዋና ዋናዎቹን መግለ ጼ ነው እንጂ ሌሎቹም መድረኮች አሉ፡፡

ተማሪዎቹ ጠዋት ጠዋት 12፡00 የአንድነት ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ በዐቢይ ጾም ግን በቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል መጻሕፍት ስለሚተረጎሙ ያንንን እንዲሰሙ ነው የምናደርገው፡፡ ተርጓሚው ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ካሣ ናቸው፡፡ ያንን መስማት ይኖርባቸዋል፡፡ በእሑድ ሰንበት በቤተ ክርስቲያን ያገለግላሉ፡፡ ከጠዋቱ ጸሎት በኋላ ከ10–15 ደቂቃ እርስ በርስ ይማማራሉ፡፡

ኮሌጁ በአሁኑ ወቅት ካሉበት ጉልህ ችግሮች መካከል ዋነኛው በቂ በጀት አለመኖሩ ነው፡፡ ተቋሙ በተለያዩ አካላት ተይዞ ቆይቷል፡፡ ቢ ሮ የለውም፡፡ ለቢሮ ታስቦ የነበረው ለመኝታ ቤት፣ ለመኝታ ቤት ታስቦ የነበረው ለሕፃናት ማሳደጊያ ኾኗል፡፡ ሕፃናት ማሳደጊያውም የቤተ ክርስቲያኒቷ ድርጅት ቢ ኾንም በስሙ ወዳለው ድርጅት እንዲያልፍ የተቀናጀ ጥረት ከለሌለ ውጤታማ አልኾነም፡፡ የተማሪዎች መጣበብ አለ፡፡

መጣበብ ብቻ ሳይሆን በክህነት ደረጃ ያሉ ወንዶች ከሴቶች ጋር ሲኖሩ ትልቅ ፈተና ይሆናል፡፡ በርግጥ በተጨባጭ ያጋጠመን ነገር የለም፡፡ ተቃራኒ ጾታዎች በዚህ ሁኔታ ተቀራርበው መኖራቸው ጥሩ አይደለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከ`ላፊዎቹ ጋር እንነጋገራለን፡፡

የበጀት ጉድለቱን ለመሸፈን ፈንድ ለማፈላለግ የልምድ ችግር አለ፡፡ ስንጀምር አብረውን የነበሩ ባለሞያዎች በብዙ መንገድ ከእኛ ጋር እንዳይቀጥሉ ተደርገዋል፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱን በጀቱን የቀረጹ አካላት ሁሉ ራቁ፡፡ በነባሩ አሠራራ ችን ደግሞ አጥንተን ጊዜ ወስደን የመሥራት ልምድ የለንም፡፡ የቤተ መጻሕፍት ግንባታ ኘላን በማኅበረ ቅዱሳን ከክፍያ ነጻ ዲዛየኑ ቢሠራ ልንም ተግባራዊ ለማድረግ ግን አቅሙ የለንም፡፡ በቅርቡ የኮሌጁን የኢንተርኔት ኔትወርክ ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር በመተባበር ዘርግተናል፡፡

<u>የኮሌጁ የወደፊት ርእይ</u>

- በአሁኑ ወቅት ኮሌጁ ላሉት መምህራን የውጭ ትምህርት ዕድል በማፈላለግ የመምህራንን ችግር ማቃለልና የውጭ አስተማሪዎች ከመጠበቅ መላቀቅ፤
- የልማትና የገቢ ማስገኛ ሥራ ዎችን ማለትም ክሊኒክ፣ ዳቦ ቤት፣ የልማት ቦታ፣ ወዘተ በማስፋፋት የበጀት ችግሩን ማቃለል
- በኮሌጁ የሚታዩት የቤተ መጻሕ ፍት፣ የቢሮ የመኝታ ክፍል ችግር ለማቃለል አዳዲስ ሕ ንፃዎችን በማሠራት ችግሮችን መቅረፍ
- በኮሌጁ ሥር የሚገኘው የአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ ውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጥ በማጠናከር ዋነኛ የኮሌጁ የገቢ ምንጭ ኾኖ እንዲ ያገ ለግል ለማድረግ ራሱን የቻ ለ ሕንፃ ማሠራትና ወደ 10+3 ማሸጋገር፡፡

በውይይታችን ማጠቃለያ ላይ የኮሌጁ የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ሐላፊ ሊቀ ትጉሃን ላእከ ታረቀ ቀጣዩን መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

የኮሌጁ ሕንፃ ከሠላሳ ዓመት በፊት ቢሠራም የመማር ማስተማር ሥራውን ከጀመረ እነኾ አራተኛ ዓመቱ ሲኾን የመጀመሪያ ፍሬዎቹን በ1996 ዓ.ም ለማስመረቅ በቅቷል፡፡ ኮሌጁ የመማር ማስተማር ሥራውን የቀጠለ ቢኾንም ብዙ ነገሮች ይጎድሉታል፡፡

ኮሌጁን ቤተ ክርስቲያኒቱ ጠ ንካራ ትምህርታዊ ተቋም ለማድ ረግና እንደ ቅዱስ ፓትርያርኩ ምኞት በዩኒቨርስቲ ደረጃ ለማሳደግ የቅዱስ ሲኖዶስ መንግሥታዊ የኾኑና መንግሥታዊ ያልኾኑ ተቋማት የለ ጋሽ ድርጅቶች፣ የኮሌጁ ማኅበረሰብ እንዲሁም ምእመናን በአጠቃላይ ሙሉ ትብብር ያስፈልገናል፡፡ ምኞ ታችን እውን ይሆን ዘንድ የሁሉም ልባዊ ድጋፍ እንዳይለየን ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

ከሊቀ ትጉሃን ጋር ያደረግ ነውን ቃለ ምልልስ እንደበቃን በእርሳቸው መሪነት በኮሌጁ ቅጽር ግቢ ያሉትን የመማሪያ፣ የመመገቢ ያ፣ የመኝታ፣ የአስተዳደር ክፍሎችና ቢሮዎች ተዘዋውረን የሚገኙበትን ሁኔታ ተመልክተናል፡፡ አንዳንድ የተቋሙ ደቀ መዛሙርትንም አነጋ ግረናል፡፡ ከእነዚህም መካከል የጉባኤ መምህራን የነበሩና ትምህርታቸውን ለማስፋፋት የገቡ እንዲሁም ከራቀው የአገራችን ክፍል መጥተው የተሰባሰቡ ይገኙበታል፡፡ የብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የግል ንብረቶችና ስብስብ ሥራዎች የሚታዩበትን ሙዚያም ለመጎብኘት ችለናል፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ሆኖ ከዚህ እትም ጀምሮ የተከፈተ ነው። ማኅበራችን ይህንን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ሲሆን፤ አጠቃላይ የሥራ ሂደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል እንዲደረግበት ሆኖ ነው።

# መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ለጠባይ ለውጥ

ጸጋዬ ጥላሁን /አ.አ.ዩ/

ባለፈው እትማችን የመንፈሳዊ ምክክር አገልግሎትን (Pastoral Counseling) ምንነት፣በራሱና ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ለማየት ሞክረናል። ከአመካካሪዎችና ከተመካካሪዎች የምምክር ግንኙነት አኳያም አንዳንድ ነጥቦችን ለማንሣ ሞክረናል። ቀጣዩን ክፍል እነኾ። መልካም ንባብ።

የምክክር አገልግሎት በተለይም መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ለሰው ልጆች ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በዐውደ ምሕረት በስብከት፣ በትምህርት ከምንሰጠው የሰው ልጆችን የመቅረጽና ዘላለማዊ መንገድን የማሳየት አገልግሎት በተጨማሪ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት እጅግ ወሳኝ ነው። ይኸውም በአሁኑ ወቅት ሰዎች በማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ችግሮች የተጠመዱበት ወቅት ስለሆነ ነው። ለምሳሌ፦ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክንያት የሰው ልጆች ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መጠኑ ይለያይ እንጅ በሥነ ልቡና የተጎዱ ናቸው። ታማሚውም፣ አስታማሚውም ተመርምሮ ነጻ መሆን አለመሆኑን ያወቀውም ያላወቀውም ይጨነቃል። ነጻ የሆነውም በሽታው እያስከተለ ስለአለው ጉዳት በማሰብ ይጨነቃል። በተለይም ደግሞ ሁላችንም የሥነ ልቡና ተጎጅዎች ነን። ስለሆነም የሥነ ልቡና ድጋፍ የሚሰጠን መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ያስፈልገናል።

ብዙ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ይህ አገልግሎት በስፋትና በተጠናከረ መልኩ በአባቶች ባለመሰጠቱ የግል ችግራቸውን በውስጣቸው አምቀው ያለ ደስታና ሰላም ይኖራሉ። በመጨረሻም ራሳቸውን ከአገልግሎት ያርቃሉ። ሌሎች ደግሞ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ጥሩ የመስማሪያ መስክ የሚያሳያቸው አጥተው መልካም ያልሆነ ምርጫ በመምረጥ ይጠፋሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ብዙዎች ያላቸውን ችሎታና አቅም ሳይጠቀሙበት ጊዜያቸውን ያባክናሉ። ይህም ጸጋቸውን አለማወቃቸው ነው። በዚህ ምክንያት «እኔ የማልጠቅም ነኝ፤ ምንም ነገር የለኝም» ወዘተ በማለት ራሳቸውንና እግዚአብሔርን ሲወቅሱ ይደመጣሉ። በመሆኑም በነፍስም በሥጋም ይጎዳሉ።

የሕይወት /የኑሮ መስመራ ቸውን/ ለቀው ሲሮጡ ከመሮጫው መስመር ይወጣሉ። ባላቸው ጠንካራ ጎን ተጠቅሞ የሚመልሳቸው ስለሌለ ብዙዎች ለዘርፈ ብዙ ችግር ተዳርገዋል። ስለሆነም ዘመኑን የሚዋጅ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት እጅግ ወሳኝ ነው።

የሚከተሉት ነጥቦች ለአገልግሎቱ አስፈላጊነት ተጨማሪ ነጥቦች ናቸው።

1. ሰዎች ሁሉ የየራሳቸው ደካማ ጎን ስላላቸውና ምናልባትም ያ ደካማ ጎናቸው ለራሳቸው ስለ ማይታያቸው፣ ለብቻቸው መወጣት የማይችሉት ችግር ስለ ሚያጋጥማቸው፣ ረዳት ስለሚያስፈልጋቸው፤

2. የሰው ልጅ ከጥንተ ተፈጥሮው ጀምሮ የመረዳዳትና የመመካከር ተፈጥሮ ስላለው «...ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም።» እንዳለ። /ዘፍ.2÷2-18፤ ገላትያ 6÷1/።

3. ብዙውን ጊዜ በግል /ቁጥራቸው አነስተኛ በሆኑ ተመካካሪዎችና አመካካሪ/ የሚካሄድ በመሆኑ የአንድን ሰው ችግር በጥልቀት ለመመርመር ያስችላል። እንዲሁም የሰውን ችሎታ፣ አቅም፣ ፍላጎት፣ ጥንካሬ፣ ልምድና ሌሎች ነገሮችን ከሌሎች አገልግሎቶች በበለጠ መልኩ ትኩረት ለመስጠት ያስችላል።

4. በአደባባይ የሚደረጉ አገልግሎቶች /ለምሳሌ፦ ምክራዊ ስብከት/ እያንዳንዱ ሰው ስለ ሚያጋጥመው የራሱ ችግር መፍትሔ ላያገኝ ይችላል። ምክንያቱም የሰዎች የግል

ችግርና ፍላጎት፣ ችግርን ለመቋቋም ያላቸው ችሎታና አቅም እንዲሁም ልምድ የተለያየ ስለሆነ ነው። ብዙ ሰዎችን በአንድ ላይ በማስተማር የእያንዳንዱን ሰው የግል ፍላጎት ማወቅና ያለበትን ችግር ዐውቆ ለችግሩ መፍትሔ ለመፈለግ እጅግ ይከብዳል። ፍላጎታችን፣ ችሎታችን፣ የእምነት ጥንካሬያችን፣ ልምዳችን፣ የትምህርት ደረጃችን፣ ሥራችንና የመሳሰሉት እንደ የራሳችን የተለያዩ ስለሆኑ ለሁላችንም በአንድ ላይ መፍትሔ መስጠት አይቻልም። ስለሆነም ይህን ክፍተት ለመሙላት አገልግሎቱ አስፈላጊ ነው።

5. ምስጢራዊ በሆነ መልኩ ስለ ሚካሄድ፦ በዚህ አገልግሎት የሚደረገው ውይይት ከችግሩ ባለቤት ከአገልግሎት ተጠቃሚው /Counselee/ ፈቃድ ውጪ አመካካሪው የተመካካሪውን ሐሳብና ችግር ለሌላ ሰው የመግለጥ መብት የለውም። ይህም በመሆኑ በዚህ አገልግሎት ምስጢራዊ ካልሆኑ እጅግ ምሥጢራዊ እስከ ሆኑ ችግሮች ድረስ አመካካሪውና ተመካካሪው ሊወያዩና ለችግሩ መፍትሔ ሊያፈላልጉ ይችላሉ። ሰዎች በዐውደ ምሕረት /በጉባኤ/ ከሚሰጡ ትምህርቶች መልካም መፍትሔ ሊያገኙ ይችላሉ። ነገር ግን በአደባባይ የማይነገሩ /የግል ጉዳዮች/ ይኖራሉ። በእነዚህ ችግሮች ዙሪያ በአደባባይ መወያየት አይቻልም። በመንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ግን በነዚህ ችግሮች ላይም መወያየትና መፍትሔ ማግኘት ይቻላል።

6. ***አገልግሎቱ የሁለትዮሽ ውይይት /two-way communication/ ስለሆነ፦***

ይህም ማለት አመካካሪውና ተመካካሪው ተራ በተራ ይነጋገራሉ። ይህ በመደበኛ የስብከት ወንጌል መርሐ ግብር /በትምህርት ጊዜ/ ሊደረግ አይችልም። በምክክር ጊዜ ተመካካሪው ሐሳቡን /ችግሩን/ ለመግለጽ ሰፊ ጊዜ አለው። እንዲያውም በውይይቱ ወቅት 3/4ኛ /75 በመቶ/ የሚሆነውን ሰዓት የሚጠቀመው ተመካካሪው ነው። ስለ ችግሩ ብዙ ነገር እንዲናገር የሚጠበቅበት ተመካካሪው ነው።

7. **መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለሆነ**





© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አገልግሎቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ቀደም ብለን ባየናቸው ርእሶች ላይ ለማየት ሞክረናል:: ለምሳሌ:- ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ምዕ.12 ቁ 6-8 ላይ «... የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ ...» በማለት አገልግሎቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጸጋ መሆኑን ተናግሯል::

8. አገልግሎቱን በማንኛውም መስጠት ይቻላል:: ይህም ሲባል ያለንን ነባራዊ ሁኔታ ወይም የሀገራችንን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መኾን ይገባዋል:: አገልግሎቱ የተሟላና ምቹ ቦታ ያስፈልገዋል:: በአሁኑ ወቅት ግን አገልግሎቱን መንፈሳዊ አመካካሪው /ካህኑና/ ተመካካሪው ለውይይታቸው ይመቻል ባሉት ቦታ ማድረግ ይችላሉ:: ለምሳሌ:- በቤት ውስጥና ሆስፒታል በመሔድ ማጽናናትና አገልግሎቱን መስጠት ይቻላል:: በዋናነት ግን በቤተ ክርስቲያን አጥር ግቢ ውስጥና ጸጥታቸው በተጠበቁ ቦታዎች አገልግሎቱን መስጠት ይቻላል::

ሕዝቡን ለማስተማር የግድ ዐውደ ምሕረት /ሰፊ ቦታ፣ የድምፅ ማጉያና ሌሎችም ነገሮች/ ያስፈልጉናል:: የምክር አገልግሎቱን ለመስጠት ግን እነዚህ ነገሮች አያስፈልጉንም::

በአጠቃላይ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ከዚህ በላይ በተዘረዘሩትና ባልተዘረዘሩት ሌሎች በርካታ ምክንያቶችና ለሰው ልጆች ሁሉ በተለይም ለእኛ ለክርስቲያኖች አስፈላጊነቱ ከምንም በላይ የጎላ ነው::

## መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት /Pastoral counseling service/ ከሌላው በምን ይለያል?

መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ሰዎች /ተመካካሪዎች/ ለገጠማቸውን ችግር ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን ሕገ እግዚአብሔርን መሠረት በማድረግ እንዲሁም የምክክር አገልግሎቱን ፅንሰ ሐሳብና ስልት በመከተል መፍትሔ የሚያገኙበት አገልግሎት ነው:: ዓላማውም ተመካካሪዎች ከአለባቸው ችግር በራሳቸው ተላቀው፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ጠቃሚ ዜጎች እንዲሆኑ መርዳት ነው:: በአጭሩ ከበደል፣ ከኃጢአትና ከጥፋተኝነት ስሜት እንዲላቀቁ ማድረግ ነው::

መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ከሌሎች የምክክር አገልግሎት ዓይነቶች በብዙ መልኩ የተለየ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ ግን የሚከተሉት ናቸው::

1. *የራሱ የሆነ ፅንሰ ሐሳብ አለው /Unique Assumption/:-* በመንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ስለ እግዚአብሔር ተራዳኢነት፣ ስለ ንስሐ፣ ስለ ሰው ተፈጥሮ፣ ስለ ኃጢአት፣ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር፣ ስለ ሞት፣ ስለ ተስፋና የመሳሰሉት ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ለተመካካሪዎች አገልግሎት ይሰጣል:: ሃይማኖትን፣ ቃለ እግዚአብሔርንና ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን ከሌሎች በተለየ መልኩ እንደ ፅንሰ ሐሳብ ይጠቀማል:: ስለሆነም አመካካሪው /ካህኑ/ እነዚህን መሠረት በማድረግ ተመካካሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኙ በማድረግ፣ ከአለባቸው ችግር እንዲላቀቁና ለሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን በመገዛት ራሳቸውንና ሌሎችን የመጠርዳት አቅም እንዲኖራቸው ያደርጋል::

2. *የተለየ ዓላማ አለው /unique goals/:-* እንደ ሌሎቹ የምክክር አገልግሎቶች መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎትም ተመካካሪዎች የጠባይ ለውጥ እንዲያመጡ፣ በጎ አመለካከት ለራሳቸውና ለሰዎች እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ስለ ማኅበራዊ ግንኙነት ክህሎት፣ ዋጋ ስለ መስጠት፣ ስለ ችግር አፈታት ክህሎት፣ በራስ ስለ መተማመን እና ራስን ስለ መሆን፣ ራስን ስለ ማወቅ እና የመሳሰሉትን ነገሮች ሰዎች እንዲያዳብሩ ያደርጋል:: እነዚህ ዓላማዎች አገልግሎቱ ከሌሎች የምክክር ዓይነቶች ጋር የሚጋራቸው ዓላማዎች ናቸው:: ከዚህ ውጭ ግን መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት አመካካሪው /ካህኑ/ የተመካካሪውንም መንፈሳዊ ዕድገት ዓላማ አድርጎ ይነሣል:: በመንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት መካሪው ግብ አድርጎ የሚሣው ተመካካሪዎች በሥጋዊ ሕይወታቸው ብቻ እንዲመቻቸው ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ጠንክረው ዘላለማዊ ሕይወትን እንዲያገኙ ነው:: ስለሆነም በዚህ አገልግሎት የተመካካሪው ፍላጎትና ችግር የሚፈተሸው ቃለ እግዚአብሐ ር ን መሠረት በማድረግ ነው:: በርግጥም ቃለ እግዚአብሔር በሥጋዊም በመንፈሳዊም ሕይወታችን የተሻልን ሰዎች እንድንሆን ነው የሚነግረን::

3. ከሌሎች የተለየ ስልት ይጠቀማል /unique methods/:- መንፈሳዊም ሆነ ሌሎች የምክክር አገልግሎቶች ብዙ ተመሳሳይ የሆነ የምክክር ስልት /methods, techniques/ ይጠቀማሉ:: ሆኖም ግን ከሌሎች በተለየ መልኩ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት የሚጠቀምባቸው ስልቶች መጽሐፍ ቅዱስንና ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን መሠረት ያደረጉ ናቸው:: በዚህ አገልግሎት ውስጥ ተመካካሪውና አመካካሪው በሚገናኙበት ጊዜ ውይይታቸውን ከመጀመራቸው በፊት እግዚአብሔር በመካከላቸው ይገኝ ዘንድ በጸሎት ይጠይቃሉ:: እንደዚሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማለትም ከሚወያዩበት አጀንዳ ጋር የሚያያዙቱን በማጣቀስ እንዴት ያንን ችግር መፍታት እንደ ሚችሉ ይጠቅማሉ:: በመጨረሻም ተመካካሪው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተሳታፊ እንዲሆንና የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ተካፋይ እንዲሆን አመካካሪው /ካህኑ/ ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

4. አመካካሪው የተለየ ጠባዕያት አሉት፤ መንፈሳዊ አመካካሪ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርቷንና ሥርዐቷን እንደዚሁም የምክክር ቴክኒኮችን/ ስልቶችን/ ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆን አለበት:: አለበለዚያ የሚሰጠው አገልግሎት ውጤታማ አይሆንም::

የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱ፣ ክብካቤው እና ምክሩ እንዲሁም በወቅቱ ይፈጽማቸው የነበሩ የትሕትና ሥራዎች፣ ለተቸገሩት ያለው አመለካከት እና ሌሎቹም ሥራዎቹ አንድ መንፈሳዊ አመካካሪ አጥብቆ ሊከተላቸው የሚገባ መመሪያዎቹ ናቸው:: ጌታችን በፍጹም ትሕትና እኛን /የሰው ልጆችን ሁሉ/ እንዲሁ÷ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወዶናል፤ ረድቶናል፤ አድኖናል:: ጌታችን በዚህ ምድር ላይ እያለ:- የተቸገሩትን ይረዳቸው ነበር:: የታመሙትን ይፈውሳቸው ነበር:: ተስፋ የቆረጡትን ያበረታታቸው፣ ተስፋቸውን ያለመልምላቸው ነበር:: ወደ ጨለማ የሔዱትን ወደ ብርሃን ይመልሳቸው ነበር::

በአካሔዳቸው መጥፎ የሆኑትን አቅጣጫቸውን ያስተካክልላቸው ዘንድ ያስተምራቸውና ይመክራቸው ነበር:: በጎ የሆነውን ጠባይ ይለማመዱት ዘንድ ያግዛቸውና ሞራል ይሰጣቸው ነበር::

ሰዎች እንድናዳምጣቸው እንድንመቻቸውና እንድናወያያቸው ይፈልጋሉ:: ከመምከራችን፣ ከማስተማራችን፣ ወይም ደግሞ ችግሩን ይጋፈጡት ይቀበሉት ዘንድ ከመንገራችን በፊት በአጽንዖት እንድናዳምጣቸው ይፈልጋሉ:: አንድ መንፈሳዊ አመካካሪም ሰዎች በኤች.አይ.ቪ /ኤድስም ይሁን በሌሎች ችግሮች ዙሪያ የሚፈለገውን የጠባይ ለውጥ እንዲያመጡለት ከፈለገ መከተል ያለበት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፈለግ ነው:: ሁሉንም የምክክር አገልግሎት መርሖዎች ጌታችን በተግባር አሳይቶናል::

ይቆየን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# መርሳት

/ኃይለ ገብርኤል ዘሐና/

የማውቃቸው ሁለት ጓደኛሞች አሉ:: አፈር ፈጭተው ውኃ ተራጭተው አብረው ያደጉ ናቸው:: አብዛኛውን ጊዜ አንድ ላይ ከመታየታቸው የተነሣ ለብዙዎች እኅትማማቾች መስለው ይታያሉ:: ይህ ዓመታትን ያስቆጠረ የአብሮ አደግ ጓደኝነታቸው ችግር እንደ ገጠመው ሰምቼ መንሥኤውን ሳጣራ «መርሳት» መሆኑን ተረዳሁ:: አንደኛዪቱ በጣም ትረሳለች:: ከመርሳትዋ የተነሣ በሥራ ገበታዋና ከበላይ ሓላፊዎችዋ ሳይቀር ችግር እየተፈጠረባት ነው:: ለመሆኑ መርሳት ምንድን ነው? ምክንያቱና መፍትሔዎቹስ?

መርሳት አንድን ነገር መዘንጋት ነው:: ልንሠራው የሚገባንን ሥራ ባለማስታወስ ወይም በመዘንጋት ሳንሠራው ስንቀር ይህ ሁኔታ መርሳት ይባላል:: ሰዎች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ የሚጠቅማቸውንም ሆነ የሚጎዳቸውን ነገር ሊረሱ ይችላሉ:: ሰዎች ከሚረሷቸው ነገሮች መካከልም:-

ሀ. <u>እግዚአብሔርን መርሳት</u>:-

ሰዎች በዚህ ዓለም ሲኖሩ እግዚአብሔርን ይረሱታል:: እግዚአብሔርን መርሳት ሲባልም ህልውናውን፣ ጥበቃውን፣ መግቦቱን፣ ውለታውን ፍርዱን መርሳት ነው:: እስራኤል ወደ ምድረ ርስት ሲጓዙ ብዙውን ጊዜ ያጉረመርሙና ተስፋ ይቆርጡ ነበር:: ሲብስም መሪያቸው ሙሴን ሊወግሩት ድንጋይ ያነሡ ደግሞም ወደ ግብጽ እንመለስ እስከ ማለት ይደርሱ ነበር:: እንዲህ እንዲሉ ያደረጋቸው እግዚአብሔርንና ሥራውን መርሳታቸው ነው::

ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከምድረ ፋራን ምድረ ርስት ከነዓንን ይሰልሉ ዘንድ ዐሥራ ሁለት ሰላዮችን ላከ:: ሊሰልሏት የተላኩባት የከነዓን ምድር እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ማርና ወተት የምታፈስ ናት:: የወይኑ ዘለላ የስንዴው ዛላ የሮማንና የበለሱ ፍሬ ያማረ ነበር:: ይሁን እንጂ ዐሥሩ ሰላዮች በምድሪቱ የሚኖሩ ረጃጅም ሰዎችን ባዩአቸው ጊዜ ተስፋ ቆረጡ:: በጸናች እጅ በተዘረጋች ክንድ ባሕር ከፍሎ ጠላት አሥጥሞ ከባርነት ነጻ ያወጣቸውን እግዚአብሔርን ረሱት:: ከእነርሱ ጋር ያለውንና የሚሳነው የሌለውን እግዚአብሔርን በመዘንጋት «እኛ በከነዓናውያን ዐይን እንደ አንበጣ ነን» በማለት ሕዝቡ «አለቃ ሹመን ወደ ግብጽ እንመለስ» ብሎ ተስፋ እስኪ ቆርጥ አደረሱት:: ዘኁል.13÷10-14::

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ወቅት ደቀ መዛሙርቱን «እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ ምን ይሆናል?» እንዲሉ ያደረጋቸው የእግዚአብሔርን መግቦት መርሳታቸው ነው:: ደቀ መዛሙርቱ እስራኤላውያን ናቸው:: ቀድሞ በኦሪት እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው በምድረ በዳ ለአርባ ዓመታት ሙሉ መናን ከደመና እያወረደላቸው እንደ መገባቸው ያውቃሉ:: ይሁን እንጂ በዘመናት ሁሉ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን መግቦት ረስተውታልና «እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆናል?» አሉ:: ዮሐ.6÷5-14::

የአክአብ ልጅ አካዝያስ በእስራኤል ላይ በሰማርያ ነገሠ:: አባቱ አክአብ በተጓዘበት የጥፋት ጎዳና ተጓዘ:: እግዚአብሔርን ትቶ ሌሎች አማልክትን አመለከ:: በዚህም የሚያስተውልበትን አእምሮ አጣ:: ከዐይነ ርግቡ ወድቆ በታመመበት ወቅት የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን እንዲጠይቁለት መልእክተኞችን ላከ:: ይህን ያደረገው መግደልም ማዳንም የሚቻለውን የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን ህልውና በመርሳቱ ነው:: ለዚህ ነው ነቢዩ ኤልያስ «የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን ትጠይቁት ዘንድ የምትሄዱት በእስራኤል ዘንድ አምላክ ስለሌለ ነውን?» በማለት የገሠጻቸው:: 2ነገ.11-4::

ቅዱስ ዳዊትም እስራኤል እግዚአብሔርን÷ ያደረገላቸውን መልካም ሥራ ይዘነጉት እንደ ነበረ: - «በሕጉም ለመመላለስ እንቢ አሉ:: መልካም ሥራውንና ያሳያቸውን ተአምራት ረሱ» ሲል ገልጧል:: ይህ እግዚአብሔርንና ሥራውን መርሳታቸው ነው ብዙውን ሕዝብ በምድረ በዳ ለመቅረትሚ በኋላም ዘመን ተማርከው ወደ ፋርስ ባቢሎን ለመውረድና ለሰባ ዘመን ሥቃይ የዳረጋቸው:: መዝ.77÷10–11:: እግዚአብሔርም አስቀድሞ በነቢዩ ሙሴ አንደበት «ዛሬ እኔ አንተን የማዝዘውን ትእዛዙንና ፍርዱን ሥርዓቱንም ባለመጠበቅ አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ፤ ... አምላክህንም እግዚአብሔርን ብትረሳ÷ ሌሎችንም አማልክት ብትከተል ብታመልካቸውም ብትሰግድላቸውም ፈጽሞ እንድትጠፉ እኔ ዛሬውኑ እመሰክርባችኋለሁ» በማለት የተናገረውን እግዚአብሔርን መርሳት ሰውን ለከፋ ጉዳት የሚዳርገው በመሆኑ ነው:: ዘዳግ.8÷11-20::

ለ. <u>ወገንን መርሳት</u>

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ወገናቸውን ይረሳሉ:: ወገንን መርሳት ሲባልም በደስታውም ሆነ በሐዘኑ ስለ ማጣቱም ሆነ ስለ ማግኘቱ ወገንን አለማሰብ÷ ልቡናን በወገን ላይ ማደንደን ነው:: ሰዎች በዚህ ዓለም ሲኖር በመተሳሰብና በመረዳዳት እንዲኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: በመሆኑም ነው :-«ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚል አምላካዊ መመርያ የተሰጠው:: ዘሌዋ.19÷18:: ይህን መሰል አምላካዊ መመርያ ቢሰጥም ከራስ ወዳድነት፣ ካለማወቅ፣ ተስፋ ከመቁረጥ፣ በጊዜያዊ ደስታ ከመደለል የተነሣ ሰዎች ወገናቸውን ይረሳሉ::

እስራኤል ተማርከው ባቢሎን በወረዱ በኻያኛው ዓመት በሱሳ ግንብ የነበረው ነህምያ በንጉሡ አርጤክስስ ፊት የጠጅ አሳላፊ ነበር:: ምንም እንኳን በባዕድ አገር ክብር አግኝቶ በንጉሡ ፊት ቆሞ ቢያገለግልም የኢየሩሳሌም ጉዳይ ያሳስበው ነበር:: በመሆኑም አንዳንድ ከምርኮ የቀሩ ሰዎችን ዜና የሚነግሩት ሲያገኝ የትሩፋንን ነገር፣ የቤተ መቅደሱን የኢየሩሳሌምን ቅጥር ጉዳይ አጥብቆ ይጠይቅ ነበር:: በስተመጨረሻም የልቡናውን አሳብ ለንጉሡ ነግሮ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ይሠራ ዘንድ÷ የፈረሰውን ሥርዐት ያድስ ዘንድ በተነሣበት ወቅት የምርኮ አገር ኑሮ የጠማቸው፣ የወገናቸው ፍቅር ከልቡናቸው የወጣላቸው አንዳንድ ሰዎች የነህምያን በጎ አሳብ «ይህ የምታደርገት ነገር ምንድን ነው? በውኑ በንጉሡ ላይ ትሸፍቱ ዘንድ ትወዳላችሁን?» በማለት ተቃወሙት:: ነህ.1÷1፤ 2÷20::

የያዕቆብ ልጆች ወንድማቸውን ተመቅኝተው ሸጠው ለባርነት ከዳረጉትና አባታቸውንም «ልጅህን ክፉ አውሬ በላው» በማለት ለመረረ ሐዘን ከዳረጉት በኋላ ወንድማቸውን ፈጽመው ረስተው የራሳቸውን ኑሮ ለማመቻቸት ይጥሩ ነበር:: ከዮሴፍ ጋር በግብጽ ምድር በወኅኒ ቤት ታስሮ ክፉውንና ደጉን አብሮ ያሳለፈው ግብጻዊ ከወኅኒ ቤት እንደ ወጣ ያን የመከራ ጊዜ ወዳጁን ጻድቁ ዮሴፍን ረሳ:: ዘፍ.405-23:: የራሳቸው ጉድለት ሲመላ የወገናቸው መከራ የማይታያቸው፣ ቢታያቸውም የወገን



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ፍቅር ማጣት እንደ በረዶ ስሜታቸውን ያቀዘቀዘባቸው ይኖራሉ::

እስራኤል በንጉሥ አርጤክስስ ወዳጅ በሐማ መሠሪነት የሞት ዐዋጅ በታወጀባቸው ጊዜ የአስቴር አጎት የነበረው መርዶክዮስ የተናገረው ነገር ወገንን መርሳት እንደ ሌለብን ያስረዳናል:: «አንቺ በንጉሥ ቤት ስለሆንሁ ከአይሁድ ሁሉ ይልቅ እድናለሁ ብለሽ በልብሽ አታስቢ:: በዚህ ጊዜ ቸል ብትዪ ዕረፍትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ሥፍራ ይሆንላቸዋል:: አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ::» መጽ.አስቴ.4÷13-14:: መርዶክዮስ ይህን መልእክት ለአስቴር የጻፈው ለጊዜው የንጉሥ ሚስት በመሆኗ ባላት ብልጥግና ተደልላ ወገኖችዋን እንዳትረሳ ነው:: በዚህም ቃል መሠረት አስቴር የወገኖቿ እልቂት አሳስቧት በጾም በጸሎት ፈጣሪዋን በመለመን ከጥፋት እንዲድኑላት አድርጋለች::

ቅዱስ ዳዊትም ወገንን በማሰብ እንድንጸና «ኢየሩሳሌም ሆይ÷ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ፤ ባላስብሽ ምላሴ በጉሮሮዬ ይጣበቅ:: ከደስታዬ ሁሉ በላይ ኢየሩሳሌምን ባልወድ» በማለት አርአያውን ሰጥቶናል:: መዝ.136÷5-6::

**ሥጋውያን መሪዎችም ሲሾሙ እንደ የእምነታቸው ሕዝቡን በቅንነትና በትጋት ሊያገለግሉ፣ ለሀገር ዕድገትም ሊሠሩ ቃል ይገባሉ:: ይህ አደራና ቃል ሲታመኑበት ክብር የሚያሰጣቸው÷ ከረሱትና በተቃራኒው መንገድ ከተጓዙ ደግሞ መከራን የሚያመጣባቸው ይሆናል::**

## <u>ሐላፊነትንና የገቡትን ቃል ኪዳን መርሳት:-</u>

በፈቃደ እግዚአብሔር በሰዎች ምርጫ ሰዎች ለተለያዩ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሐላፊነቶች ይመረጣሉ:: እነዚህ ሰዎች የተመረጡበትን ወይም በ^ላፊነት የተረከቡትን አደራ መፈጸም ይጠበቅባቸዋል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ^ላፊነታቸውን መወጣታቸውን ይረሳሉ::

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ 16÷1-9 በምሳሌ የገለጠው መጋቢ ሐላፊነታቸውን ስለ ሚረሱ ሰዎች ያስረዳል:: በምሳሌው የተገለጠው ባዕለጸጋ ቤተሰቡንና ሀብቱን የሚቆጣጠርለትና የሚያስተዳድርለት መጋቢ ሾመ:: መጋቢው ግን በመጋቢነት መዓርግ ከመሾምና በስሙ ከመጠራት በስተቀር የሚጠበቅበትን ግዴታ አላስተዋለም:: ይልቁንም የጌታው ቤተሳቦች በረኀብ፣ በጥምና በእርዛት ሲሠቃዩ እርሱ የጌታውን ገንዘብ ይበትን ነበር:: ባዕለጸጋው ጠርቶ ወደፊት ለእኔ መጋቢ ልትሆን አትችልምና የመጋቢነትህን ሐሳብ አስረክበኝ እስኪለው ድረስ ሐላፊነቱን ረስቶት ነበር::

እግዚአብሔር ከብዙዎች መካከል ጥቂቶችን አስነሥቶ በ^ላፊነት ወንበር የሚያስቀምጠው ከላይ እንደ ተገለጠው አንቱ ተብለው ከሰዎች ውዳሴን እንዲቀበሉበት ወይም የተሻለ ገቢ እንዲያገኙበት አይደለም:: ነገር ግን እነርሱ ከክፉ ርቀውና ተጠብቀው የሕዝቡን ሁለንተናዊ ሕይወት እንዲጠብቁና እንደ አባትና እንደ እናት ሆነው ሐላፊነት የተቀበሉባቸውን ወገኖች ሥራ በመልካም እንዲመሩ ነው::

በራእየ ዮሐንስ ከተገለጡት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የአምስቱ ማለትም የኤፌሶን፣ የጴርጋሞን፣ የትያጥሮን፣ የሰርዴስና የሎዶቅያ አብያተ ክርስቲያናት አለቆች ተወቅሰው÷ ተገሥጸው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል:: እነዚህ አለቆች በግላቸው መልካም ሕይወት እንደ ነበራቸው ተጠቅሷል:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ምእመናኑን በእምነትና በምግባር የመጠበቅ ሐላፊነታቸውን ስለ ረሱና ቸላ ስላሉ ተወቀሱ:: ራእ.2÷1፤ 3÷22::

ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሥራዎችን ለመፈጸም ቃል የሚገቡና ሥራቸውን የሚረሱ አሉ:: ሰውን ከሌሎች ፍጡራን ከሚለዩት ነገሮች መካከል ቃሉን መጠበቅ መቻሉ ነው:: ከቃል የወጣ መሐላ፣ ውል፣ ስእለት በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተፈጻሚነቱ ይጠበቃል:: በመሆኑም ነው እግዚአብሔር በሙሴ አድሮ:- «ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ፈጽሞ ይሻዋልና ኃጢአትም ይሆንብሃልና መክፈሉን አታዘግይ፤ በአፍህ የተናገርኸውን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር በፈቃድህ ተስለሃልና ከከንፈርህ የወጣውን ታደርግ ዘንድ ጠብቅ» በማለት ሰው በማንኛውም መስክ ሊፈጽመው የገባውን ቃል ኪዳን እንዲፈጽም ተናግሯል:: ዘዳግ.23÷21-23:: ጠቢቡ ሰሎሞንም «የሰነፍ ድምፅ በቃሉ ብዛት ይሰማል:: ሰነፎች ደስ አያሰኙትምና ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ፤ የተሳልኸውን ፈጽመው::» በማለት የገቡትን ቃል መርሳትና አለመፈጸም ስንፍና መሆኑን ተናግሯል:: መክ.53-5::

በዓለማችን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲሾሙ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 እና 15 ተነቦ ይተረጎማል:: ይህም የተጣለባቸውን አደራ ያስረዳል:: ሥጋውያን መሪዎችም ሲሾሙ እንደ የእምነታቸው ሕዝቡን በቅንነትና በትጋት ሊያገለግሉ፣ ለሀገር ዕድገትና ሥራም ሊሠሩ ቃል ይገባሉ:: ይህ አደራና ቃል ሲታመኑበት ክብር የሚያሰጣቸው÷ ከረሱትና በተቃራኒው መንገድ ከተጓዙ ደግሞ መከራን የሚያመጣባቸው ይሆናል::

ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ሲመረቁ እጃቸውን አንሥተው ሀገራቸውንና ወገናቸውን በሞያቸው በትጋትና በታማኝነት ሊያገለግሉ ቃል የሚገቡ ሰዎች በተለያዩ የብዙኀን መገናኛ እናያለን:: እነዚሁ ሰዎች የተጣለባቸውን ሀገራዊ አደራ የገቡትን ቃል ኪዳን ረስተው የግል ጥቅማቸውን ብቻ ለማካበት የሚሯሯጡበት አደራቸውን የሚፈጽሙበትን ጊዜ በዋዛ የሚያባክኑበት ሁኔታ በርካታ ነው::

ቅዱስ ጴጥሮስን በሮም አደባባይ ቁልቁል ለመሰቀል ያበቃው አባግዕ ምእመናንን እንዲጠብቅ አደራ በተሰጠው ወቅት:- «ጌታ ሆይ÷ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» በማለት የገባውን ቃል ኪዳን ማስታወሱ ነው:: ዮሐ.21÷15-19:: ኢያሱ እስራኤል ዘሥጋን ወደ ምድረ ርስት ሊያገባ የተመረጠ መስፍን ነበር:: ከእግዚአብሔር የተቀበለውን አደራም በአግባቡ እየተወጣ የነበረ ነው:: ይሁን እንጂ ሠላሳ ስድስት የሚሆኑ እስራኤላውያን በጋይ ሰዎች ተመትተው በሞቱበት ወቅት ከጧት እስከ ማታ ድረስ በግንባሩ ተደፍቶ ስለ ሕዝቡ ለመነ:: ይህም ሐላፊነትን የተቀበሉ ሹመኞች በሕዝቡ ሐዘንና ደስታ ወቅት ማድረግ ያለባቸውን ያሳያል:: ኢያሱ.1÷1-9::

በሥርዐተ ተክሊል በቅዱስ ጋብቻ ትዳርን መሥርተው የትዳር አጋራቸውን ድካም መታገሥ÷ መቻል÷ ማገዝ ተስኗቸው ትዳራቸውን የሚጠሉ÷ ትዳሩ የሚፈርስበትን ምክንያትና ዕለት የሚጠባበቁ ሰዎችም ቃላቸውን የዘነጉ ናቸው:: እነዚህ ሰዎች አስቀድመው ተዋደው ተፋቅቀደው የተጋቡ ናቸው:: በጋብቻቸው ዕለትም በታቦቱ ፊት ቆመው ወንጌልና መስቀል ጨብጠው ካህኑን ምስክርነት ይዘው እርሱ ቢከሳ ብትመክን ሳይተዋት ቢጠቀር



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ሳትተወው፣እርስዋ ብትሰንፍ ቃል ይገባሉ። ይሁን እንጂ ይህ ቃል ኪዳን ተዘንግቶ ÷የብዙዎች ትዳር በትንሽ ውይይት ሊፈታ በሚችል ግጭት የሚፈርስበት ሁኔታ አለ። በሌላ በኩልም የድንግልና ሕይወት የገቡት ቃል ሊጠበቅበት የሚገባው ነው። የድንግልና ሕይወትን ሰዎች የሚመርጡት ያለልቡና መከፋፈል እግዚአብሔርን ለማገልገል እንደ ሆነ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ይልቁንም የቅዱስ ጳውሎስ ምክር ያስረዳል። 1ቆሮ.7÷32-35። ድንግልና ለኃጢአትና ለክፋት ሞተው ለጽድቅ ሕያው የሚሆኑበት ኑሮ ነው። ይህ ደግሞ የተለያዩ መከራዎችን መታገሥንና መቻልን ይጠይቃል። ይህ ትዕግሥት የሚኖረው ራስን ለእግዚአብሔር በማጨት በድንግልና ለማገልገል የገቡትን ቃል ማሰብ ሲኖር ነው። ይህ ቃል ከተረሳ ምንኩስናው ÷ብሕትውናው ይፈርሳል፤ ቆቡም ይወልቃል።

### መ. ኃጢአትን መርሳት

ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ቆርጣ የምትለይ ምሳር ናት። ሰው ደግሞ በማንኛውም የሕይወት ዘርፍ ፍሬያማ ሊሆን የሚችለው ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ሲኖረው ነው። ይህም አንድነት እንዲጸና ከኃጢአት መጠበቅ÷ የፈጸመውም ኃጢአት ካለ ፈጥኖ ንስሐ መግባት ይጠበቅበታል።

ይሁን እንጂ ሰዎች ኃጢአት ሠርተው ኃጢአታቸውን የሚረሱበት ሁኔታም አለ። ጻፎችና ፈሪሳውያን ሕይወታቸው በኃጢአት ተመልቶ ሳለ «ስታመነዝር አገኘናት» ያሏትን ሴት ይከሷትና በድንጋይ ያስወግሯት ዘንድ ወደ ጌታችን ያመጧት የራሳቸውን ኃጢአት ስለ ረሱት ነው። ሰዎች ኃጢአታቸውን ከረሱ ንስሐ አይገቡም። ይልቁንም ሌሎችን ከሳሾች ይሆናሉ። በሌላውም ይፈርዳሉ። ማቴ.7÷1-5። ለምጻሙ ስምዖን ከጌታ እግር ተደፍቶ ስለ ቀደመው ኃጢአቷ ታለቅስና ምሕረት ከፈጣሪዋ ትለምን ከነበረችው ማርያም እንተ እፍረት የተነሣ - «ይህስ ነቢይ ቢሆን ይህች የምትዳስሰው ሴት ማን እንደ ሆነች እንዴትስ እንደ ነበረች ባወቀ ነበር» በማለት ፈጣሪውን በልቡናው መንቀፍ የጀመረው ኃጢአቱን ስለ ረሳ ነው። ሉቃ. 7÷39።

የእግዚአብሔር ሰዎች ኃጢአታቸውን ዘወትር ያስባሉ። በፈጣሪያቸው ፊትም «እኔ መተላለፌን ዐውቃለሁና ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና» በማለት ኃጢአታቸውን ዘወትር እያሰቡ ያለቅሳሉ። ለነገ ይዋል ይደር ሳይሉም ፈጥነው ንስሐ ይገባሉ። መዝ.50÷3፤ ማቴ.6÷34።

### 2. የመርሳት መንሥኤዎች

እንደ ማናቸውም ክሥተቶች ሁሉ መርሳት የራሱ የሆኑ መንሥኤዎች አሉት። እነዚህን መንሥኤዎች አስቀድሞ ማወቅ ከችግሩ ለመጠበቅ መፍትሔ ይሆናል።

#### ሀ. ከሰይጣን ፈተና የተነሣ

ሰይጣን የማያቋርጥ ተዋጊ ጥንተ ጠላታችን ነው። በመሆኑም በየጊዜው በሃይማኖት እንዳናድግ፣ የሚጠበቅብንን ሐላፊነት እንዳንወጣ ከተማርነው ቃለ እግዚአብሔር የተነሣ በእምነት እንዳናድግ ይፈታተናል። ነገሮችን በማስተዋል እንዳንፈጽማቸው ከልቡናችን ላይ ይወስዳቸዋል። ይህን ጠባዩን ጌታችን በወንጌል፡- «እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ። ወፎችም መጥተው በሉት» በማለት አስረድቷል። ማቴ.13÷3-5።

#### ለ. ከሐሳብ መብዛት የተነሣ

የሰው ልጅ ኑሮውን ለማሸነፍ በሚያደርገው ውጣ ውረድ ብዙ ሐሳቦች በኅሊናው ይመላለሳሉ። ያስጨንቁታል። የሰው አእምሮ መቀበልና ማስታወስ የሚችለው በዐቅምና በልክ ነው። ከዐቅም በላይ ከሆነበት ይረሳል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «... ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» በማለት ያስተማረው ሐሳብ ሲበዛ ሞት እንዳለ ኩነኔም እንዳለ ከማሰብ ሰውን የሚያዘናጋው በመሆኑ ነው። ሉቃ.21÷34።

#### ሐ. አስፈላጊውን ትኩረት ካለመስጠት

አንድ ነገር በልቡናችን ሊጻፍና ልናስታውሰው የምንችለው በሰማንበት ወቅት ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ስንሰጠው ነው። ያለበለዚያ እንደ ዋዛ የምንሰማው ከሆነ መርሳት የተባለው ችግር በኑሮአችን ውስጥ የግድ ይከሠታል። ጌታችን በሚያስተምርበትና የአብነት ሥራዎችን በሚሠራበት ወቅት ደቀ መዛሙርቱን «ይህን ሁሉ አስተዋላችሁን?» እያለ ይጠይቃቸው የነበረው ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጡትሚ ከመርሳትም እንዲድኑ ነው። ማቴ.13÷51።

እስራኤል ዘሥጋ ነቢያቱ ከእግዚአብሔር ተልከው ሲናገሩ በእምነትና በማስተዋል አይሰሟቸውም ነበር። ይልቁንም የነቢያቱ የንስሐ ጥሪ ለእነርሱ እንደ ዘፈንና እንደ ጨዋታ ይታያቸው ነበር። ሕዝ.33÷31-33። በመሆኑም እንደ ነቢያቱ ቃል ንስሐ ከመግባትና ከእግዚአብሔር ጋር ከመታረቅ ይዘገዩ ነበር። ከዚህም የተነሣ እየተማረኩ ወደ ባዕዳን አገሮች ይወርዱ ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም» እንዳለ ቃለ እግዚአብሔር ለእምነትሚ እምነትም ለሥራ የሚያበቃው አንዱን ነገር በትኩረት መከታተል ሲኖር ነው። ዕብ.4÷2። ልድያ ልቡናዋን ጌታ እንደ ከፈተላት /ማስተዋል እንደ ተሰጣት/ ተጠቅሷል። የሐዋ.16÷14-15። ይህ «የልቡና መከፈት» የተገኘው የሐዋርያውን ቃል በትኩረት ትከታተል ስለ ነበረ ነው።

እነዚህና ሌሎችም መንሥኤዎች መርሳትን ሊፈጥሩ ይችላሉ። በመሆኑም ከእነዚህ መንሥኤዎች መጠበቅና እግዚአብሔርን በእምነት በርትቶ መለመን ይገባል። የባሰ የመርሳት ችግር ካለብንም በሕይወታችን፣ በሥራችን፣ በትዳራችንና በማኅበራዊ ኑሮአችን ችግር እንዳይፈጥርብን ልንሠራቸው የሚጠበቁብንን ሥራዎች፣ የተሳልናቸውን ስእለቶች፣ ለወገኖቻችን የገባናቸውን ቃል ኪዳኖች በማስታወሻ መያዝና መጠቀም ይገባል። ይህም አገባብ ነው። እስራኤል በምድረ በዳ ሳሉ ዐሥሩ ትእዛዛት ተሰጧቸው። ከእነርሱ መካከል አንዱ ከመርሳት የተነሣ በዕለተ ሰንበት እንጨት ሲለቅም ተያዘ። እንደ እግዚአብሔርም ቃል በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ። በቀሪው ዘመናቸው ግን ምልክት

***መርሳት ሲያዩት ቀላል ኃጢአት ቢመስልም ከግለሰብ እስከ ሕዝብ ያለውን ለከበደ ችግር የሚዳርግ ኃጢአት ነው። ሌላውን ከመርሳት ጀምሮ ራስን እስከ መርሳት ያደርሳል። የሚጠበቅብንን ነገር መወጣታችንን ብንረሳ እንኳን የማይረሳ እግዚአብሔር አለ።***

የሚሆን ሰማያዊ ጥለት በልብሳቸው ዘርፍ እንዲያሠሩ ተነገራቸው። ዘኍል.15÷32-41። እነዚህን ሁሉ አድርገን የመርሳት ችግራችን የማይወገድልን ከሆነ ከመምህረ ንስሐችን ጋር በመመካከር፣ ጠበል በመጠመቅ ለችግራችን መፍትሔ ማግኘት ይቻላል።

እንግዲህ መርሳት ሲያዩት ቀላል ኃጢአት ቢመስልም ከግለሰብ እስከ ሕዝብ ያለውን ለከበደ ችግር የሚዳርግ ኃጢአት ነው። ሌላውን ከመርሳት ጀምሮ ራስን እስከ መርሳት ያደርሳል። የሚጠበቅብንን ነገር መወጣታችንን ብንረሳ እንኳን የማይረሳ እግዚአብሔር አለ። ስለዚህ እግዚአብሔርን ሆነ ቃሉን ሕዝቡን ሆነ አደራችንን ኃጢአታችንን ሆነ ዞሮ መግቢያችንን ሳንረሳ ለበለጠው መልካም ሕይወት ልንተጋ ይገባናል።



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## በማኅበረ ቅዱሳን የቅዱሳት መካናት ልማትና ተራድኦ ክፍል በመተግበር ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሀገረ ስብከት | የሚተገበርለት ገዳም | በመተግበር ላይ ያለው ፕሮጀክት | የበጎ አድራጊዎች ስም | የብር መጠን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ባሌ | መካነ ሕይወት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም | የወተት ከብት ርባታ | በአሜሪካ እና ሀገር ውስጥ ከሚገኙ ሁለት በጎ አድራጊዎች | 63,000.00 |
| 2 | ምዕ.ጎጃም | ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም | የንብ ማነብ ፕሮጀክት | የግል በጎ አድራጊ | 15,000.00 |
| 3 | ምዕ.ሐረርጌ | ቦኬ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን | የንብ ማነብ ፕሮጀክት | በማኅበረ ቅዱሳን የኮሜርስ ግቢ ጉባኤ 1995 ዓ.ም. ተመራቂዎች | 7,000.00 |
| 4 | ምዕ.ወለጋ | ቂልጡ ካራ | የአትክልት ልማት | [illegible] አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሠራተኛ [illegible] | 12,100.00 |
| 5 | ምዕ.ወለጋ | ቂልጡ ካራ | ምንጭ ማጎልበት | የባንኮች ሠራተኛ ጉባኤና የሸራተን አዲስ ፈለገ አብርሃም መንፈሳዊ ማኅበር | 26,692.90 |
| 6 | ምዕ.ወለጋ | ቂልጡ ካራ | የተማሪዎች መኖሪያ ግንባታ | በሀገር ውስጥ ያሉ አንድ በጎ አድራጊ | 60,000.00 |
| 7 | ምዕ.ሐረርጌ | ደብረ ወገግ አሰቦት አባ ሳሙኤልና ቅድስት ሥላሴ ገዳም | ሽመና | በእታ ለማርያም ባርኪኝ የጽዋ ማኅበር | 23,000.00 |
| 8 | ምዕ.ወለጋ | ቂልጡ ካራ | የንብ ማነብ ፕሮጀክት | የተለያዩ የግል በጎ አድራጊዎች | 50,328.00 |
| 9 | ሰሜን ጎንደር | ዱር አንበሳ ኪዳነ ምሕረት | አነስተኛ መስኖ እና ልማት አትክልት ል | የደብረ ኀይል ቅዱስ ራጉኤል ሰንበት ት/ቤት የጎልማሶች ንኡስ ክፍል | 20,000 |
| 10 | ትግራይ ምዕራባዊ ዞን | ቆየፃ አቡነ ሳሙኤል ገዳም | የንብ ማነብ ፕሮጀክት | የ1995 ዓ.ም የቴክኖ ፋርም ተመራቂዎች | 15,000.00 |



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ በማኅበረ ቅዱሳንና በተለያዩ አካላት ተጠንተው በማኅበረ ቅዱሳን የቅዱሳት መካናት ልማትና ተራድኦ ክፍል ውስጥ የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ከሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶች በከፊል

| ተ.ቁ | ሀገረ ስብከት | የተጠናለት ገዳም/ ደብር/ ቤ/ክ | የፕሮጀክቶች ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ትግራይ ምዕራባዊ ዞን | ቆየፃ አቡነ ሳሙኤል | የሚከራይ ቤት ግንባታ |
| | | | የአብነት ት/ቤት |
| 2 | ትግራይ ምዕራባዊ ዞን | የአቡነ መርዓዊ ክርስቶስ | ንብ ርባታ |
| 3 | ትግራይ ምሥራቃዊ ዞን | ደብረ ገሪዛን ጉንዳጉንዶ ቅድስት ማርያም | የሚከራይ ቤት ግንባታ |
| 4 | ትግራይ ማዕከላዊ ዞን | አባ ሃደራ | ንብ ርባታ |
| | | | ፍየል ርባታ |
| | | | የቤት እድሳት |
| 5 | ትግራይ ማዕከላዊ ዞን | ዳግና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም | ወፍጮ |
| 6 | ትግራይ ማዕከላዊ ዞን | አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ገዳም | ከጣራ ላይ የመጠጥ ውኃ ማሰባሰብ |
| 7 | መቐሌ | የማይታወሩ አቡነ ዐብየ እግዚእ እና ክርስቶስ ሠምራ | የጓሮ አትክልት ልማት |
| | | | ቋሚ ፍራፍሬ ልማት |
| | | | የወተት ከብት ርባታ |
| | | | የመነኮሳት መኖሪያ ቤት ግንባታ |
| 8 | ሰሜን ወሎ | ደብረ ዘመዳ ቅድስት ማርያም አቡነ በርተሎሜዎስ | የዳቦ ቤት |
| | | | የሚከራይ ቤት ግንባታ |
| 9 | ደቡብ ወሎ | አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ | ዐጸደ ሕፃናት ት/ቤት |
| | | | የውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳ |
| | | ደብረ ብርሃን | በግ ርባታ |
| | | ተድባብ ማርያም | የንዋያተ ቅዱሳት ማስቀመጫ ቤት ግንባታ |
| | | ደ/ብ/ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን | በግ ማድለብ |
| 10 | ሰሜን ጎንደር | ዱር አንበሳ ኪዳነ ምሕረት | የንብ ርባታ |
| 11 | ደቡብ ጎንደር | ሳይኮ ኪዳነ ምሕረት | የመጠጥ ውኃ |
| 12 | ምዕራብ ጎጃም | ማየ ሐጹራ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | የዶሮ ርባታ |
| | | ማየ ሐጹራ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | የንብ ርባታ |
| | | አቡነ ገሪማ | መስኖ እና የአትክልት ልማት |
| 13 | ምሥራቅ ጎጃም | ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ | የቤተ መዘክር ግንባታ |
| | | ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ | የእርሻ ልማት |
| | | የደብረ አሚን ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የአብነት ት/ቤት | የቅኔ ቤት ተማሪዎች መኖሪያ ግንባታ |
| | | ዋሻ አምባ ተክለ ሃይማኖት | ወፍጮ |
| 14 | አዊ ዞን | እምነ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ | የንብ ርባታ |
| | | እምነ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ | የሽመናና ልብስ ስፌት |
| 15 | ጅማ | ጅማ መረዋ | የእርሻ ልማት |
| | | አበልቲ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም | የንብ ርባታ |
| | | አበልቲ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም | የአብነት ት/ቤት |
| | | አበልቲ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም | የመጠጥ ውኃ |
| 16 | ከፋ ሸካ ቤንች ማጂ | ደብረ በረከት ኮከብ አቡነ ተክለ ሃይማኖት | ወፍጮ |
| | | ደብረ በረከት ኮከብ አቡነ ተክለ ሃይማኖት | የወተት ላም ርባታ |
| 17 | ምሥራቅ ሸዋ | ዝዋይ ሐመረ ብርሃን | የወተት ላም ርባታ |
| | | ዝዋይ ሐመረ ብርሃን | ዶሮ ርባታ |
| 18 | ሰሜን አሞ | ገዳመ ዮርዳኖስ | ወፍጮ |
| 19 | ደቡብ አሞ | አንቀጸ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት | የመስኖ እና የአትክልት ልማት |
| 20 | ምዕራብ ሐረርጌ | የከሞና ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ | ወፍጮ |



© ማኅበረ ቅዱሳን 

# መንገደኛው
# «ጋብቻ በፎቶ»

/ኃይለ ገብርኤል ዘሐና/

እንዴት ከረማችሁ! የ1997 ዓ.ም. ሪምት ዝናቡ ብርዱ ኀይለኛ ነበር ይባላል:: ከድሮው ጋር በምን መጣሪያ እንዳወዳደሩት ባላውቅም እግዚአብሔር ጊዜ በጥቶን ለመጪው ክረምት ቢያደርሰንም:- «አቤት የዘንድሮው ......» ማለታችን አይቀርም:: በእኛ ልማድ ሁልጊዜ ከትላንት ዛሬ ይብሳል:: መች ይሆን የተሻለ «ዛሬ»ን የምናገኘው::

አይ መንገደኛው! እኔ ክረምት አዝሎት ባመጣው ዝናብ በመንገድ ስንከራተት ሊመታኝ ሲፈልግ እኔ መንገደኛነቴን ትውት፥ በቤቴ ቁጭ፥ ከዚያማ «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገር የዘገየ» እንደ ተባለው አደረግሁ:: ለነገሩማ ሁለት ጆሮ አንድ ምላስ የተሰጠኝ «ሁለቴ ሰምተህ አንዴ ተናገር» ስባል አይደል:: ከዚያማ ሰማሁ ሰማሁ .... ብቻ የተሰማው ሁሉ፣ የታወቀው ሁሉ፣ የታየው ሁሉ አይነገር፥ አይወራ::

«ደግሞ ወደላይ ምን አንጠራራህ?» እንዳትሉኝ እንጂ. አንዳንድ «ሰባኪዎች» አሉ፤ ያዩትን፣ ያነበቡትን፣ የሰሙትን፣ ያወቁትን፣ የዳሰሱትን፣ ያሽተቱትን ፣የቀመሱትን ሁሉ በመድረክ ቆመው ለምእመናን «የሚያስተምሩ»::የአድማጮቹና የተመልካቾቹ ዕውቀት፣ ኑሮ፣ ችግር፣ መፍትሔ፣ ፍላጎት፣ ጊዜ... ምን እንደ ሆነ ያላስተዋለ ሰባኪ «ይዘራል እንጂ. አይሰበስብም»:: ይህቺንም ደግሞ ጥሩ አባባል ናት ብለው በመድረክ እንዳያስተምሩባት.... ምን ላወራላችሁ ነበር? ውይ በሞትኩትii እንደ እንትና ሆንኩ:: እርሷ ለወሬ ከመጓጓቷ የተነሣ አንድ ቁም ነገር ልታወራ ትጀምርና እንደ አንዳንድ ሬድዮ ጣቢያ ይደባለቅባታል:: ሌላውን አውርታ ስታበቃ «ምን ነበር ልነግራችሁ የነበረው?» ትላለች:: አሁን ማን ይሙት እኔን መንገደኛውን «ያሰበችውን ነገር ይነግራታል» ብሎ የሚያስብ አለ? ልቧን ምን ነበር ላወራው የነበረው? ለምን ጉዳይ? ሰሚዬን ይጠቅመዋል? አመለካከቱን አያዛባውም?» ብሎ መጠየቅ አይበጅም::

አዎ፥ አሁን ትዝ አለኝ ላወራላችሁ የነበረው:: «ጋብቻ በፎቶ» ታውቁታላችሁ? አሁን ከሁለት ሰንበት በፊት የሰማሁት ነው:: መቼም እምብዛም አገባብ ባይሆንም ሁለት ሰዎች ሲገናኙ ስለ ሦስተኛ ሰው ማንሣታቸው አይቀርም:: በመልካም ማንሣታቸው ደግ ነው:: በክፉ ማንሣታቸው ግን..... እንትን ነው:: እኛም አነሣንና ማን ናት አይ ከእንትና ጋር አወራን::

«እንትናን አገኘህ ወይ?» አላገኘሁትም:: «ብታገኘው ጥሩ ነበር?» ምነው ደኅና አይደለም ወይ? «ደኅና ነው፤ ብቻ በትዳሩ ደስተኛ አይደለም::» አውጣኝ! ገና ካገባ 40 ቀን እንኳን አልሞላው፥ መቼ ተዋወቁና ነው ደስተኛ ያልሆነው? ቀጠለች እንትና ማስረዳቷን:: ከጋብቻቸው ዋዜማ ጀምሮ ደስተኛ አልነበረም:: እንዴት? ክብርት ሚስት ልትሆነው የተዘጋጀችውን ልጅት ለመጀመሪያ ጊዜ በዐይነ ሥጋ ያየው በጋብቻቸው ዋዜማ ነው:: ይህ ለመንገደኛው የዓመት አግራሞት ነው:: «ወይ ጦርነት!!» አሉ ተገኝ ብረቱ::

እርሷ ሁሉም ከማይቀርባት አገር፣ ከገዳመ አሜሪካ ነበረች /አሁን መንገደኛውም በእግሩ ተጉዞ ሊደርስባት ነው/፤ እርሱ ደግሞ አዲስ አበባ ነበር:: ሁለቱም ትዳርን ያስባሉ:: ሁለቱም ከገዳም ወጥተው አዲስ አበባ ከነወይዘሮ ማንጠግቦሽ ግቢ ካለው ሰርቪስ ቤት ከገደሙት «አባ» ጋር ይተዋወቃሉ:: እርስ በርሳቸው ግን እንኳን ሊተዋወቁ ስለ መፈጠራቸውም አያውቁም:: «አባ» ግን ሁለቱንም ያውቋቸዋል:: እርሷ እርሱን ብታገባ የትዳር እንቆቅልሿ እንደ ሚፈታ እርሱም እርሷን ቢያገባ በኢትዮጵያ ምድር ተቆጥሮ ከማያልቀው ችግር እንደ ሚላቀቅ ያስቡና «ተጋቡ» ይሏቸዋል:: በስልክ ድምፅ ለድምፅ ያስተዋውቋቸዋል:: ፎቶ እንዲ ላላኩ ያደርጓቸዋል:: ፎቶው መቼ የተነሣችው እንደ ኾነ አይታወቅም:: «አባ» ያጣድፏቸዋል:: ሁሉም ይደግሳል:: እርሷም ለሰርጓ ሦስት ቀን ሲቀራት ከች አለች:: በማግሥቱ ዕረፍት አድርጋ በሰርጓ ዋዜማ «አባ» በቀጠሯቸው በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተገናኝተው ይተዋወቃሉ:: ገና ሲያያት ልቡናው እንደ ቁጠማ ስንጥቅ አለ:: ጠላቱ ሰይጣን በሰይፈ ሚካኤል ስንጥቅ ይበልለትና:: በደስታ በፍቅር መሰላችሁ? አይደለም:: ልጅቷ ልክ እንደ «አያቱ» ሆነችበት:: የተቀባባችው ሜክአፕ ቢያደምቃትም የአንገቷን መሸብሸብ ሊደብቅ አልቻለም:: አይተዋት ነገር፥ ሁሉ ነገር አልቋል:: አያገባት ነገር «አለአቻ ጋብቻ» ሆነበት፤ ትረካዋ አበቃ::

መንገደኛው ልቤ «ጋብቻ በፎቶ» ሲል አደነቀ ወይስ ታዘበ ልበል? ደግሞስ አንዱ ለሌላው የመረጠውን ሳይተያዩ ለማግባት መወሰን «አባትን ከማክበር» ወይስ አሜሪካ ለመግባት ከመጓጓት የተነሣ? ሰው ለሰው በጎውን ከመመኘት የተነሣ «እገሊትን ብታገባ፣ እገሌን ብታገቢ» ሊል ይችላል:: ግን ግን ውሳኔውን ሁለቱ ተረጋግተው፣ ጊዜ ሰጥተው፣ ተያይተው፣ ልብ ለልብ ሲገናኙ አይሻልም:: ጎበዝ? ታድያ ምን ይሻላል? አልኳት እንትናን:: «ያው አያቱን እየረዳ መኖር ነው» ብላ እንደ ማሽላ አሣቀችኝ:: ማሽላ ሲያርር ይሥቃል ነው ነገሩ::

መቼም የጋብቻ ነገር ከተነሣ «ጋብቻ በፎቶ» ብቻ ሳይሆን ሌላም አለ:: እናንተ ሰይሙት:: ልጅቷ እንደ ልብ አሜሪካ ለመግባት ለመውጣት ሕጋዊ ፈቃድ ካለው መሥሪያ ቤት ትሠራለች:: የቤቱን ነገር ብዙም አታውቅም:: ጠልታ፥ ንቃ ሳይሆን የሚያሳውቃት፣ እንደ ናትናኤል የሚጠራት አጥታ እንጂ:: በኋላ በሆነ በሆኑ ልጆች በኩል ቤተ ክርስቲያን ሄዳ መማር ትጀምራ ለች:: ቤተሰብ «ዓለምሽን ሳታሳይን» እያለ ያውካታል:: ቤተ ክርስቲያን ወጣ ገባ ስትል ያየና መሥሪያ ቤቷን ያጠና አንድ «ጎበዝ» ወጥሮ ይይዛታል:: እናንተ ይህን ሱሪ በአንገት የሚል ነገር መጠርጠር አይከፋም:: «እሽ በይኝ» ውጥረት፣ «ቶሎ እንጋባ» ውጥረት፣ «ከጋብቻ በፊት በሥጋ ፈቃደ እንተዋወቅ» ውጥረት፣ «እንፈራረም» ውጥረት... «እንፋታ» ውጥረት:: ሰውረን አውጣን በሉ:: «ለሁሉ የሚቸኩል ሌባ ነው» ይባላል:: ዘግኖ፣ አፍሶ ለመሮጥ የሚቸኩል ሌባ ነው::

እነዚያ ወደ ቤተ ክርስቲያን ያቀረቧት ልጆች «እናውቀዋለን፥ አግቢው» ብለው አጣደፏት:: ለመንገደኛው የሚከብደው ነገር «ሰውን ዐውቀዋለሁ» ማለት ነው:: መልኩን፣ የትምህርት ደረጃውን፣ ቤቱን፣ ስሙን ላውቀው እችላለሁ፤ ልቡን ግን እንዴት? እማማ ወለቱ እኮ ናቸው ዘወትር «የወፍ ወንዱ የሰው ሆዱ» አይታወቅም የሚሉት:: ያማረ ሥራ እንዳለው፣ ቤት እንዳለው፣ የቤተ ክርስቲያን ሰው እንደ ሆነ መሰከሩለት:: ድል ያለ ድግስ ተደግሶ ተጋቡ:: «Honey moon» የጫጉላ ሽርሽራቸው ለንደን፣ አሜሪካን አሳለፉ:: በጋብቻ ምክንያት የአሜሪካ የይለፍ ወረቀት /entrance Visa/ ያዘ:: በሰላም ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ:: ወዲያው ጠባዩ ተለወጠ:: ጀርባ አዙሮ መተኛት፣ ምግብ አልበላም ማለት ጀመረ:: በስተመጨረሻ ተደብቋት ሽው ወደ አሜሪካ:: እርሷ ፍለጋ እዚህ ትንከራተት ጀመረች:: እኔን!! በኋላ በቀጭን ሽቦ «ቻው በቃሽኝ» አላት:: ለካ አጅሬው ብዙ ጊዜ አሜሪካ ወደ ሚኖሩ ዘመዶቹ ሊሄድ ብሎ አልሳካለት በማለቱ አመቺ ሁኔታ ፍለጋ ሲያደፍጥ ነበር:: «ወይ ሰው» አለች አሉ ቀበሮ:: እርሷ ባትልም መንገደኛው ብሏታል::

እንግዲህ ምን ይሁን? ሰዉ በሽማግሌ፣ በማዘጋጃ፣ በሥጋ ወደሙ ቢያገባ አልጸና አለ:: ጎበዝ! ኑ «አውጣን፥ አውጣን» እንበል:: እንዲህ ቢሆንስ ራሳችንን ስናስተዋውቅ ያለንበት አገርና መሥሪያ ቤቱ ቢቀርስ? «ከአሜሪካ መጣሁ:: እዚያ ነው የምኖረው» ሲባል ሰው መሰላል ወይም ድልድይ ሁነኝ /ሁኚኝ/ የሚል ከሆነ፣ «መሥሪያ ቤቴ ከዚህ ነው» ሲባል ከሰውየው /ከልጅቷ/ ጀርባ ያለው <ቢዝነስ> የሚታሰብ ከሆነ፣ እነ <አባም> የትዳር ክቡርነት ሳይሆን የልጆቻቸው ጊዜያዊ ችግር መፈታት ብቻ የሚታያቸው ከሆነ ምን ይበጃል? መንገደኛው እንደ ሆነ ጣጣውን ጨርሷል:: ሥራው መሄድ.... ኑሮው አይታወቅ.... በቃ:: መንገደኛው፥ ሱባዔውን ጨርሶ መንገድ እስኪ ጀምር በጸሎት አስቡኝ ይላችኋል::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org


አዲስ የቪዲዮ ፊልም
ብዙ ምዕመናን በጉጉት ሲጠብቁት የነበረው ዘጋቢ ፊልም።
"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትላንት ዛሬና ነገ"
በቪድዮ ካሴት እና በቪሲዲ ተዘጋጅቶ ስርጭት ላይ ውሏል።
በውስጡ:-
የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
ቅዱሳት መካናት
ቅዱሳት መጻሕፍት
ቅዱሳት ሥዕላት
ንዋያተ ቅድሳት
ዜማ
ከመንፈሳዊ ትርጉማቸው እና ጥቅማቸው ጋር በዝርዝር ቀርቧል።
አዘጋጅ:- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች
ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን
ስልክ 011-122-86-01 11-123-42-26
የናግራን ሰማዕታት
- በ6ኛው መ/ክ/ዘ በዛሬዋ የመን ናግራን በተባለችው ከተማ የነበሩት ክርስቲያኖች ስለሃይማኖታቸው የከፈሉት መስዋዕትነት
- የአፄ ካሌብን አስደናቂ ዘመቻ እና የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት የሚያሳይ ጥናታዊ መጽሐፍ
ዋጋ ብር 5.00
አርተር:- ዲ.ን ዳንኤል ክብረት
አሳታሚ:- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ዋጋ ብር 3.50
በበረሐው ጉያ ውስጥ
ከ3ኛው - 5ኛው መ/ክ/ዘ በግብጽ በረሐዎች በምናኔ የነበሩ አበው እና እማት ሕይወት፣ ምክርና ትምህርት
- አባባሎች
- ታሪኮች
- ምክሮች
- የኑሮ መፍትሔዎች
- ከሰይጣን ጋር የመዋጊያ ስልቶች የቀረቡበት ለሕይወት መመሪያ የሚሆን መጽሐፍ
አዘጋጅ - ዲ/ን ዳንኤል ክብረት
አሳታሚ - ማኅበረ ቅዱሳን
ዋጋ ብር 8.00
መንፈሳዊ ሕይወት ምንድንነው?
ታላቁ አባ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ የጻፈው፣ የሙሴን ሕይወት መሠረት በማድረግ የሰበከው
- የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃዎች
- ፍጹምነት
- ተጋድሎ
- ፈተናዎች፣ ወዘተ በተመለከተ ያስተማረበት መጽሐፍ
አዘጋጅ - ዲ/ን ዳንኤል ክብረት
አሳታሚ - ማኅበረ ቅዱሳን
ዋጋ ብር 10.00
ሜጋ ማተሚያ ድርጅት

© ማኅበረ ቅዱሳን

© ማኅበረ ቅዱሳን
ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣ እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው።